አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# የዲዚ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ

በ
ደስታ ወ/መስቀል

ሰኔ/ 2006 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# የዲዚ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ

በ

ደስታ ወ/መስቀል

ሰኔ/2006 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| የአማካሪ ስም | ፊርማ |
| ---------------------------------- | ---------------------------- |
| የውስጥ ፈታኝ ስም | ፊርማ |
| ---------------------------------- | ---------------------------- |
| የውጪ ፈታኝ ስም | ፊርማ |
| ---------------------------------- | ---------------------------- |

# ምስጋና

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ከመጀመሩ በፊት ጀምሮ እስከ ፍጻሜው ድረስ ረቂቅ በማስተካከል እና አስፈላጊውን እርማት በሰዓቱ በመስጠት ለዚህ እንድበቃ ላደረጉኝ ውድ መምህሬ ለዘሪሁን አስፋው ምስጋናዬ ከልብ የመነጨ ነው፡፡ በተጨማሪም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት በጀት መድቦ ይህንን ጥናት እንድሰራ ለስለረዳኝ አመሰግናለሁ፡፡

መረጃ በምሰበስብበት ወቅት አብረውኝ በመሆን ስራዬን ቀላል እንዲሆን ላደረጉልኝ ለአቶ ዘለቀ ገሩ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ የትርጉም ስራ ለማሰራት ቢሮህ በመጣሁ ጊዜ ከስራህ ብዛት የተነሳ ራስህን እና ጊዜህን አጨናንቀህ ከስራ ባልደረቦችህ ጋር አብረህ ለመስራት ፍቃድህን በደስታ ለገለጽክልኝ ለጋዜጠኛ ካሳሁን ሽብሩ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡

በመስክ ቆይታዬ አስፈላጊውን እገዛ ላደረጋችሁልኝ ለማጂ ወረዳ የባህል እና ቱሪዝም ቢሮ ሰራተኞች፣ እንዲሁም በቆይታዬ ወቅት ከፍተኛ ትብበር ላደረጋችሁልኝ (ለወ/ሮ ትዝታ እሸቴ እና ወ/ሮ ገነት እሸቴ ከነቤተሰቦቻችሁ) ስላደረጋችሁልኝ ትብብር አመሰግናለሁ፡፡ በቤተሰቦቼ እና ጓደኞቼ (እናቴ፣ ባለቤቴ፣ የክፍል ጓደኞቼ እንዲሁም ውቤ ታደገ) የእናንተ እገዛ ለጥናቴ ትልቅ አስተዋጽኦ ነበረውና ምስጋና ይገባችኋል፡፡

# ማውጫ

**ይዘት** **ገፅ**

ምስጋና ........................................................................................ I
አጠቃሎ ........................................................................................ V
ምዕራፍ አንድ፡ መግቢያ ........................................................................ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................................................ 2
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................................ 2
1.3 የጥናቱ አላማ ........................................................................ 3
1.4 የምርምር ጥያቄዎች ............................................................ 4
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ................................................................ 4
1.6 የጥናቱ ወሰን ........................................................................ 4
1.7 የጥናቱ ዘዴ ........................................................................ 5
1.7.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ...................................................... 5
1.7.1.1 ምልከታ ........................................................................ 6
1.7.1.2 ቃለ መጠይቅ ................................................................ 7
1.7.1.3 ተተኳሪ ቡድን ውይይት ...................................................... 8
1.7.2 የመረጃ አተናተን ............................................................ 8
1.8 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ...................... 9
1.9 የመስክ ተሞክሮ ................................................................ 9
ምዕራፍ ሁለት፡ ክለሳ ድርሳን ...................................................... 13
2.1 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ...................................................... 13
2.2 ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት ............................................................ 21
2.2.1 ሞት ........................................................................ 21
2.2.2 ለቅሶ ........................................................................ 22
2.2.3 ማህበራዊ ደረጃና የለቅሶ ስርዓት ............................................ 23
2.2.4 የሙሾ ቃል ግጥም .............................................................. 23
2.3 ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ............................................................ 24

ምዕራፍ ሶስት፡ አካባቢያ ዳራ ....................................................................................28
3.1 የዲዚ ብሄረሰብ መገኛ ...........................................................................28
3.2 የወረዳው መልክዓ ምድር አቀማመጥ ............................................... 28
3.3 ቋንቋ ........................................................................................... 29
3.4 ታሪካዊ አመጣጥ ............................................................................ 29
3.5 ባህላዊ እሴቶች............................................................................. 30
3.5.1 ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት "ታርቅ ሲ" .................................... 30
3.5.2 ባህላዊ አልባሳት ................................................................. 32
3.5.3 ባህላዊ የአመጋገብ ስርዓት ..................................................... 34
3.5.4 ባህላዊ የሙዚቃ መሳርያዎች.................................................... 35
3.5.5 የጋብቻ ስርዓት .................................................................... 36
3.5.6 የሃይማኖት ተቋማትና ሀገረሰባዊ ዕምነቶች ................................ 37
3.6 ባላባታዊ የአስተዳደር ስርዓት "ቡርጅ ያብ"........................................ 37
ምዕራፍ አራት፡ የዲዚ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ...................................... 41
4.1 የባላባቶች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ....................................................... 42
4.1.1 የኑዛዜ ስርዓት ...................................................................... 43
4.1.2 ከቀብር በፊት........................................................................ 45
4.1.2.1 ውርስ(ቂዝ) ................................................................. 47
4.1.2.2 የውርስ ደንብ ................................................................ 48
4.1.2.2 የአንጀት ማንበብ ስርዓት (ኢብ-ጋብስ)................................... 51
4.1.2.3. የውሀ መርጩት ስርዓት (ቼድ) ........................................ 55
4.1.3 ጊዜ ቀብር ............................................................................ 68
4.1.4 ድህረ ቀብር........................................................................... 70
4.2 የአዛውንቶች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ "ታል"......................................... 71
4.2.1 ቅድመ ቀብር........................................................................ 71
4.2.2 ጊዜ ቀብር .............................................................................. 75
4.2.3 ድህረ ቀብር ........................................................................... 76

4.3 የጎልማሶች እና የወጣቶች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ.................................... 78

4.3.1 ከቀብር በፊት ..................................................................... 79

4.3.2 ከቀብር በኋላ ..................................................................... 82

4.4 የሕፃናት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ "ኩም" ................................................... 82

4.5 የዲዚ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ማህበራዊ ተግባራት ............................. 84

4.5.1 ለቅሶ የባላባታዊ ስርዓት ሽግግር ከማስቀጠል አንጻር.................... 84

4.5.2 ለቅሶ ማህበራዊ አንድነትን ከማጠናከር አንጻር ............................ 85

4.5.3 ለቅሶ የማህበረሰቡን ታሪክ፣ እምነትና አመለካከት

ከመግለጽ አንጻር ...................................................................... 86

ምዕራፍ አምስት፡ ማጠቃለያ ......................................................................... 87

ዋቢዎች .......................................................................................................... 89

አባሪዎች

# አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የዲዚ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ ጥናቱ የሚያተኩረው በዲዚ ብሄረሰብ የለቅሶ ስነ ስርዓት ላይ ነው፡፡ የጥናቱ አላማ የዲዚ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ላይ ገላጭ ትንተና በማድረግ ስርዓቱን ማሳየት ነው፡፡ አላማውን ለማሳካት በዋናነት ምልከታ፣ ቃለመጠይቅ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተካሂድዋል፡፡ በሶስት ተፈጥሯዊ የለቅሶ መቼቶች ላይ በመገኘት መረጃው ተሰብስቧል፡፡

በተገኘው መረጃ መሰረት የዲዚ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ በአራት ተከፍሎ እንደሚከወን ታውቋል፡፡ በዲዚ ብሄረሰብ በእድሜ፣ በጾታና በማህበራዊ ደረጃ አንፃር የተለያዩ የለቅሶ ክዋኔዎች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከማህበራዊ ደረጃ አንጻር ስንመለከተው ሟች የጎሳ መሪ፣ የሐገር ሽማግሌ፣ የእምነት መሪ ወዘተ ከሆኑ የሚከወንላቸው ስርዓት የሟችን ተግባርና ማንነት የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔውን ከዕድሜ እንዲሁም ከጾታ አንጻር ስንመለከተው የሴት እና የወንድ በቀብር ቦታ አቆፋፈርን እና የቀብር አቅጣጫን እንደሚወስኑ ጥናቱ ጠቁሟል፡፡

የጥናቱ ግኝት የለቅሶ ስርዓቱ የባላባት ስርዓት ሽግግርን የሚያጠናክሩበት እና የሚገነቡበት፣ ማህበራዊ አንድነታቸውን የሚያጠናክሩበት እንዲሁም የማህበረሰቡን ታሪክ፣ እምነትና አመለካከት የሚገልጹበት መንገድ መሆኑን ያሳያል፡፡ በክዋኔ ውስጥም የሚተላለፉ መልዕክቶች እና ትርጓሜዎች በጥናቱ ውስጥ ተካትተዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ፡ መግቢያ

በፎክሎር ጥናት ዘርፍ ውስጥ በርካታ ባህላዊ ስርዓቶችና እሴቶች ይጠናሉ፡፡ ከእነዚህ ባህላዊ ስርዓቶች እና እሴቶች መካከል አንዱ የለቅሶ ስነ ስርዓት ነው፡፡ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔዎችን በማጥናት የማህበረሰቡን አኗኗር፣ ባህል፣ ማንነት፣ አስተሳሰብ እና የህይወት ፍልስፍና የሚጠቁሙ ጉዳዮችን ማግኘት ይቻላል፡፡

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በዲዚ ብሄረሰብ የለቅሶ ስነ ስርዓት ላይ ነው፡፡ ጥናቱ በክዋኔው ወቅት የሚታዩ የፎክሎር ዘሮች ለምሳሌ (ሀገረሰባዊ ልማዶች፣ ስነ ቃሎች፣ በስርዓቱ ክዋኔ ላይ የሚታዩ ቁሳዊ ባህሎች፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት) እና ማህበረሰቡ ለእነዚህ ክዋኔዎች ያለው አመለካከትም ይቃኛል፡፡ ጥናቱ በአምስት ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው፡፡

በምዕራፍ አንድ ጥናቱን ለማጥናት ያነሳሱ ምክንያቶች÷ የጥናቱ ዋናና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ መረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ ዘዴዎች፣ ጥናቱ በሚካሄድበት ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች እንዲሁም የመስክ ተሞክሮ ተካትቷል፡፡

ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳን የቀረበበት ሲሆን ሁለት ንዑሳን ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመርያው ክፍል ከዚህ ጥናት ጋር የሚዛመዱ ቀደምት ጥናቶችና ጽሁፎችን በመመልከት ከዚህ ጥናት ጋር በምን እንደሚመሳሰሉና እንደሚለያዩ የተዳሰሰበት ክፍል ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል የንድፈ ሃሳብ ቅኝት የቀረበበት ሲሆን በተለይ ለጥናቱ ወሳኝ የሆኑ የክዋኔ ንድፈ ሃሳቦች የሚቃኙበት ነው፡፡

ሶስተኛው ምዕራፍ የዲዚ ብሔረሰብ አጭር ማስተዋወቂያ የሚቀርብበት ሲሆን ስለብሔረሰቡ ቋንቋ፣ ታሪካዊ አመጣጥ፣ የጋብቻ ስነ ስርዓት፣ የበዓላት አከባበር፣ ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት፣ ባህላዊ አልባሳት፣ ባህላዊ የአመጋገብ ስርዓት እና እምነት የሚሉ ንኡሳን ክፍሎች አሉት፡፡

አራተኛው ምዕራፍ ከመስክ የተገኙ መረጃዎች የሚተነተኑበት ሲሆን የመጨረሻውና አምስተኛው ምዕራፍ የጥናቱ ማጠቃለያ የቀረበበት ነው፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የዚህ ጥናት ዋንኛ ትኩረት የዲዚ ብሔረሰብን የለቅሶ ክዋኔ መግለጽ ነው፡፡ የዲዚ ብሄረሰብ በርካታ ባህላዊ እሴቶች ያሉት ሲሆን ከእነዚህ መካከል አንዱ የለቅሶ ስርዓት ነው፡፡ ይህ ስርዓት የተለያዩ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን የያዘ ነው፡፡ ብሄረሰቡ ከለቅሶ ስርዓቱ ጋር አያይዞ የሚከውናቸው ክዋኔዎች በርካታ ናቸው፡፡

በዲዚ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ውስጥ ከለቅሶ ስርዓተ ክዋኔው ተነጥለው የማይታዩ የሙሾ ቃል ግጥሞች፣ ቁሳዊ ባህሎች፣ ሀገረሰባዊ እምነቶች እና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባቶች አሉት፡፡

በለቅሶው ስርዓት ላይ ድምቀትን የሚሰጡና የሟችን ክብርና ማንነት ለመግለጽ የሚጠቀሙባቸው ስነ ቃሎች (ሙገሳዎች፣ ፉከራ፣ ቀረርቶ እንዲሁም የሙሾ ቃል ግጥሞች) አሏቸው፡፡ ስርዓቱ ሲከወን የሚታዩት ሙዚቃዎች እና ሙዚቃውን ተከትለው የሚመጡ እንቅስቃሴዎችን ለክዋኔው ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡

የሟች ዘመዶችና ቤተሰቦች በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ለማልቀሻነት ይዘዋቸው የሚወጡት እንደ ጦር፣ ጋሻ፣ ከበሮ ፣ቃጭል ወ.ዘ.ተ እና የለቅሶ ስርዓቱን ለማከናወን የሚደረጉ ዝግጅቶች (የምግብ፣ አዲስ ቤት መስራት) በቁሳዊ ባህል ስር የምንመለከታቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

ሌላው በለቅሶ ስርዓት ላይ የሚከወኑ ልማዳዊ ተግባራት ( ከብትን ቀጥቅጦ ማረድ፣ አንጀት ማንበብ፣ ውሃ መርጨት፣ ተስካር ማውጣት ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡

የእነዚህ ክዋኔዎች ተግባር ሟችን ለማስታወስ፣ ብሄረሰቡ ያበጀውን ስርዓት ለመፈጸም እንዲሁም ማህበራዊ ህይወታቸውን ለማጠናከር ነው፡፡ ይህ ስርዓት ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍበት መንገድ ደግሞ ክዋኔ ነው፡፡ በክዋኔው ወቅት የሚታዩ ስነ ቃሎችን፣ ቁሳዊ ባህሎችን እና ልማዶችን ከክዋኔው ጋር በማጣመር በጥናቱ ይገለጻሉ፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለማድረግ ያነሳሱኝ ምክንያቶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው፡፡

- በ2005 ዓ.ም ወደ ማጂ አካባቢ በለቅሶ ምክንያት ሄጄ ነበር፡፡ የቀብር ስነ ስርዓቱ የሚፈጸምላቸው ሰው በማጂ አካባቢ ለ50 ዓመታት የቆዩ የአማራ ብሄረሰብ

ተወላጅ ሲሆኑ ለሳቸው የሚደረገው የለቅሶ ስርዓት በሁለት የተከፈለ ነበር፡፡ የአማራ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት እና የዲዚ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ፡፡ በአካባቢው የሚገኙ የሟቹ የቅርብ ጓደኞች፣ ጎረቤቶች፣ እንዲሁም የሃገር ሽማግሌዎች በስርዓቱ ላይ ተገኝተው በአካባቢው ባህል መሰረት ሃዘናቸውን ሲገልጹ፣ የሟች ቤተሰቦች እና ከሌላ አካባቢ የመጡ ሰዎች ደግሞ በራሳቸው ባህል መሰረት ሃዘናቸውን ሲገልጹ ተመልክቻለሁ፡፡ ለማህበረሰቡ እንግዳ በመሆኔ ስርዓቱ እጅጉን አስደንቆኝ ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከአካባቢው ብዙም ሳይርቅ የዲዚ ብሄረሰብ አባል የሆኑ እንዲት እናት የለቅሶ ስርዓት ላይ ተገኝቼ ነበር፡፡ እነዚህን የለቅሶ ስርዓቶች በማየቴና በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በስራ አጋጣሚ ለብሄረሰቡ እና ለባህሉ ስለቀረብኩ የብሄረሰቡን የተለየ የለቅሶ ስርዓት በይበልጥ ተጠግቼ ለመመርመር እና ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት ስላስደረብኝ ነው፡፡

- ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በዲዚ ማህበረሰብ ዙርያ ፎክሎራዊ ጥናቶች ያልተኪያሂዱ በመሆናቸው ይህ ጥናት አካባቢውን፣ ብሄረሰቡን እንዲሁም ባህሉን ከማስተዋወቅ አንጻር የራሱ የጎላ ድርሻ አለው ብዬ ማሰቤ ነው፡፡
- ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ባወጣቸው ጽሁፎች ላይ ብሄረሰቡ ቀድሞ የነበረው ባህል እና የክዋኔ ስርዓት እየቀነሰና እየጠፉ መሆኑን፣ እንዲሁም ማህበረሰቡን የሚመለከቱ ጥናቶች በስፋት ያልተጠኑና ያልተሰነዱ መሆናቸው በመገለጹ፣ የለቅሶ ስርዓቱን እና ከስርዓቱ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን አሁን ባሉበት ደረጃ ለመሰነድ ያለኝ ፍላጎት ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የዲዚ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ላይ ገላጭ ትንተና በማድረግ ስርዓቱን ማሳየት ነው፡፡ በተጨማሪ ይህ ጥናት የሚከተሉት ንዑሳን አላማዎች አሉት፡፡

- ✓ የክዋኔውን ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳ መግለጽ፣
- ✓ በስርዓቱ ላይ የሚታዩ ትዕምርቶችን መተርጎም፣
- ✓ በክዋኔው ወቅት ጾታ፣ ማህበራዊ ደረጃ እና ዕድሜ ያላቸውን ሁኔታ ማሳየት፣
- ✓ ከለቅሶ ስርዓቱ ጋር ተያይዘው የሚታዩ ፎክሎሮችን( ሃገረሰባዊ እምነቶች፣ ስነ ቃሎች፣ ቁሳዊ ባህል እንዲሁም ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት) መግለጽ፣

- ✓ በዲዚ ብሄረሰብ የለቅሶ ስነ ስርዓት ከጊዜ ወደ ጊዜ የታዩ ለውጦች ምንድን እንደሆኑ መግለጽ እና የለውጦቹን ምክንያት ማሳየት ናቸው፡፡

## 1.4 የምርምር ጥያቄዎች

ጥናቱ የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡

1. ዲዚዎች ስለ ሞት ያላቸው እሳቤ ምን ይመስላል?
2. በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚታየው ክዋኔ ትርጉም ምንድነው?
3. ለቅሶ በዲዚ ብሔረሰብ ዘንድ እንዴት ይገለጻል?
4. በዲዚ ብሄረሰብ የተለየ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ የሚደረግላቸው ሰዎች አሉ? እነማን ናቸው? ልዩነቱ ከምን የመነጨ ነው?

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የዲዚ ብሄረሰብን የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ መጠናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

1. በዲዚ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ምን አይነት ፎክሎራዊ ገጽታ እንዳለው ያስተዋውቃል፡፡
2. ከዚህ ቀደም ብሄረሰቡ ላይ ፎክሎራዊ ጥናት የተደረገ ባለመሆኑ በብሄረሰቡ ዙርያ ሌሎች ጥናቶች እንዲደረጉ ሊያነሳሳ ይችላል፡፡
3. የዲዚን ብሄረሰብ ባህላዊ ማንነት ለማወቅ ለሚሹ መጠነኛ መረጃ ይሰጣል፡፡
4. ከፎክሎራዊ ጠቀሜታው በተጨማሪ የብሔረሰቡን ባህልና ገጽታ የሚያሳይ በመሆኑ ለአካባቢው የቱሪዝም እድገት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት አቢይ ትኩረት የዲዚ ብሔረሰብ የለቅሶ ሥርዓተ ክዋኔን ማሳየት ነው፡፡ በዚህም ይህ ጥናት የተወሰነው ብሄረሰቡ ከሚኖርባቸው ሁለት ወረዳዎች መካከል በማጂ ወረዳ ላይ ብቻ ነው፡፡ በማጂ ወረዳ ውስጥ ባሉ 22 ቀበሌዎች ላይ ያተኩራል፡፡ ጥናቱ በቤሮ ወረዳ የሚኖሩ ዲዚዎችን አያጠቃልልም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ደግሞ በቤሮ ወረዳ የሚገኙ የብሄሰቡ አባላት በብዛት ከሌሎች ብሄረሰቦች ጋር ተሰባጥሮ በመኖሩ ነው፡፡

በመሆኑም ጥናቱ የተወሰነው በመሀል ማጅ አካባቢ በሚኖሩ የዲዚ ብሔረሰቦች የለቅሶ ሥርዓት ላይ ብቻ ነው፡፡

የጥናቱ ወሰን በመሃል ማጂ የተከለለውም በአሁኑ ወቅት ቦታው ሰላማዊ በመሆኑና መረጃ በቀላሉ ማግኘት ስለሚያስችለኝ እንዲሁም በአብዛኛዉ የዲዚ ብሄረሰብ ባህል የሚገኝበት ከመሆኑ በተጨማሪም በአካባቢው ከሚኖሩ ህዝቦች መካከል 83.42% ያህሉ ዲዚዎች በመሆናቸው ጥናቱ በዚህ ቦታ ላይ ተወስኗል፡፡ አውዱን መነሻ በማድረግም በክዋኔው ላይ የሚታየውን ባህላዊ ስርዓትና ቁሳቁሶች ትርጉም ያጠናል፡፡ በመሆኑም በክዋኔው ወቅት ሟችን እና የሟች ቤተሰቦችን በማስመልከት የሚቀርቡ የተለያዩ ስነ ቃሎች (ሙሾ፣ ፉከራ፣ ቀረርቶ እንዲሁም ሙገሳ)፣ ቁሳዊ ባህሎች የመሳሰሉትን በመቃኘት ትንታኔው ቀርቧል፡፡

## 1.7 የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ጥናት የምጠቀመው ዘዴ ገላጭ የምርምር ዘዴን ነው፡፡ ለዚህም ዋነኛ ምክንያቴ ገለፃ በትንታኔ ወቅት የምናስቀድመው ተግባር ሲሆን እኛ ያየነውን ክዋኔ ያላዩት ሰዎች በአእምሯቸው እንዲቀርፁት ማድረግ ስለሚያስችል ነው፡፡ በተጨማሪም በተፈጥሮአዊ መቼቶች በተገኙ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ትንታኔ ለመስጠት ስለሚረዳ ነው፡፡

ጥናቱ የሚከተለው ንድፈ ሃሳብ የክዋኔ ንድፈ ሃሳብ ነው፡፡ ይህ ንድፈ ሃሳብ የተመረጠበት ምክንያት ጥናቱ ክዋኔ ተኮር በመሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ንድፈ ሃሳብ ክዋኔውን፣ የሚከወንበትን አጋጣሚ፣ ታዳሚን፣ የክዋኔ ቦታና ማህበራዊ አውዶችን፣ መልዕክት፣ አቀራረብ የሚመለከት በመሆኑ

መረጃ ለመሰብሰብ ተፈጥሯዊ መቼትን የተጠቀምኩ ሲሆን ይህን መቼት የመረጥኩበት ምክንያት ክዋኔው በሌላ መቼት ቢሰበሰብ የመረጃውን ምልዑነት ሊያሳጣው ስለሚችል እንዲሁም ክዋኔውን በተፈጥሯዊ መቼት ለማግኘት አስቸጋሪ ባለመሆኑ ነው፡፡

### 1.7.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለፎክሎር ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች በተፈጥሮአዊ በመቼታቸው ሊሰበሰቡ ይገባል፡፡ መረጃዎቹን መመልከት፣ መሰብሰብና መሰነድ የጥናቱ ተገቢ በሆነ መንገድ ነው፡፡ Goldstein የተለያዩ መረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች መኖራቸውን ገልጸው የተሟላ

መረጃ ለመሰብሰብ ጥልቀት ያለው መረጃ አሰባሰብ ዘዴ ተመራጭ መሆኑን ይመክራሉ፡፡ (1964፡65)፡፡

ከመስክ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ደግሞ ጥናቱ መስክ ወጥቶ መረጃ መሰብሰብን ስለሚጠይቅ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቆች እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት በመታገዝ መረጃዎች ይሰበሰባሉ፡፡ ይህን አስመልክቶ ፈቃደ አዘዘ

*"የመስክ ምርምር ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሲሆን በሶስት ልዩ ልዩ መንገዶች ሊካሄድ ይችላል፡፡ እነሱም ምልከታ (observation)፣ ኢንተረቪው (interview) እና መጠይቅ (qu estioner) ናቸው፡፡ የመስክ ምርምር በብዙ ሙያተኞች ዘንድ አስፈላጊና ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡" (1991፡90) በማለት ይመክራሉ፡፡*

እነዚህ የፎክሎር የመስክ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ርስ በርስ ተደጋጋፊና የመረጃ ክፍተት እንዳይኖር የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ይህም በአንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ያልተገኘን ወይም አጠራጣሪ መረጃ በሌላ በመንገድ በመፈተሽ ማረጋገጥ ስለሚቻል ነው፡፡ እነዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ለምን እና እንዴት እንደምጠቀም እንደሚከተለው እገልጻለሁ፡፡

### 1.7.1.1 ምልከታ

በዚህ ጥናት ምልከታ አስፈላጊና አይቀሬ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በቦታው በመገኘት እና የለቅሶ ስርዓቱን በመመልከት በገላጭ የምርምር ዘዴ ለመተንተን ስለሚረዳኝ በዋንኛነት ተጠቅሜያለሁ፡፡ በዚህም በክዋኔው ወቅት የሚታዩትን የከዋኞችን ሁኔታ እንዲሁም የክዋኔውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለመመልከት ያግዛል፡፡ ምልከታ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ያለውን ጠቀሜታ Goldstein እንደገለጹት፡-

"*The term 'obsrvation' as used in this context, is not limited oniy to visual aspects of the situation, but also involves a full range of sensual experience including hearing, feeling, smeling and testing, whenever these may be appropriate." (1964:77)፡፡*

ከምልከታ አይነቶች ውስጥ ለጥናቴ የተጠቀምኩት ኢተሳትፏዊ ምልከታን *(non-participatory observation)* ነው፡፡ ይኸውም የማህበረሰቡን ባህል እና ቋንቋ በሚገባ ባለማወቄ ነው፡፡ ነገር ግን ተፈጥሯዊውን አውድ በመጠቀም መረጃውን ሰብስቤያለሁ፡፡

ምልከታውን የተሟላ ለማድረግ በምልከታው ወቅት በፎቶግራፍና በቪዲዮ በመቅረፅ ትክክለኛውን መረጃ ለትንታኔው ተጠቅሜያለሁ፡፡ በምልከታው ወቅት 90 ፎቶግራፎች፣ 20GB የሚሆን ቪዲዮ፣ በመጠቀም መረጃውን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ በመስክ ቆይታዬ በሶስት ተፈጥሮአዊ መቼቶች ላይ ምልከታ አኪያሂጃለሁ፡፡

#### 1.7.1.2 ቃለ መጠይቅ

ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በምልከታ ወቅት ያየኋቸው እና ማህበረሰቡ እንዲመልስልኝ የምፈልጋቸውን ጥያቄዎች እንድጠይቅ ስለሚያግዘኝ ልመርጠው ችያለሁ፡፡ ቃለ መጠይቅ ጠያቂና ተጠያቂ ፊት ለፊት ተቀምጠው የሚያደርጉት የሃሳብ ልውውጥ በመሆኑ ጠያቂው የመላሹን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ማለትም አካላዊ ገለጻን፣ ስሜትን፣ ድምጸትን በመከታታል መረጃን የሚያገኝበት መንገድ ነው፡፡ Goldstein ቃለ መጠይቅን *“The method used by the field workers to obtain data about ideas or events outside the context of the interview itself through questioning persons believe or known to have that informant.”* (1964:77-78) በማለት ይገልጹታል፡፡

መረጃውን ከመረጃ አቀባዮች መሰብሰብ ይቻል ዘንድ ቃለ መጠይቁ በሁለት መንገድ የተከፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው መረጃ አቀባዮችን ከመጠየቄና ከማግኘቴ በፊት ቀድሜ የተዋቀረ ቃለመጠይቅ ያዘጋጀሁ ሲሆን ይህም ሰፋ ያለ ውይይት ለማድረግ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከመረጃ አቀባዮቼ ጋር ተገናኝቼ ቃለመጠይቅ በማደርግላቸው ወቅት ከማያቸውና ከምሰማቸው መረጃዎች በመነሳት ለምን? እንዴት? ከዚያስ? ወዘተ በማለት ያልተዋቀረ ቃለመጠይቅ አካሂጃለሁ፡፡

በመስክ ቆይታዬ በወረዳው የተለያዩ ቀበሌዎች በመዘዋወርና መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ለሆኑልኝ ለአስራ ዘጠኝ መረጃ አቀባዮች ቃለመጠይቅ አድርጌያለሁ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዘጠኙ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ሲሆኑ አስሩ ደግሞ አጋዥ መረጃ አቀባዮች ናቸው፡፡ እነዚህን መረጃ አቀባዮች የመረጥኩት ታላሚ ናሙናን (purposive sampling) በመጠቀም ነው፡፡ መረጃ አቀባዮቹ የለቅሶ ስርአቱን፣ የሚያውቁና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ናቸው፡፡ እነሱም የጎሳ መሪ፣ የእድሜ ባለጸጎች፣ በብሄረሰቡ ባህል ዙርያ ያጠኑ የብሄረሰቡ ተወላጆችና ጋዜጠኞች፣ የቤት እመቤቶች እና በለቅሶ ስርዓት ላይ ከፍተኛ ሚና ያላቸው ( ደንብ ሰሪ፣ ሙሾ ደርዳሪ እና አንጀት አንባቢዎች) ናቸው፡፡ ቃለ

መጠይቁ የተኪያሄደው በአማርኛ ቋንቋ እና በዲዚኛ ቋንቋ ሲሆን 60 ደቂቃ የሚያዙ 5 መቅረጸ ደምጾችን ለመረጃነት ተጠቅሜያለሁ፡፡

ቃለ መጠይቁን በማደርግበት ወቅት ዋንኛነት መቅረጸ ድምጽ የተጠቀምኩ ሲሆን መረጃው የተሰበሰበበት ቦታም በለቅሶ ቤት፣ በቀብር አካባቢ፣ በመኖርያ ቤት፣ በቢሮ ውስጥ እንዲሁም በሻይ እና ቡና ቤቶች ውስጥ ነው፡፡

#### 1.7.1.3 ተተኳሪ የቡድን ውይይት

በዚህ ጥናት አንድ የተተኳሪ ቡድን ውይይት አኪያሄጃለሁ፡፡ ይህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተጠቀምኩት በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ወቅት ያልተገኙ መረጃዎች ሲኖሩ እና የተለየ መረጃ እንደማገኝ እርግጠኛ የሆንኩባቸውን ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ነው፡፡ በቡድን ማዋቀሩ ወቅት የተለያዩ የማህበረሰቡን አካላት ያሳተፍኩ ሲሆን የቡድኑ አባላትም ሶስት የእድሜ ባለፀጎች ፣ ሁለት ታሪኩንና ባህሉን የሚያውቁ የብሔረሰቡ አባላት፣ አንድ የጎሳ መሪ፣ አንድ የሙገሳና የሙሾ ግጥም ደርዳሪ ፣ አንድ የቀበሌ ሊቀመንበር እና አንድ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ከፍተኛ ሚና ያለው ሰው( ደንብ ሰሪ) ናቸው፡፡ በመሆኑም ዘጠኝ ሰዎችን የያዘ የቡድን ውይይት የተካሄደ ሲሆን ዘጠኝ ሰዎችን የመረጥኩበት ምክንያት አንድም በጎዶሎ ቁጥር መቀመጡ በውይይቱ የሚገኙ መረጃዎች ወገናዊ ለማድረግ ሁለትም፣ Kruegor (1994፡79) ተተኳሪ የቡድን ው ይይት ለማድረግ አባላቱ ከ8-10 ቢሆኑ የተሻለ እንደሚሆን በገለጹት መሰረት ነው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በቀረቡት መንገዶች የተሰበሰቡት መረጃዎች በገላጭ ዘዴ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

### 1.7.2 የመረጃ አተናተን

ከላይ በቀረቡት የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች መረጃዎችን እያደጋገፍኩና እያስማማሁ ለመጠቀም ሞክሬአለሁ፡፡ የአንደኛውን የመረጃ መሰብሰቢያ መንገድ ክፍተት በሌላኛው በሟሟላት የተሟላ መረጃ ለማግኘት ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ መረጃዎቹ በሚሰበሰቡበት ወቅትም ሆነ ከተሰበሰቡ በኋላ የእያንዳንዱ ክዋኔ ትዕምርትም ሆነ ትርጉም ከክዋኔው እና ከባህሉ ጋር ለማገናኘት ሞክሬያለሁ፡፡ የክዋኔዎች ትዕምርቶች ከከዋኔው የመነጩ ናቸው፡፡ የጥናቱ ዘዴ ገላጭ እንደመሆኑ መጠን መረጃዎችን በአይነታቸው በመመደብ በቅደም ተከተል ለመግለጽ ሞክሬያለሁ፡፡ በተጨማሪም መረጃው የክዋኔ ንድፈ ሃሳብ የሚጠራ ትንተናው በክዋኔ ንድፈ ሃሳብ የተቃኘ ነው፡፡

ትርጉም የሚያስፈልጋቸውን መረጃዎች ከሶስት የብሄረሰቡ ተወላጆች ጋር በመሆን የትርጉም ስራው ተከናውኗል፡፡

## 1.8 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

ይህን ጥናት በማጠናበት እና መረጃዎች በሚሰበሰብበት ጊዜ የተለያዩ ችግሮች ገጥመውኛል፡፡ ከእነዚህም ችግሮች መካከል የመጀመሪያው በብሄረሰቡ የሚገኙ ሁሉንም የለቅሶ አይነቶች በተፈጥሯዊ መቼት ማግኘት አለመቻል ነው፡፡ በተፈጥሮአዊ መቼቶች ላይ በመገኘት መረጃዎችን በምሰበስብበት ጊዜ ከክዋኔው መጀመሪያ እስከ ፍፃሜ ድረስ ያለውን ዝግጅት ሙሉ በሙሉ ለመመልከት አለመቻሌ ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ ደግሞ ባህሉ አለመፍቀዱ እና መረጃውን በተፈጥሮአዊ መቼት እንዳልሰበስብ አንዳንድ የብሄረሰቡ አባላት መከልከላቸው ነው፡፡ እነዚህ ችግሮችን በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት እንዲሁም በተለያዩ ጊዜያት የተቀረጹ ቪዲዮዎችን በመመልከት ለማቃለል ችያለሁ፡፡

በጥናቱ ወቅት ሌላው ያጋጠመኝ ችግር የገንዘብ እጥረት ነው፡፡ በተፈጥሮአዊ መቼት ላይ በመገኘት መረጃዎችን ለመሰብሰብና ክዋኔዎችን ለመቅረፅ የሚጠየቀው ብር ከፍተኛ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አንዳንድ መረጃ አቀባዮችን ቃለ መጠይቅ በማደርግበት ጊዜ የሚጠይቁኝ የገንዘብ መጠን ከፍ ያለ በመሆኑ ችግሩን ከበድ አድርጎታል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ አንዳንድ መረጃ አቀባዮች ያለምንም ክፍያ መረጃዎችን ለመስጠት ፍቃደኛ በመሆናቸው ችግሩን በመጠኑ ለመቀነስ ሞክሬያለሁ፡፡

እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው በጥናቱ ጊዜ ያጋጠሙ ዋና ችግሮች ይሁኑ እንጂ ሌሎች (የቋንቋ፣ የመጓጓዣ እጥረት፣ እና ለባህሉ እንግዳ መሆን፣ ወዘተ) የገጠሙኝ ተጨማሪ ችግሮች ነበሩ፡፡

## 1.9 የመስክ ተሞክሮ

ጥናቱ ከተጀመረበት ጊዜ እንስቶ ወደ መስክ እስከምሄድ ድረስ ጥናቱ የሚካሄድበትን አካባቢ የተመለከቱ መረጃዎችን ከቤተ መጻሕፍት እና በተለያዩ አጥኚዎች የተሰሩ ስራዎችን ተመልክቻለሁ፡፡ ከቤተ መጻሕፍት ከተገኙ የመረጃ ምንጮች መካከል መጽሐፎች፣ መጽሄቶች ጆርናሎች እንዲሁም የምርምር ስራዎች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህን ጽሁፎች በማንበብ በቂ መረጃ ሰብስቢያለሁ፡፡ ወደ መስክ ከመሄዴ በፊት ለመስክ ስራው የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን መቅረጸ ድምፅ፣ ካሴት፣ ቪዲዮ ካሜራ፣ ፎቶ ካሜራ፣ እና ማስታወሻ ደብተሮችን አዘጋጀሁ፡፡

ቅድመ ዝግጅቶች ከተጠናቀቁ በኋላ በ30/05/06 ዓ.ም ጉዞ ወደ ማጂ ጀመርኩ፡፡ በመጀመርያ ከአዲስ አበባ 561 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ወደምትገኘው የቤንች ማጂ ዞን ዋና ከተማ (ሚዛን) ጉዞ አደረኩ፡፡ የደረስኩትም በሁለተኛው ቀን ከቀኑ 7፡15 አካባቢ ነው ፡፡ በማግስቱ በ02/06/02 ወደ ቤንች ማጂ ዞን ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ በመሄድ በትምህርት ክፍሉ የተፃፈልኝን የድጋፍ ደብዳቤ በማቅረብ ወደ ማጂ ወረዳ መሄድ እንደምፈልግ ተናግሬ የድጋፍ ደብዳቤ እንዲጻፍልኝ ጠየቅኩ፡፡ ነገር ግን ይህን ደብዳቤ ለማግኘት አራት ቀናትን መጠበቅ ግድ ሆነብኝ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ የቢሮው ሃላፊ በስብሰባ ምክንያት ወደ ክልሉ ርዕሰ ከተማ ሃዋሳ በመሄዳቸው ነው፡፡

በዚህ ወቅት ከአንዳንድ ሰዎች ጋር ትውውቅ በማድረግ እና በቢሮው ውስጥ የሚገኙ ጥናታዊ ጽሁፎችን በማንበብ ቆየሁ፡፡ ከሳምንት ቆይታ በኋላ በ 09/06/06 በዞኑ ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ የተፃፈልኝን ደብዳቤ በመያዝ ወደ ማጂ ወረዳ መቀመጫ ከተማ ወደ ቱም ሄድኩ፡፡ በቦታው እንደደረስኩም የተፃፈልኝን ደብዳቤ ለወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በማቅረብ አስፈላጊውን ትብብራቸውን እንዲሰጡኝ ጠየኩ፡፡ የቢሮው ሐላፊና የህዝብ ግንኙነት ባለሙያው ስለ ብሄረሰቡ በመጽሃፍ መልክ የተጻፉ እንዲሁም የቪዲዮ ምስሎችን እና የተለያዩ ቁሳዊ ባህሎችን እንድመለከት አድርገዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መረጃ ለመሰብሰብ ወደ ገጠሩ አካባቢ በምሄድበት ጊዜ አቶ ዘለቀ ገሩ የተባሉ ሽማግሌና የቀበሌ ሊቀመንበር አብረውኝ እንዲሄዱ ያደረጉልኝ ሲሆን ወደ ተለያዩ ቀበሌዎች በምሄድበት ጊዜ በመንገድ መሪነት እና በአስተርጓሚነት ሊሰሩና የቀን የውሎ አበል 70 ብር ልከፍላቸው ተስማምተን በማግስቱ ለመገናኘት ቀጠሮ ይዘን ተለያየን፡፡

በ10/06/06 ዓ.ም ወደ ማጂ ለመሄድ ስነሳ እዛው ያለሁበት አካባቢ የለቅሶ ድምጽ ሰማሁ፡፡ ከሌሊቱ አስር ሰዓት ገደማ ይሆናል፡፡ የለቅሶው ቤት እኔ ካረፍኩበት ቦታ የራቀ ባለመሆኑ ሁኔታውን ሄጄ ለመከታተል ወሰንኩ፡፡ ቀረብ ብዬም ጠየቅሁ፡፡ በለቅሶው ቤት አስከሬን እንደሌለና አስከሬን ለመቀበል እየተዘጋጁ መሆናቸውን ተነገረኝ፡፡ በለቅሶ ቤቱ ውስጥ ያለችን አንዲት ልጅ ( ዕድሜዋ በግምት 15 ዓመት ይሆናል) ማን እንደሞተ እና አስከሬኑ ከየት እንደሚመጣ ጠየቅኳት፡፡ ሟች በሚዛን ከተማ ተማሪ ስትሆን እድሜዋ 17 እንደሆነና በድንገተኛ ህመም ምክንያት እንደሞተች አስከሬኑም ከሚዛን ከተማ እየመጣ እንደሆነ ገለጸችልኝ፡፡ በለቅሶ ቤቱ ውስጥ የሚደረጉ ክዋኔዎችን እየተመለከትኩ አስከሬኑን መጠበቅ ጀመርኩ፡፡ የለቅሶ ስርዓቱን በአጠቃላይ ተከታትዬ በሶስተኛው ቀን ወደ ማጂ ለመሄድ ተነሳሁ፡፡ ለባህልና ቱሪዝም ሃላፊው ማጂ ከተማ ውስጥ ያሉ

ሽማግሌዎችን ማግኘት እንድችል በስልክ እንደሚያሳውቅልኝ ከነገረኝ በኋላ የለቅሶ ስርዓት በሚኖርበት ጊዜ እንዲደውልልኝ በማሳሰብ ጉዞ ጀመርኩ፡፡

ማጂ ከገባሁ በኋላ ከተማውን እና ቅርብ ቀበሌዎችን ጎበኘሁ፡፡ በማግስቱም ጠዋት 3:00 ላይ ከአቶ ዘለቀ ገሩ ጋር ተገናኘን፡፡ እንደአጋጣሚ ከሁለት ቀን በፊት አንድ በእድሜ የገፉ አዛውንት የሞቱበት ቤት ስለነበር ወደ ቤቱ ለመሄድ ወሰንኩ፡፡ ከዚያም በለቅሶ ቤቱ ውስጥ የሚገኙ ሽማግሌዎችን ቃለ መጠይቅ አደረግሁ፡፡ በቃለ መጠይቁ ወቅት በድምጽም ሆነ በምስል መረጃዎችን እንዳልወስድ ነገሩኝ፡፡ ቱም በነበርኩበት ወቅት በለቅሶ ክዋኔ ጊዜ የተመለከትኳቸውን ክዋኔዎች መሰረት በማድረግ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት እና ቃለ መጠይቅ በማድረግ የተለያዩ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ቻልኩ፡፡ ሰዎችን በቃለ መጠይቅ በማድረግ እንዲሁም ለቡድን ውይይት ከሚመቻቸው ሰዎች ጋር ቀጠሮ በማስተካከል አንድ ሳምንት አሳለፍኩ፡፡

በ19/06/06 ዘጠኝ ሰዎችን የያዘ ቡድን ውይይት አደረግሁ፡፡ የቡድን ውይይቱን ማኪያሄዱ ቀላል አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ሰዎቹ ለመወያየት ፍቃደኛ ያለመሆናቸው እና እከሌ እያለ እኔ አልናገርም በሚል ስሜት የተወሰኑ ሰዎች ሃሳብ ብቻ የሚቀርብበት ሁኔታ ነበር፡፡

ከዚህ በኋላ በ20/06/06 ዓ.ም ወደ ቱም ከተማ በመሄድ በተለያዩ ቦታዎች በመዘዋወር እና ስለ ባህሉ ጥሩ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፤ የተባልኳቸውን ሰዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃዎችን ሰበሰብኩ፡፡ በ 22/06/06 ወደ ሚዛን ከተማ ተመለስኩ፡፡

ከሁለት ሳምንት በኋላ አንድ ባላባት መሞቱን ተደውሎ ተነገረኝ፡፡ ባላባቱ ከሞቱ አራት ቀናት ያለፉ መሆናቸውንና እስከ ስምንት ቀን ድረስ እንደሚቆይ ነገሩኝና በ4/07/06 ጉዞ ጀመርኩ፡፡ የሟች ቤተሰቦች ዝግጅት እያዘጋጁ መሆኑን በመስማት ወደ ቦታው ሄድኩ፡፡ መጨረሻም እስከ ክዋኔው መጨረሻ በመቆየት መረጃዎችን ሰበሰብኩ፡፡ በማግስቱም በአካባቢው ከሚገኙ ሽማግሌዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት በመፍጠር የምፈልገውን መረጃ ለመሰብሰብ ቻልኩ፡፡ ቱም በሚገኘው ወረዳው ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ የተቀረጹ ቪዲዮ ፊልሞችና ቁሳዊ ባህሎችን በድጋሚ በመመልከት የትርጉም ስራዎችን ለመስራት ወደ ሚዛን ተመለስኩ፡፡ የትርጉም ስራውን እና ሌላ ለቅሶ ካለ እንዲደውሉልኝ በማድረግ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ፡፡

በ28/08/06 ዓ.ም ለዳግም ምልከታና የትርጉም ስራዎችን ለመጨረስ ወደ ሚዛን ተመለስኩ፡፡ ሚዛን በነበርኩበት ወቅት ማለትም በ 01/09/06 ዓ.ም አንድ መረጃ አቀባዬ የነበሩት አቶ ባልኩ ኩሙ የተባሉ አዛውንት (ዕድሜያቸው 88 ነው) መሞታቸው ተነገረኝ፡፡ በሳቸው የለቅሶ ስርዓት ላይ በመገኘት ተጨማሪ መረጃዎችን መሰብሰብ ችያለሁ፡፡ መረጃዎቼን በትክክል መጠናቀራቸውን ካረጋገጥኩ እና የትርጉም ስራዎች በትክክል ወደ አማርኛ መተርጎማቸውን በሌሎች ተጨማሪ ጋዜጠኞች ካረጋረጥኩ በኋላ 10/09/06 ዓ.ም ተነስቼ ወደ አዲስ አበባ መጣሁ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፡ ክለሳ ድርሳን

በዚህ ክፍል ሶስት አበይት ጉዳዮች ተተኩሮባቸዋል፡፡ እነሱም የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት፣ ጽንሰ ሃሳባዊ ዳራና ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ የሚሉ ናቸው፡፡ መጀመሪያ ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው ጥናቶች እና ስለ ለቅሶ ስርዓት የተፃፉ የተለያዩ ጽሁፎች የተቃኙበት ክፍል ነው፡፡

## 2.1 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርዕስ ስር ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው የኤም ኤ ዲግሪ ጥናቶች እና ስለ ለቅሶ ስርዓት ዙሪያ የተጻፉ ጽሁፎች የሚዳሰሱበት ነው፡፡ በዳሰሳው ጥናቶቹና የጽሁፎቹ አላማ ምን እንደሆነ እና ምንምን ነጥቦች ላይ እንደሚያተኩሩ እመለከታለሁ፡፡

በዚህ ክፍል የሚቃኙት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ በለቅሶ ስርዓተ ክዋኔና ላይ ያተኮሩ ጥናታዊ ጽሁፎችና በ (Ethnological Society Bulletin) ውስጥ በተለያዩ ምሁራን የተጻፉ የለቅሶ ስነ ስርዓቶች ላይ ያተኮሩ ጽሁፎች ናቸው፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ትኩረታቸውን በለቅሶ ስርዓተ ክዋኔና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ያደረጉ ስድስት የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሁፎችን ቃኝቻለሁ፡፡ ጥናታዊ ጽሁፎቹ በቀረቡበት ዘመን ቅደም ተከተል የቀረቡ ሲሆን በአንድ ዘመን የተገኙት ጥናቶች ደግሞ በአጥኚዎቹ ስም ፊደል ተራ ቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

ሞገስ ሚካኤል በ2002 ዓ.ም "በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ስነ ስርዓት፣ በስርዓቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔ" በሚል ርዕስ ጥናት አድርጓል፡፡ የጥናቱ አቢይ ትኩረት በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የለቅሶ ስነ ስርዓትና በስርኣቱ ላይ የሚካሄዱ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔ ላይ ገላጭ ትንተና ማድረግ ነው፡፡ በጀግና የቀብር ስነ ስርዓት ላይ የሚደረገውን የቀረርቶና የፉከራ ክዋኔ በቪዲዮ በመቅረጽ ፣በቴፕ በመቅዳት፣ ፎቶግራፍ በማንሳት እና ጥናቱን በጽሁፍ በማዘጋጀት እንዲቀረስ ማድረግ ነው፡፡

አጥኚው ተፈጥሯዊ መቼት ላይ በመገኘት በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ መረጃውን ሰብስቧል፡፡ ተዛማጅ ጥናቶችን የቃኘው "የለቅሶ ስርዓቱን እና ሙሾን ያጠኑ፣

የለቅሶ ስርዓቱን ብቻ ያጠኑ እና ቀረርቶንና ፉከራን ያጠኑ" ብሎ በመመደብ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከቀብር ስነ ስርዓት፣ ከቀረርቶ፣ ከፉከራና ከክዋኔ ጋር የተያያዙ ንድፈ ሃሳቦችን ቃኝቷል፡፡

በጥናቱ ውስጥ የቅድመ ሞት ዝግጅት፣ የኑዛዜ ስርዓት አፈጻጸም፣ ለዋናው ለቅሶና ለለቀስተኛ ማስተናገጃ የሚደረጉ ዝግጅቶች፣ ግንዘት፣ ጊዜ ሞት እና ከቀብር በኂላ የሚከናወኑ ስርዓቶችን በላይ አርማጭሆ አካባቢ ምን እንደሚመስሉ በትንታኔው ክፍል አሳይቷል፡፡ በማጠቃለያውም የገለጸው በለቅሶ ስርዓቱ ሃይማኖታዊና ልማዳዊ ስነ ስርዓቶች በአንድነት የሚከወኑ መሆናቸውን ነው፡፡ የቀረርቶና የፉከራ ክዋኔዎች በማህበረሰቡ ውስጥ የፖለቲካ፣ የሃይማኖት፣ የማህበራዊ ደረጃ እንዲሁም ከኢኮኖሚ ጋር ተያይዘው እንደሚነሱ እና በማህበረሰቡ ዘንድ የሚታዩ የአመለካከት ልዩነቶች የሚያንጸባርቁ እንደሆኑ ጥናቱ ያመላክታል፡፡ ይሁን እንጂ ጥናቱ በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ስነ ስርዓት የሚል ሲሆን አጥኚው ያተኮረው በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ በሚከወነው የለቅሶ ስርዓት ላይ ነው፡፡ ይህም ከዚህ እምነት ውጪ ያሉትን አለማካተቱ የጥናቱ ድክመት ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

ሁለተኛው ጥናት ህይወት አበሩ በ2003 ዓ.ም "የመኢኔት ብሄረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ" በሚል ርዕስ ያቀረበችው ነው፡፡ የህይወት ጥናት አላማ የመኢኔት ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔን ማሳየት ነው፡፡ ጥናቱ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔውን ከመግለጽ በተጨማሪ በስርዓቱ ላይ የሚቀርቡ ትዕይንቶችን ትርጉምና ተግባር ይገልጻል፡፡

ጥናቱ የመስክ ምርምርን መሰረት አድርጎ የተኪያሄደ ሲሆን መረጃዎቹ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ፣ እንዲሁም በቡድን ውይይት የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ መረጃዎቹም ስለ ባህሉ እውቀት አላቸው ከተባሉ አዛውንቶች፣ ከሃይማኖት መሬዎች፣ ከጎሳ መሪዎች፣ ከቤት እመቤቶችና ከባህልና ማስታወቂያ ቢሮ ሃላፊዎች የተገኙ ናቸው፡፡ ጥናቱ በሁለት ማህበራዊ ደረጃና በአሟሟት ሁኔታ ተከፍሎ፣ በቀብር ስርዓት አፈጻጸም፣ በግንዘት፣ በቀብር ቦታ መረጣ እና በስርዓቱ ላይ የሚከወኑ ድርጊቶች አንጻር ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ እነዚህም ስርዓቶች የሞተውን ሰው ማህበራዊ ደረጃ የሚገልጹና በማህበረሰቡ ዘንድ የሚሰጠውን ከበሬታ የሚያሳዩ መሆናቸውን ጥናቱ አመላክቷል፡፡

በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚከወኑትን ድርጊቶች ከማሳየት በተጨማሪ የስርዓቱን ማህበራዊ ፋይዳ እና ተግባራት አጥኚዋ ገልጻለች፡፡ ስርዓቱ ለብሄረሰቡ ታሪክን ከማቆየት

አንጻር ያለው ፋይዳ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ተቋማትን ከማስጠበቅ አንጻር ያለው ፋይዳ፣ የማህበረሰቡን አመለካከት፣ እምነት ከመግለጽ አንጻር እንዲሁም የለቅሶ ስርዓቱን ለትውልድ ለማስተላለፍ የሚያደርገው የማህበረሰቡ ትጋት ምን እንደሚመስል መፈተሽ በጥናቱ የተተኮረባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

በስርዓተ ከዋኔው ትንተናም በዕድሜ ከህጻንነት እስከ አቅመ አዳም/ሄዋን ለደረሱ እና ለዕድሜ ባለጸጋዎች፣ በስልጣን ለባለቃልቻዎች እና ለጎሳ መሪዎች እንዲሁም ከአሟሟት ሁኔታ አንጻር በሰው ለተገደለ የሚደረጉ ስርዓቶችን ከቅድመ ሞት እስከ ድህረ ሞት ያለውን ክዋኔ አቅርባለች፡፡ በተለይ ጥናቱ የሚያተኩረው የ"ኤይሬን" ባህላዊ እምነት ተከታዮች ላይ ነው፡፡ አጥኚዋም በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ የሌላ ሀይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ለምን አላሳየችም? የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ በተጨማሪም በክዋኔው ወቅት የሚታዩ ስነ ቃሎችን ጥናቱ አለማካተቱ ጉድለት ነው፡፡

በ2004 ዓ.ም በዘላለም ፋንቱ "የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ በበና ጸማይ ወረዳ" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርቧል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት በበና ብሄረሰብ ዘንድ የሚደረገውን የለቅሶ ስነ ስርዓት ክዋኔ ማሳየት ሲሆን ሁለት አበይት አላማዎች አሉት፡፡ እነሱም የበና ብሄረሰብ የለቅሶ ስነ ስርዓት ክዋኔ ምን እንደሚመስል ማሳየት እና ከእያንዳንዱ የለቅሶ ስነ ስርዓት ክዋኔ ጀርባ ያለውን ትርጉም መግለጽ ናቸው፡፡ መረጃውንም የሰበሰበው ተፈጥሮአዊ መቼትን በመጠቀም ዳር ቆሞ በመመልከት፣ የተተኳሪ የቡድን ውይይት በማኪያሄድ እንዲሁም ታላሚ ናሙና አመራራጥን በመጠቀም 21 ሰዎችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ ነው፡፡

በጥናቱ ውስጥ ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ጥናቱን ለማጠናከር የተለያዩ ንድፈ ሃሳቦችን እና ከጥናቱ ጋር የሚነሱ ጉዳዮችን (ሞት፣ ለቅሶ፣ ክብረ በዓል፣ ክዋኔ እንዲሁም የክዋኔ አላባውያን) የንድፈ ሃሳብ ቅኝት አካሂዷል፡፡ በትንታኔው ክፍልም ቅድመ ሞት ዝግጅትን፣ ሞት መቅረቡን ማረጋገጫ ብልሃቶችን፣ ኑዛዜ፣ ለለቅሶው ማስኬጃና ለለቀስተኛ ማስተናገጃ የማደረጉ ዝግጅቶች፣ በሞት እንዲሁም በድህረ ሞት የሚደረጉ ስነ ስርዓቶችን ዘርዝሯል፡፡

በአጠቃላይ ጥናቱ በደረሰበት ድምዳሜ በለቅሶ ስርዓተ ክዋኔው ውስጥ የሚተላለፈው መልዕክት የማህበረሰቡን አመጣጥ፣ አሰፋፈር፣ አኗኗር እና ለህይወት ያለውን አመለካከት የሚያሳይ መሆኑን ገልጿል፡፡

ማናዬ እንግዳ ወርቅ በ 2005 ዓ.ም "በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ንጽጽራዊ ጥናት" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርቧል፡፡

የጥናቱ አላማ በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔን በንጽጽር ማሳየት ነው፡፡ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን የሰበሰበው በተፈጥሯዊ አውድ ላይ በመገኘት በተሳትፏዊ ምልከታ እንዲሁም 22 ሰዎችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ ነው፡፡

በትንታኔው በሁለቱም የሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የሚደረገውን የቅድመ ሞት ክዋኔ፣ የጊዜ ሞት ክዋኔ እንዲሁም ድህረ ሞት ክዋኔ በዘርዝር አሳይቷል፡፡ በተጨማሪም በስርዓቶች ላይ የታዩ አንድነቶችና ልዩነቶችን አመልክቷል፡፡ በማጠቃለያው ክፍል በሁለቱ የሃይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነ ስርዓት ላይ የሚታዩት ልዩነቶች ከቅድመ ሞት እስከ ድህረ ሞት ድረስ ባሉት ክዋኔዎች ላይ መሆናቸውን ገልጿል፡፡

አየሁሽ ቶማ በ 2005 ዓ.ም "የወላይታ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርባለች፡፡ የጥናቱ አላማ የወላይታ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ያለውን ገጽታ በመግለጽ ለትዕምርታዊ ጉዳዮች ማህበረሰቡ የሚሰጠውን ባህላዊ ፍቺ መመርመር ነው፡፡ ይህንኑ አላማ ከግብ ለማድረስ ከዞኑ ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል በአንድ ቀበሌ ውስጥ ከአንድ የዕድሜ ባለጸጋ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ላይ በመገኘት እና ምልከታ በማድረግ መረጃ ሰብስባለች፡፡ በተጨማሪም 12 ሰዎችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ እንዲሁም የተተኳሪ የቡድን ውይይት በማከናወን እና መረጃ በመሰብሰብ በገላጭ የትንተና ዘዴ ቀርቧል፡፡

ግኝቱም ማህበረሰቡ በባህላዊ የለቅሶ ግጥሞች ሞትን መናቁ፣ በሞት ህይወትን ማስታወሱ፣ ሟች በአካል እንጂ በመንፈስ እንደማይሞት መታሰቡ፣ ለቅሶ የማህበራዊ ትስስር መፍጠርያ ወይም ማፍረሻ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑ እንዲሁም በነባሩ የለቅሶ ስርዓት ውስጥ በርካታ ለውጦች መደረጋቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በመጨረሻም የለቅሶ ቃል ግጥሞቹ ተሰብስበው ቢጠኑ ከመሰነድም ባለፈ የህብረተሰቡን ማንነት እና አመለካከት የበለጠ ለመረዳት የሚያስችሉ መሆናቸው ጠቁማለች፡፡

ጥናቱ ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ ሲሆን በሰፊው የትዕምርቶች ትርጉም ይታያል፡፡ ለዚህ ደግሞ የአካባቢው ተወላጅ መሆኗ እንዲሁም ቋንቋና ባህሉን ማወቋ ጠቅሟታል ብዬ አስባለሁ፡፡ በአባሪነት የተቀመጡት በርካታ ቃል ግጥሞች በይዘት በመከፋፈል

የተወሰኑትን ከክዋኔው ጋር ይበልጥ አቆራኝታ አለመግላጿ እንደ ድክመት የሚታይ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ቃል ግጥሞቹ ከተዘረዘሩት ክዋኔዎች ጋር ተጣምረው ቢቀርቡ ኖሮ ስራው ይበልጥ የተዋጣለት ይሆን ነበር፡፡ የወላይታ ብሄረሰብ ከሚኖርባቸው አካባቢዎች ከየትኛው ክፍል (ስንት ቀበሌ/ዎች) መረጃዎቹን እንደሰበሰበች አልገለጸችም፡፡

ቅኝት የተደረገበት ሌላው ጥናት ውቤ ታደገ በ2005 ዓ፣ም "የቤንች ብሄረሰብ የለቅሶ ሥርዓተ ከዋኔ" በሚል ርዕስ ያቀረበው ነው፡፡ የጥናቱ አላማ የቤንች ብሄረሰብን የለቅሶ ስርአተ ክዋኔ መግለፅ ነው፡፡ ጥናቱም የቤንች ብሄረሰብ የለቅሶ ሥርዓተ ከዋኔን ከቃል ግጥሞቹ ጋር በማያያዝ ተንትኗል፡፡ ጥናቱ የክዋኔ ንድፈ ሃሳብን የተከተለ ሲሆን ክዋኔ ተኮር ዘዴን ተጠቅሟል፡፡

ለጥናቱ ተፈጥሯዊ መቼት ላይ በመገኘት መረጃ የሰበሰበ ሲሆን መረጃውንም ለመሰብሰብ ምልከታን፣ ቃለ መጠይቅን እና ተተኳሪ የቡድን ውይይትን አገልግሎት ላይ አውሏል፡፡ በሦስት ተፈጥሮአዊ መቼቶች ላይ በመገኘት መረጃዎችን ሠብስቧል፡፡
ምልከታውም ኢተሳትፏዊ ምልከታ ሲሆን ያልተደገበ የተሰኘውን የምልከታ ቴክኒክ ተጠቅሟል፡፡ 21 የሚሆኑ ሰዎችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃዎችን የሰበሰበ ሲሆን 8 ሰዎችን የያዘ የቡድን ውይይትም አካሂዷል፡፡

ከመረጃዎቹም በመነሳት የቤንች ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ከሟቾቹ ማህበራዊ ደረጃ፣ ጾታ እና እድሜ አንጻር አምስት አይነት የለቅሶ ስርዓት እንዳላቸው ገልጿል፡፡ እነዚህን የለቅሶ ስርዓት አይነቶችም "የባለቃልቻዎች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ"፣ "የባላባትና የሚያንግ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ"፣ "የዕድሜ ባለጸጎች የለቅሶ ስርዓተ ከዋኔ"፣ "የወጣቶች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ" እና "የህጻናት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ" በማለት የገለጸ ሲሆን የቤንች ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓትን ከቅድመ ቀብር እስከ ድህረ ቀብር ክዋኔ ድረስ በዝርዝር ገልጿል፡፡

በትንታኔው ክፍል በእያንዳንዱ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ውስጥ የሚተላለፉ መልዕክቶችን እና የመልዕክቶቹን ይዘት አሳይቷል፡፡ የለቅሶ ስርዓቱም የሟችን ስራ ለምሳሌ፡- የዕምነት መሪ፣ የአካባቢ አስተዳዳሪ፣ የሃገር ሽማግሌ ቢሆኑ ከስራቸው በተጨማሪ ስለ ማንነታቸው እና ተግባራቸው የሚያወሱ ስርዓቶች እንደሚከናወኑላቸው ገልጿል፡፡ በክዋኔው ወቅት የሚደረደሩ ቃል ግጥሞችንም ተንትኗል፡፡

የጥናቱ ግኝትም የብሄረሰቡ የለቅሶ ስርዓቶች የታሪክን ተሳታፊነት የሚያጸኑ፣ የብሄረሰቡን ቋሚ የሆነ የስልጣን ሽግግር የሚያበስሩ፣ የብሄረሰቡን የጎሳ የዘር ግንድ

መሰረት የሚገልጹ እንዲሁም የብሄረሰቡን ሃገረሰባዊ እምነት የሚያስጠብቁ መሆናቸውን አመላክቷል፡፡

በአጠቃላይ የውቤ ታደገ ጥናት ጠንካራ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ጥናቱ በማህበረሰቡ የለቅሶ ስርዓት ላይ የሚታዩ ቁሳዊ ባህሎችን፣ ስነ ቃሎችን፣ በስርዓቱ ላይ የሚታዩ ትዕምርቶችን ትርጉም መስጠቱና ስርዓቱን ለማሳየት ሶስቱን ተገቢ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች መጠቀሙ ጠንካራ ጎኑ ነው፡

ከዚህ በመቀጠል የሚቀርቡት ቅኝቶች በ "Ethnological Society Bulletin" (2002) በአማራ፣ በትግራይ እና በሀረር ክልል የሚከወኑ የለቅሶ ስነ ስርዓቶች ላይ ትኩረት ያደረጉ ጽሁፎች ናቸው፡፡ እነዚህ ጽሁፎች በተለያዩ ሰሚናሮች ላይ የቀረቡ ናቸው፡፡

ፋሲካ በለጠ ያቀረበው ጥናት *"The Death Custom among the Amharas of Sawa"* በሚል ርዕስ ሲሆን ትኩረቱ በዋናነት በአማራ ክልል በሸዋ አካባቢ የሚገኙ የክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚከወነውን የቀብር እና የሃዘን መግለጫ ስነ ስርዓት መግለጽ ነው፡፡ መረጃው የተሰበሰበው በአካባቢው የሚገኙ ሽማግሌዎችን በመጠየቅ ነው፡፡

የለቅሶ ስርዓቱ በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች ቀርቧል፡፡ በጥናቱም አንድ ሰው በቅርብ ይሞታል ተብሎ ከተገመተ የኑዛዜ ስርዓት እንደሚፈጸምለት፣ ይህን ስርዓት ለማስፈጸምም የሟች ነፍስ አባትና በአካባቢው የሚገኙ ሽማግሌዎች ግንባር ቀደም ተጠሪዎች እንደሆኑ ገልጿል፡፡ የሟች ህልፈተ ህይወት ከተረጋገጠ በኂላ ለወዳጅ፣ ለዘመድ አዝማድ፣ ለጎረቤቶች የሚነገርበትን ሁኔታ የገለጸ ሲሆን መርዶው በስሚ ስሚ (በቅብብሎሽ)፣ በእግር ጉዞ በመሄድ እንዲሁም ራቅ ወዳሉ ቦታዎች ደግሞ በፈረስ በመሄድ እንደሚነገር ተገልጿል፡፡ የግንዘት ስርዓቱም ለቀሳውስት፣ ለመነኮሳት እና ለሌሎች የሚደረገው የተለየ እንደሆነ ጽሁፉ ያስረዳል፡፡

ሟች ከመቀበሩ በፊት የሚደረጉ ሀይማኖታዊ ክዋኔዎች ያሉ ሲሆን እነሱም የፍታት፣ ጸሎት እና የመጽሃፍ ቅዱስ ጥቅስ ንባብ ናቸው፡፡ ሬሳው ወደ ቀብር ቦታ ሲሄድ በጉዞው ወቅት የሚኖረው ቅደም ተከተል በቅድሚያ ካህናት እና የሟች ቤተሰቦች ከዚያም ጎረቤቶችና ዘመዶች ይከተላሉ በማለት ገልጿል፡፡

የቀብር ቦታውም ለቤተክርስቲያን አገልጋዮች እና በማህበረሰቡ ዘንድ ለሚከበሩ ሰዎች የተለያየ መሆኑን ገልጿል፡፡ በተጨማሪም ሟች ከሞተ በ3ኛ፣ በ7ኛ፣ በ12ኛ፣ በ40ኛ፣ በ80ኛ ቀኖች፣ በ6ኛ ወር እና በ1ኛ አመት ላይ እንደሚለቀስ ፅሁፉ ያመለክታል፡፡

ጥናቱ በሸዋ አካባቢ የሚከወኑ የለቅሶ ልማዶች መግለጽ ላይ ቢያተኩርም ለየትኛው የማህበረሰብ ክፍል እና ወረዳ እንደሆነ በግልጽ የሚጠቅሰው ነገር የለም፡፡ በተጨማሪ በርካታ ትርጉም የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች በቂ ገለጻ አልተደረገባቸውም፡፡ ምክንያቱም እንዳንዶቹ ለምን ይሆን? የሚሉ ጥያቄዎችን የሚያስነሱ ናቸው፡፡

አንዳርጋቸው ተስፋዬ *"Funeral Custom of the Kottu of Harar"* በሚል ርዕስ በቆቱ የእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚከወነውን የለቅሶ ስነ ስርዓት በተመለከተ የጻፈው ጽሁፍ በዚህ ጥናት የተዳሰሰ ነው፡፡ (በቆቱ ማህበረሰብ ላይ ማተኮሩ ከግርጌው ማስታወሻ ላይ የተገኘ ነው፡፡)

በጽሁፉ ውስጥ በቅድመ ሞት ጊዜ ሟች ለሞት መቃረቡን ከሌሎች ሰዎች ጋር በሚያደርው ንግግር ማወቅ እንደሚቻል ገልጿል፡፡ ሟች ከሞተ በኂላ ስርዓቱን ለማከናወን የሚደረጉ የጾታ እንዲሁም የስራ ክፍፍሎችን አሳይቷል፡፡ በቀብር ወቅት የቀብሩን ጉድጓድ በማን እና በምን መልኩ እንደሚቆፈር እንዲሁም በአቀባበር ሁኔታ ከጾታ አንጻር የወንድና የሴት ቀብር በማለት ገልጿል፡፡

በስርዓቱ ላይ በድህረ ቀብር ጊዜ ወንዶች ከፍተኛ የስራ ድርሻ እንዳላቸው የገለጸ ሲሆን እስከ ሰባት ቀን ድረስም ያጽናናሉ፡፡ በዚህ ወቅት ያልተሳተፈ ሰው አንድ በሬ ይቀጣል፡፡ የለቅሶ ስርዓቱም ሰባት ቀን እንደሚቆይ ጥናቱ የሚያመለክት ነው፡፡ የሀረሪ ብሄረሰብ የቆቱ የእስልምና ተከታዮች የሚከዉኑትን የለቅሶ ስርዓት ያቀረበ ሲሆን ለአንዳንድ ክዋኔዎች ግን በቂ ዝርዝር አላቀረበም፡፡

አብደላ አብዱራህማን *"The Harari Funeral Customs "* በሚል ርዕስ በሁለት ክፍል ጽሁፍ አቅርቧል፡፡ ትኩረቱ በገላን እና አርባን አካባቢ የሚገኙ ሙስሊሞችን የለቅሶ ስርዓት መግለጽ ነው፡፡ በዚህ አካባቢ "አፎቻ" ወይም ዕድር መሰል ማህበር ያለውን ከፍተኛ ሚና የገለጸ ሲሆን ዕድር የሌለው ሰው ቀባሪ ሊያገኝ አይችልም በማለት ገልጿል፡፡ የቀብር ስርዓቱም በጾታ እና በማህበራዊ ደረጃ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ጠቁሟል፡፡ በዕድሜ ጠና ያሉ ሰዎች በግንዘት ወቅት ሬሳውን ማጠብ፣ ቅባት መቀባት፣ መገነዝ እና ልብስ ማልበስ የስራ ድርሻቸው እንደሆነ ተገልጿል፡፡

የአካባቢው ሰዎች በቀብር ጉዞ ወቅት ለሟች ያላቸውን ክብር ለመግለጽ በአብዛኛው ሬሳውን በመሸከም ይተጋገዛሉ፡፡ በዕለተ አርብ ለሞተ ሰው ከቀብር በፊት መስጊድ ወስደው ጸሎት ያደርጉለታል፡፡ ከቀብር በኋላ የሟች ቤተሰቦች "ከፋራ" ወይም ቂጣ ለለቅሶው ታዳሚዎች ያቀርባሉ፡፡ በተጨማሪም አቅማቸው በፈቀደው መልኩ በሬ ወይም ፍየል አርደው ድሆችን ሊያስተናግዱ ይችላሉ፡፡

ሟች ከተቀበረ ከአራት ቀን በኋላ የዕድሩ አባላት 25 ሳንቲም በማዋጣት የሚጸልዩ ሲሆን በስምንተኛው ቀን ደግሞ የሟች ቤተሰቦች በሬ አርደው የዕድሩን አባላትና የቅርብ ዘመዶችን በመጥራት ሟችን አስበው ይውላሉ፡፡ በዚህ ወቅት የተጠሩት ሰዎች የቻሉትን ገንዘብ ለሟች ቤተሰቦች ያበረክታሉ፡፡ ከዛም የስርዓቱ ፍጻሜ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ የአብደላ ጽሁፍ የለቅሶ ስርዓቱን ሟች ለሞት ከተቃረበበት ጊዜ አንስቶ እስከ ድህረ ሞት ዝግጅት ድረስ ያሉትን ክዋኔዎችን ገልጿል፡፡ ነገር ግን በተለይ በስርዓቱ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ያላቸውን የጾታ እና የማህበራዊ ደረጃ ጉዳይ አልገለጸም፡፡

ነጋ ተሰማ *"The Death Customs in the Province of Tigre"* በሚል ርዕስ ጽሁፍ ያቀረበ ሲሆን የጥናቱ ትኩረት በትግራይ ክልል የሚደረግ የለቅሶ ስርዓት ምን እንደሚመስል ማሳየት ነው፡፡ ጸሃፊው በማህበረሰቡ በድህረ ሞት ወቅት የሚከወኑ የተለያዩ ክንውኖችን አንስቷል፡፡ ይህም አንድ ሰው ከመሞቱ በፊት ቤተሰቦች፣ ዘመዶች እና ጎረቤቶች ተሰብስበው ከህመሙ እንዲሻለው ጸሎት ያደርጉለታል፡፡ ነፍሱ ከመውጣቷ በፊትም ተሰባሰባስበው ይሠናበቱታል፡፡ እንዳንዶች በዚህ ወቅት ማልቀስ ይጀምራሉ፡፡ ነፍሱ ከወጣች በኋላ አስከሬኑን በአዲስ ጨርቅ ይገንዙታል በማለት ገልጿል፡፡

በጽሁፉ ውስጥ እንደተገለጸው የሟችን ህልፈተ ህይወት የሰሙ ዘመዶችና ጎረቤቶች እየጮሁ፣ ፊታቸውን እየቧጨሩ፣ ጸጉራቸውን እየነጩ ማልቀስ ይጀምራሉ፡፡ በሌሊት ቄሶች መጥተው አስከሬኑን ከበው ፍታት ያከናውናሉ፡፡ ከፍታት በኋላ ከቤተ ክርስቲያን በሚመጣ ከእንጨት እና ከቆዳ በተሰራ ትንሽ አልጋ በሚመስል ነገር አስከሬኑ ወደ ቤተክርስቲያን ይሄዳል፡፡ በጉዞ ወቅት ከአስከሬኑ በኋላ ወንዶች ከዛም ሴቶች ደግሞ ይከተላሉ፡፡ ከቀብር በኋላ ለቀስተኞች ወደ ቤት ይመለሳሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሴቶች ይቀድማሉ፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት ቡና እና ንፍሮ አዘጋጅቶ ለማቅረብ ነው፡፡ ለቀስተኞች ሲመለሱ ቡና፣ ንፍሮ፣ አንባሻ ከተገኘም ጠላ ይቀርብላቸዋል በማለት ነው፡፡

ለቅሶውን ያልሰሙ ዘመዶች እና ወዳጆች በሰሙ ጊዜ እየሔዱ ያለቅሳሉ። ጎረቤቶችና ዘመዶች ደግሞ ለስምንት ቀናት ጠዋት ጠዋት ሟችን በማስታወስ እያለቀሱ ያጽናናሉ።

ሌሎች በማህበረሰቡ ከፍተኛ ክብር ያለቸው ሰዎች ሲሞቱ ሁለት ጊዜ የለቅሶ ስርዓት ይደረግላቸዋል። የሟች ቤተሰቦች በአንገታቸው ነጭ ክር ያስራሉ፣ የጣት እና የጆሮ ጌጣጌጦችን ያወልቃሉ፣ ልብሳቸውን አይቀይሩም፣ ወንዶች ጺማቸውን ሴቶች ጸጉራቸውን ይላጫሉ በማለት ጽፏል።

በአጠቃላይ ጽሁፉ በትግራይ በየትኛው የማህበረሰብ ክፍል የሚከወን የለቅሶ ስርዓት እንዳሳየ የገለጸው ነገር የለም። በተጨማሪም በጽሁፉ ውስጥ በክርስቲያን እና በእስልምና እምነት ተከታዮች መካከል ያለውን ልዩነት በአንዳንድ ክዋኔዎች የገለጸ ሲሆን ሌሎቹ ክዋኔዎች ደግሞ ተመሳሳይ ናቸው ማለት ይቻላል? የሚለውንም ጥያቄ ያስነሳል። ትግራይ ሰፊ በመሆኑ ጥናቱ የሁሉምን የትግራይ ማህበረሰብ የሚወክል ነው ብሎ ለመገመት ያስቸግራል።

## 2.2 ጽንሰ ሀሳባዊ ዳራ

ይህ ንዑስ ክፍል ስለ ለቅሶ ስርዓት የተፃፉ እሳቤዎች የሚዳሰሱበት ሲሆን ሞት፣ ለቅሶ፣ የለቅሶ ስርዓትና ማህበራዊ ደረጃ ፣ ሙሾ ግጥሞች የሚሉት ነጥቦች ትኩረት ተደርጎባቸዋል።

### 2.2.1 ሞት

ህይወት ያለው ነገር በመጀመሪያ ይወለዳል፣ ያድጋል ከዛም ይሞታል። ሞት እና ልደት በተቃራኒ ጽንፍ የቆሙ ክስተቶች ናቸው። ይህ ጉዳይ ደግሞ ህይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ የሚሆን ነው።

በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር በተዘጋጀው የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ የሞት እሳቤ በሚከተለው መልኩ ተገልጿል። *“ሞት የነፍስና የስጋ መለየት ወይም ህይወት ማጣት፤ ይህም በስጋዊ ወይም በመንፈሳዊ ሊሆን ይችላል።”* (1972፡50) ስጋዊ ሞት የስጋን ፍላጎት በመጉዳት፣ ራስን ዝቅ በማድረግ እምነቱ በሚፈቅደው መልኩ ራስን ለእምነቱ ማስገዛት ሲሆን የነፍስ ሞት የምንለው ደግሞ ሀይማኖቱ ወይም መንፈሳዊ ማንነቱ የሚገዛበትን ህግ ጥሶ መገኘት ነው። በዚህም ደስታውንና ህይወቱም ይጠላል።

ሞት በህይወት ውስጥ ያለና አብሮን የኖረ ነገር ቢሆንም በተከሰተ ጊዜ በሰው ልጅ ላይ የሚያሳድረው ከፍተኛ ስሜት አለ፡፡ ይህ ስሜት ደግሞ ሀዘን ነው፡፡ Hertz ይህን ስሜት *"we all belive we know that death is because it is familiar event and one that arouses in tense emotion."* (1960:27) በማለት የገለጸ ሲሆን ይህ ሃዘን ደግሞ ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ ለቅሶ ነው፡፡

### 2.2.2 ለቅሶ

ለቅሶ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ባዘጋጀው መዝገበ ቃላት ውስጥ *"ሃዘን፤ ሙሾ፣ ዋይ ዋይታ፣ መጮህ፣ ማንባት፤ የእንባ መመንጨት፣ መውረድ፣ መፍሰስ"* (1993፣17) የሚል ተገልጾ እናገኛለን፡፡ ሞት ሁሌም ከፍተኛ የሆነ ስሜትን ይፈጥራል፡፡ ይህ ስሜት ደግሞ በእንባ በማፍሰስ፣ በጩኸት ወ.ዘ.ተ ሊገለጽ ይችላል፡፡

እንደባህሉ እና እንደ አካባቢው የተለያዩ የለቅሶ ክንውኖችና ስርአቶች ይደረጋሉ፡፡ እነዚህ ስርዓቶች ደግሞ ማህበረሰቡን የሚገልጹ ናቸው፡፡ የተለያዩ ማህበረሰቦች ሰው ሲሞት በተለያዩ መንገዶች ስርዓተ ክዋኔውን ይፈፅማሉ፡፡ ዘሪሁን አስፋው

> *በአንዱ የለቅሶ ስነስርአት ሙሾ እየተደረደረ ደረት ይደለቃል÷ ይዘለላል፡፡ በሌላው ደግሞ የሟች የቅርብ ዘመዶች ፊታቸውን ይቧጥጣሉ÷ ፀጉራቸውን ይነጫሉ፡፡ በቀረው ደግሞ ከበሮ ይዞ በመጨፈር የልቅሶ ክዋኔ ይደረጋል፡፡ በሆታና በድልቂያ ሙታቸውን የሚሰናበቱም አሉ፡፡* (1992፡22-23) በማለት ይገልፁታል፡፡

ይህ ሀሳብ እንደሚያመለክተው በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ የሚከወነው የለቅሶ ስርዓት እንደባህሉና እንደ አካባቢው የሚለያይ መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን የለቅሶ ስርዓቱ ከማህበረሰብ ማህበረሰብ እና ከባህል ባህል የሚለያይ ቢሆንም በዓለም ላይ ተመሳሳይ የሆኑ ክንውኖች እንዳሉ World Book Encyclopedia ላይ ተገልጾ እናገኛለን፡፡

> *Funeral customs vary from society to society, but many of the same practices are found through out the world. These practices include public announcement of the death; preparation of the body; religious ceremonies or other services; a procession; a burial or other form of disposal; and mourning* (vol.7,1978, 483).

ጽሁፉ እንደሚያመለክተው ተመሳሳይ ከሆኑ ክዋኔዎች መካከል ሟች መሞቱን ማሳወቅ፣ መገነዝ፣ ሃይማኖታዊ ስርዓት መፈጸም፣ ወደ ቀብር ቦታ ጉዞ ማድረግ፣

ሬሳውን መቅበር እና ለሟች ማልቀስ የዓለም ህዝቦች የሚከናወኗቸው ድርጊቶች እንደሆኑ ነው፡፡

### 2.2.3 ማህበራዊ ደረጃና የለቅሶ ስርዓት

በአንድ ማህበረሰብ ወይም ቤተሰብ ውስጥ ማህበራዊ ደረጃ በለቅሶ ሥነ-ስርአት ላይ የራሱ የሆነ ሚና ይኖረዋል፡፡ የማህበራዊ ደረጃ እንደየባህሉ ሁኔታ የተለያየ ቢሆንም በእያንዳንዱ ማህበረሰብ ውስጥ አባላቱ የየራሳቸው ተግባራት ይኖሯቸዋል፡፡ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ለአንድ ሰው የሚሰጠው ማህበራዊ ደረጃ ያከናወነው ተግባር ከሌሎች አባላት ጋር ተነጻጽሮ ያገኘውን ውጤትን መሰረት ያደረገ ሊሆን ይችላል፡፡

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ለአንድ ሰው የሚሰጠው ቦታ ወይም ማህበራዊ ደረጃ ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ የለቅሶ ስርዓቱ ነው፡፡ ሟች በማህበረሰቡ ውስጥ እንዳለው ማህበራዊ ደረጃ የለቅሶ ስርዓቱም ይከወንለታል፡፡ ሟች ጀግና ፣ ባላባት ወይም የባላባት ልጅ፣ የጎሳ መሪ ወዘተ ከሆነ በስርዓቱ ላይ ከማልቀስ በተጨማሪ እንደባህሉ የተለያዩ ስርዓቶች ሊከወኑለት ይችላሉ፡፡ በዚህ ስርዓት ላይ የሚከወኑ ማንኛውም ድርጊቶች የሟችን ሁኔታ የሚገልጹ ናቸው፡፡ ይህን ሀሳብ Brown "*When death takes …. Some important member of the group, the whole community becomes involved every people the fact of grief and almost every where there are patterns of mourning.*" (1963:60)በማለት ያስረዳሉ፡፡

### 2.2.4 የሙሾ ቃል ግጥም

የሙሾ ቃል ግጥም ሟች በህይወት ዘመኑ የፈጸማቸውን በጎ ተግባራት እያወሱ ቤተሰቦች እንዲሁም ወዳጅ ዘመዶች ሀዘናቸውን የሚገልጹበት መንገድ ነው፡፡ ክዋኔው ምልዑ የሚሆነው የሙሾ ግጥሙ ብቻውን ቀርቦ ሳይሆን በስርዓቱ ላይ ከሚቀርበው አጠቃላይ ክዋኔ ጋር ተዋህዶ ነው፡፡ ቃል ግጥሙ ያለ ከዋኔው ህይወት አይኖረውም፡፡ ክዋኔው ደግሞ ከቦታ ቦታ የተለያየ ነው፡፡

የቃል ግጥም ክዋኔ የተለዋዋጭነት ባህሪው የጎላ ነው፡፡ ለዚህም ምክንያቱም ቃል ግጥም በቃል የሚተላለፍ በመሆኑና ቃል ግጥሞቹ ከሟች ማንነት ጋር ለማዛመድና አጽንኦት ለመስጠት ሲባል በክዋኔው ወቅት ስለሚቀየር ነው፡፡ ይህን ባህሪ Finnegan እንደሚገልጹት *"Many of this songs are tropical and empermeral that is they are composed for use at the funeral of one individual and related to him only."*

(1970:149)፡፡ ከላይ በቀረበው ሃሳብ መሰረት ብዙዎቹ የሙሾ ቃል ግጥሞች በክዋኔው ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉና ከክዋኔው በኋላ የሚችሉ ናቸው፡፡

## 2.3 ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ

በዚህ ክፍል የቀረበው የክዋኔ ንድፈ ሃሳብ እና በንድፈ ሃሳቡ ውስጥ የምንመለከታቸውን የክዋኔ አላባውያንን የሚመለከት ነው፡፡

ክዋኔ ተግባቦታዊ ድርጊት ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ ከተውኔት ጋር የሚቆራኝ ጥበባዊ ድርጊት ነው፡፡ እያንዳንዱ ክዋኔ በአጋጣሚው ውስጥ በቃልም ሆነ በተግባር እየተከወነ ይኖራል፡፡ በዚህም ህልውናውን ያስጠብቃል፡፡ የአንድ ፎክሎር ክዋኔ እንደየማህበረሰቡ እና ባህሉ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል፡፡ ክዋኔ ከትንሽ አጋጣሚ እስከ ከፍተኛ ዝግጅት የሚያስፈልገው አጋጣሚ ድረስ ማህበረሰቡ የሚገለገልበት እና ራሱን የሚገልጽበት መንገድ ነው፡፡ Finnegan ክዋኔን "*performance takes place kinds of sitution from highly organized and plan to quite informal and impromptu.* (1992:95) በማለት የክዋኔን መከሰቻ አጋጣሚዎች ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም Finnegan (1992፡87) ክዋኔን ሲያብራሩ ክዋኔው የሚካሄድበትን ጊዜና ቦታ ፣ የክዋኔውን መከሰቻ ምክንያት፣ የክዋኙንና የታዳሚውን ሚና፣ የከዋኙን ጥበባዊ አቀራረብ፣ የታዳሚዎቹ አቀባበል ይይዛል ብለዋል፡፡

በክዋኔ ውስጥ ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ ፣ አውድ፣ የክዋኔ ጠቋሚዎች እጅግ የተቆራኙ ነገሮች ናቸው፡፡ ይህን ቁርኝት Bauman *"The term performance has used to convey a dual sense of artistic action the doing of folklore an artistic event the performance situation. Involving performer, art form, audience and setting."* (1977፡4) ማለት ይገልጹታል፡፡

እንደ Bauman አገላለፅ ክዋኔ የሚለው ቃል ጥበባዊ ድርጊት ሆኖ የክዋኔውን ሁኔታ፣ ከዋኞችን፣ ጥበቡን፣ ታዳሚውን እና መቼቱን የያዘ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ለክዋኔ መሠረታዊ ነገሮች ናቸው ከሚባሉት ነጥቦች መካከል ከዋኝ (Performer)፣ ታዳሚ (audience)፣ አውድ(context) እና የክዋኔ ጠቋሚዎች (markers) የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ከዋኝ የክዋኔ አላባውያን ከሚባሉት ውስጥ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ከዋኙ ክዋኔውን በሚገባ አቀናጅቶ ለማቅረብም ሆነ የክዋኔውን አላማ ለማድረስ ማንነቱ፣ ማህበራዊው ደረጃው፣ እድሜው፣ የአከዋወን ብቃቱ ፣ የታዳሚን አያያዝ ችሎታው እና

የፈጠራ ችሎታው ጉልህ ሚና አላቸው፡፡ ከዋኝን አስመልክቶ Finnegan *"Performers are also of certain ages, gender, social position, training, reputation, and competence all needing investigation" (1992፣90)* በማለት ይገልፃሉ፡፡ የክዋኔውንም ሁኔታ የሚወስኑ ናቸው፡፡ ከዋኝ በክዋኔው ወቅት የሚያሳያቸው አካላዊ እንቅስቃሴዎች እና ድምጸቶች ለክዋኔው ወሳኝ ናቸው፡፡ እነዚህን በድል የተወጣ ከዋኝ በማህበረሰቡ ተመራጭ እና ተደናቂ ይሆናል፡፡

በአንድ ክዋኔ ውስጥ አንድ ሰው ብቻውን የከዋኝነት ሚና ሊጫወት ይችላል፡፡ በሌሎች ክዋኔዎች ደግሞ ታዳሚዎች ባሉበት ሊከውን ይችላል፡፡ ይህንን ሀሳብ Finnegan *"They may be acting singly; in pairs; in a small or a large group; interacting or exchanging with other single or collective performers as leader, follower, or equal; overlapping or interchanging with more audience-like roles.*" (1992፣89) በማለት ይገልፁታል፡፡

ከዋኝ በተለይ በለቅሶ ስርዓት ላይ ሟችን የሚመለከቱ ጥሩ ተግባራት እያነሳ ( በሙሾ፣ በፉከራ ወይም በቀረርቶ ) ሊሆን ይችላል እየገለጸ ወዳጅ ዘመዶች ሃዘናቸውን እንዲወጡ ያደርጋል፡፡

ታዳሚ በክዋኔ ውስጥ የሚነሳ ሌላው ጉዳይ ሲሆን ለክዋኔው ህልውና ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ የከዋኙም የከዋኝነት ሚና የሚረጋገጠው በታዳሚው በኩል የሚሰጡ አስተያየቶችና መስተጋብሮች ሲኖሩ ነው፡፡ የታዳሚዎች ሚና እንደፎክሎሩ አይነት ቢለያይም በአድማጭነት፣ በማጨብጨብ፣ በመቀበል ለክዋኔው አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡ በአንዳንድ ባህሎች በተለይ በሙሾ ክዋኔ ወቅት በሙሾ ደርዳሪ (አልቃሽ) እና በሙሾ ተቀባይ መካከል የሚደረገው መስተጋብር ታዳሚው በክዋኔው ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ሚና የሚያሳይ ነው፡፡ በክዋኔው ወቅት ሙሾ በመቀበል፤ ዋይ ዋይ በማለት፣ ደረት በመምታት፣ በመዝለል፣ በማልቀስ ወዘተ ይሳተፋሉ፡፡ ከዚህን በተጨማሪ በሙሾው ክዋኔ ወቅት በሚፈጠረው መስተጋብር ወይም ቅብብሎሽ በተጨማሪ በአንድነት መከወኑ የሚታይበት ሁኔታ አለ፡፡

በመሆኑም የክዋኔው ውጤታማነት እና ግብ መቺነት የሚወሰነው በከዋኞችና በታዳሚዎች ብቃት፣ እድሜ፣ ጾታ፣ ባህርይና ሚና ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች በወቅቱ የሚከሰቱ ወይም ባሉ ዓውዳዊ ነገሮች ላይ የተመሰረቱ እንደሆኑ ምሁራን ያስረዳሉ (Sims and Stephens, 2005:132)፡፡

አውድን አስመልክቶ Sims and Stephens የሚከተለውን ብለዋል፡፡ *"....context refers to anything and everthing that surrounds a text and performance."* (2005፡137)፡፡ አውድ አንድ ክዋኔ በሚከወንበት ወቅት ያለው አጠቃላይ ሁኔታ እንደሆነ ነው፡፡ ይህም ክዋኔው የሚከወንበትን ጊዜና ቦታ፣ በከዋኝ እና በታዳሚ መካከል ያለ መስተጋብር፣ የመከወኛ ቁሳቁሶችን ጭምር የሚያጠቃልል ነው፡፡

Sims & Stephens፦ Dan Ben Amosን ጠቅሰው አውድ ተጨባጭ አውድ እና ማህበራዊ አውድ በመባል በሁለት ክፍሎች ከፍሎ መመልከት እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡ ተጨባጭ አውድ የምንለው በክዋኔው ወቅት የሚታየው የመልክዓምድር ሁኔታ፣ የአየር ንብረቱ ሁኔታ፣ አካላዊ እንቅስቃሴ፣ ክዋኔው የሚኪያሄድበትን ጊዜ፣ ከዋኙንና ታዳሚውንም እንዲሁም ፎክሎረኛውንም የሚያጠቃልል ነው፡፡ Sims and Stephens ይህን ሃሳብ *"The physical environment also includes who is persent performer and audience members as well as any observers of course that includes the folklorist".* (2005:138) በማለት ይገልጹታል፡፡

ማህበራዊ አውድ የምንለው ደግሞ የከዋኙን እና የታዳሚን ማንነት፣ ጾታ፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ ሀይማኖት የሚመለከት ነው፡፡ በአንድ ከዋኔ ላይ የሚታዩ የከዋኝን እና የታዳሚን ስብጥር፣ በክዋኔው ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ፣ ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር ያላቸውን ግንኙነት የምናይበት ነው፡፡

በአንድ የፎክሎር ክዋኔ ውስጥ የክዋኔውን መጀመርና እና መጠናቀቅ እንዲሁም እየተከወነ መሆኑን የሚያሳውቁ ጠቋሚዎች መኖራቸውን Sims & Stephens "*...devices or actions mark the ends and beginnings of performances. We often call these signs markers, and they are an important part of describing and analyzing performance"* (2005፣141) በማለት ይገልጻሉ፡፡

እነዚህ ጠቋሚዎች በከዋኝና በታዳሚ መካከል ያለ መስተጋብር እንዲሰምር የሚያደርጉ፣ የክዋኔውን ስርዓት መልክ የሚያሲዙ፣ የከዋኝንና የታዳሚን የክዋኔ ቅደም ተከተል የሚያሳውቁ እንዲሁም ማህበረሰቡ ይሁነኝ ብሎ ተስማምቶ የፈጠራቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ስምምነቶች በክዋኔው ወቅት ምን መደረግ እንዳለበት ወይም የእያንዳንዱን የስራ ድርሻ ምን ሊሆን እንደሚችል የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን

ከተለመደው የማህበረሰቡ የአከዋወን ስልት እንዳይወጣ የክዋኔ ጠቋሚዎች ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

የታዳሚና የከዋኝ እንቅስቃሴ፣ መከወኛ ቁሳቁሶች በአንድ ክዋኔ ውስጥ ክዋኔ ጠቋሚዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ጠቋሚዎች ታዳሚዎች በክዋኔው በንቃት እንዲሳተፉ፣ እረፍት እንዲወስዱ፣ እንዲሁም ከአንዱ ድርጊት ወደ ሌላ ድርጊት እንዲሸጋገሩ ፍንጭ ይሰጣል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት፡ አካባቢያዊ ዳራ

## 3.1 የዲዚ ብሄረሰብ መገኛ

የዲዚ ብሄረሰብ በቤንች ማጂ ዞን ከሚገኙ 6 ብሄረሰቦች መካከል አንዱ ሲሆን በማጂ ወረዳ በ22 ቀበሌዎች በቤሮ ወረዳዎች ደግሞ በ12 ወረዳዎች ሰፍሮ ይገኛል፡፡ የማጂ ወረዳ በደቡብ ክልል በቤንች ማጂ ዞን ከሚገኙት አንድ የከተማ አስተዳደር 10 ወረዳዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የወረዳው ከተማ ቱም ከሚዛን አማን 187.5 ኪ.ሜ፣ ከክልሉ ርእሰ ከተማ ከሃዋሳ ደግሞ 1004 ኪ.ሜ እንዲሁም ከአዲስ አበባ በ777 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡

የዲዚ ብሄረሰብ  በማጂ ወረዳ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በቤንች ማጂ ዞን ውስጥ ይገኛል፡፡ ወረዳውን  በሰሜን የመዒኒት ሻሻ ወረዳ፣ በደቡብ የሱርማ ወረዳ፣ በምዕራብ ከሀሮ ወረዳ፣ በምስራቅ በኩል ደግሞ የደቡብ ኦሞ ዞን ጋር ያዋስኑታል፡፡

አሁን ማጂ ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ቀደም ባሉት ጊዜያት በተለያዩ ስያሜዎች ይታወቅ ነበር፡፡ ከነዚህም ቀደምት መጠርያዎቹ መካከል የማጂ አውራጃ ግዛት፣ የማጂ አውራጃ አስተዳደር፣ የማጂ ዞን እንዲሁም የዲዚ ወረዳ ተብሎ ይጠራ ነበር፡፡ ("ዲስት ያብ/የዲዚ ሰው" 1997፡13 ዓ.ም)

## 3.2 የወረዳው መልክዓ ምድራዊ ገፅታ

የማጂ ወረዳን የመልክኣ ምድር አቀማመጥ ስንመለከት  ከባህር ጠለል በላይ ከ400 እስከ 2500 ሜትር ሲሆን የሙቀት መጠኑም በአማካይ 27°c ነው፡፡ የዝናብ መጠኑም  ከ900 እስከ 2000 ሚሊ ሜትር የሚገመት ሲሆን ከስነ ምህዳር ስብጥር አንጻር  40.6% ቆላማ፣ 42.8% ወይና ደጋ፣ 12% ደጋ እንዲሁም 4.6% በረሃማ የአየር ንብረት መያዙን ከቤንች ማጂ ዞን ባህልና ቱሪዝም የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ( ለ3ተኛው የቤንች ማጂ ዞን የባህል ፌስቲቫል የተዘጋጀ ጽሁፍ፡፡ 2005፡3)

ብሔረሰቡ በዋነኝነት የሚኖርባቸው የማጂና የቤሮ ወረዳዎች ሜዳማ፣ ተራራማና ሸለቋማ የመሬት አቀማመጥ ሲኖራቸው፤ የአየር ንብረታቸውም አብዛኛው ክፍል ወይና ደጋ እና ቆላ በጣም አነስተኛው ደግሞ ደጋና በረሃማ ነው፡፡ ብሔረሰቡ ለኑሮ የሚመርጠው ተራራማ፣ ደጋና ወይና ደጋ የአየር ንብረት ያላቸውን ቦታዎች ነው፡፡

በአካባቢው የሚኖሩ ሽማግሌዎች እንደሚገልጹት፡- “ዲዚ” ማለት ቀዝቃዛ፣ ደጋ እንዲሁም ውሃማ ማለት ነው። ይህ ስያሜ ብሔረሰቡ ለኑሮ ከሚመርጠው የአየር ንብረት ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት አለው።

ከዚህም በተጨማሪ ዲዚዎች ጎጇቸውን የሚቀልሱት አራርቀው ሲሆን ለዚህም ምክንያታቸው ርስ በርስ ላለመጣላት እንዲሁም ቅርብ ለቅርብ ከሆኑ ያንዱን ሚስት አንዱ ያባልጋል ከሚል ስጋት የመነጨ እንደሆነ አቶ ባልኩ ኩሙ የተባሉ የሃገር ሽማግሌ ነግረውኛል።

በ1999 ዓ.ም በተደረገው የህዝብና የቤት ቆጠራ መረጃ መሰረት የዲዚ ብሄረሰብ ህዝብ ብዛት 36,380 ያህል እንደሆነ የማእከላዊ ስታስቲክ ኤጀንሲ ይገልጻል። ከወረዳው ከሚገኙ 22 ቀበሌዎች መካከል 11 ቀበሌዎች አርብቶ አደሮች ሲሆኑ የሚኖሩበት ቦታ የቆዳ ስፋትም 691,160 ሄክታር ነው። ሌሎች የብሄረሰቡ አባላት በእርሻ እና በንግድ ስራዎች የሚተዳደሩ ናቸው። በወረዳው ተጠቃሽ የሆነ የደን ሃብት የሚገኝ ሲሆን የተለያዩ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች( ብርቱካን፣ አናናስ፣ ሙዝ፣ ቲማቲም) በከፍተኛ ደረጃ የሚገኙበት አካባቢ ነው።

### 3.3 ቋንቋ

የዲዚ ቋንቋ “Afroasiatic” ከሚባል የቋንቋ ግንድ ከOmotic የቋንቋ ቤተሰብ ሰሜናዊ ኦሞቲክ Dizoid (ዲዝና፣ ሽኮ) ቡድን ጋር እንደሚመደብ የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፕሮፋይል (2001፣85) ይገልጻል። ብሄረሰቡ በዋነኛነት ዲዚኛ ቋንቋ የሚናገሩ ሲሆን ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተጨማሪ ሱርመኛ፣ መኤንኛ እና አማርኛን በተለያዩ ደረጃ ይጠቀማሉ።

### 3.4 ታሪካዊ አመጣጥ

የዲዚ ብሄረሰብ የዘር ግንድ አመጣጡ ከ3 አቅጣጫ ማለትም ከትግራይ፣ ከቀደመው የጋሞ ጎፋ ብሄረሰብ እና ከደቡብ ቤንች ወረዳ ዞዞ ቀበሌ በመነሳት በአንድነት ተጣምረው የሚኖሩ ብሄረሰቦች መሆናቸውን “የማጂ ጎልዲያ ውበት“ በሚል ርዕስ በ1952 ዓ.ም በሌ/ኮሎኔል ከበደ ተሰማ የተጻፈው ታሪካዊ ጽሁፍ ያስረዳል። ከዚህም በተጨማሪ “ዲዚ ሰው” በሚለው ጽሁፍ የብሄረሰቡ ታሪካዊ አመጣጥ በሁለት መልኩ ተገልጾ ይገኛል።

*ማጂ ገገር፣ አዲካስ፣ ጀባ ቡርጂና ጋዝ ቡርጂ እንዲሁም ኩሪ[1] ከትግራይ በመነሳት ጎሞጉፋ ደርሰው ልዩ ስሙ ባኮ በተባለው ስፍራ ከሰፈሩ በኋላ ኦሞን በመሻገር ቡሜ ገብተዋል፡፡ ቀጥለውም ኮሎ ቀበሌ ሲደርሱ ጋዝ፣ ኔርን እና ኩም የተባሉት ኮሎ ሲቀሩ የተቀሩት አዲካስ ገብተው ሰፈሩ፡፡ ጀባ ቡርጂ ወደ ጀባ ሲሄድ አዲካስም አዲካስ ላይ ቀረ፡፡ ማጂ ገገርና ኩሪ ለጊዜው አዲካስ ላይ ቢሰነብቱም አሁን እንጦጦ በሚባለው ስፍራ ባላባት የነበረው ጋቡ ቡርጂ/አሁን የለም/ ልዩ መልዕክተኛውን ደምጻይኒ ወደ አዲካስ ላይ በመላክ እነዚህ አዲካስ ላይ የሰፈሩትን ሰዎች ወዴት የምትሄዱ ናችሁ? ምንስ ትፈልጋላችሁ? ብሎ እንዲጠይቅ ይልከዋል፡፡ መልዕክተኛው ዳም ጸይኒም አዲካስ ደርሶ ይጠይቃቸዋል፡፡ መልሳቸውም ማጂ ጥሩ ሃገር ነው ሲባል ስለሰማን ልንኖርበት መጥተናል በማለት ይመልሳሉ፡፡ ከኩሪ በስተቀር ሁሉም ከትግራይ መምጣታቸውን ገልጸዋል ኩሪ አብሮአቸው ነው የገባው፡፡ (1997፡3)* በማለት ታሪካዊ አመጣጡን ይገልጻል፡፡

የብሄረሰቡን ታሪካዊ አመጣጥ እንደዚህ ነው ብሎ ለመግለጽ ትክክለኛ መረጃ ያላገኘሁ ሲሆን ይሁንና ከላይ ከተገኘው መረጃና ከብሄረሰቡ ተወላጅ የሃገር ሽማግሌዎች ለማወቅ እንደቻልኩት ቡሜን ተሻግረው መምጣታቸው ይስተዋላል፡፡፡

አቶ ባልኩ ኩሙ የብሄረሰቡን ታሪካዊ አመጣጥ አስመልክቶ እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፡፡

*የዲዚ ሰው እዚህ ማጂ ላይ ሲሰፍር ከብዙ ቦታ መጥተው ነው፡፡ እኔ አባቴ እንደነገሩኝ ከሆነ በዚህ ቦታ ሁለት ታላላቅ ባላባቶች እንደነበሩ ነው፡፡ የመጡትም በጠብ ምክንያት ከትግራይ ፈልሰው "ከምቢት" በሚባለው ስፍራ ላይ ይቀመጣሉ፡፡ ብዙ ከኖሩ በኋላ ልጆቻቸው ይበዛሉ፡፡ በመካከላቸውም ጠብና ክርክር በመነሳቱ ተለያይተው መኖር ይጀምራሉ፡፡ አባትየው "ጋር ቡርጂም" ልጆቹን በመሰብሰብ "ያልግ" በሚባለው ቦታ መኖር ይጀምራል፡፡ ከርሲ ኪያም ከያልግ ፈቀቅ ብሎ "ጎተት" በሚባለው ቦታ ተቀምጦ መኖር ይጀምራል፡፡ ከዛም ትውልዳቸው እየበዛ እየበዛ እየሰፋ መጥቶ እዚህ እንደደረሰ ነው፡፡* (ቃለመጠይቅ፡10/06/06 በመኖርያ ቤታቸው ውስጥ)

የብሄረሰቡ ነዋሪዎች የመጡበትን ጊዜ በውል እንዲህ ነው ብለው መናገር ባይችሉም ከነሱ ትውልድ ጀምሮ ያለውን ትውልድ የኖረበትን ዘመን በመቶ ዓመት ስሌት በማስላት ከ300 እስከ 400 ዓመት ሊደርስ እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡

[1] ማጂ ገገር፣ አዲካስ፣ ጀባ ቡርጂ፣ ጋዝ ቡርጂና ኩሪ የሚባሉት በዲዚ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ባላባቶች ሲሆኑ ቀደምት የብሄረሰቡ ነዋሪዎች እንደሆኑ የሀገር ሽማግሌዎች ይገልጻሉ፡፡

## 3.5 ባህላዊ እሴቶች

በዲዚ ብሄረሰብ ዘንድ የሚታዩ ባህላዊ እሴቶች ብዙ ናቸው፡፡ እነዚህ ባህላዊ እሴቶች ከለቅሶ ስርዓቱ ጋር ተያይዘው የሚከወኑና ተያያዥነት ያላቸው ናቸው፡፡ በዲዚ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ውስጥ ምግብ እና የአመጋገብ ስርዓት፣ አልባሳት፣ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት ፣ባህላዊ የሙዚቃ መሳርያዎች  እንዲሁም የጋብቻ ስርዓታቸው በለቅሶው ክዋኔ ጊዜ የሚታዩ እና አብረው የሚከወኑ በመሆናቸው ከዚህ በታች ይቀርባሉ፡፡

### 3.5.1 ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት "ታርቅ ሲ"

የዲዚ ብሔረሰብ አስተዳደር መዋቅር ከአብይ ጎሳዎች ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዳለው መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ የአስተዳደር መዋቅሩ የተለያዩ ተዋረዳዊ እርከኖች ያሉት ሆኖ በበላይነት የሚመራው በየጎሳው ውስጥ ባሉት ባላባቶች ነው፡፡ የጎሳ መሪዎች (ባላባቶች) ስያሜያቸው ከጎሳ ጎሳ የሚለያይ ሲሆን ቡርጂ፣ ኪያብም፣ ኪያዝ የሚባሉት እኩል ስልጣን ያላቸው(አቻዎች) እንዲሁም በባህሉ "መሶብ" የሚጋሩ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ከዚህም ቀጥሎ ዝቅ የሚሉት ያኒ፣ ባር፣ ኮይዝ፣ ጨየዢ፣ ባቡ ተብለው የሚጠሩት እንደ የጎሳቸው የራሳቸው ኃላፊነት ቢኖራቸውም ተጠሪነታቸው ለባላባቱ የጎሳ መሪ ነው፡፡

ከጎሳ መሪዎች ጀምሮ በብሔረሰቡ ኃላፊነት ያለው ማንኛውም አካል አስተዳደራዊና መንፈሳዊ ስራዎችን የመምራት ግዴታ አለበት፡፡ እነዚህ አካላት በብሔረሰቡ እንደ ሀይማኖት መሪም ስለሚቆጠሩ በሽታ ሲገባ፣ ድርቅ ሲከሰት እና ሌሎች ያልተጠበቁ ክስተቶች ሲፈጠሩ ባህላዊ ስርዓቶችን በየደረጃው ይፈጽማሉ፡፡ ከአቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ የአገር ሽማግሌዎች ተሰብስበው በጎሳ መሪው መሪነት ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡ የጎሳ መሪዎችም ሆነ በየደረጃው ኃላፊነት ያላቸው አካላት የሀይማኖት መሪ ከመሆናቸው በተጨማሪ በተፈጥሮ ላይ ስልጣን እንዳላቸው ይታመናል፡፡ በመሆኑም የዲዚ ብሔረሰብ የጎሳ መሪዎች ዝናብ ማዘነብና ማስቆም የሚችሉ፣ በበሽታን የሚያጠፉ፣ የዱር አራዊቶችን ማዘዝ እንደሚችሉ ይታመንባቸዋል፡፡

ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት እንደ የጉዳዩ ክብደትና ቅለት ከሽማግሌዋች አንስቶ እስከ ጎሳ መሪዎች ውሳኔ ሊሰጡበት ይችላል፡፡ በባህሉ ከሚዳኙ ጉዳዮች መካከል ግጭት(ጥል)፣ ሌብነት፣ አስገድዶ መድፈር የመሳሰሉት ናቸው፡፡ በብሔረሰቡ ባህል እነዚህን እና ሌሎች

ውግዝና ፀያፍ ጥፋቶች መፈፀም በትንሹ ከብት ከመክፈል ጀምሮ በግርፋት እንዲሁም በሞት ሊያስቀጣ እንደሚችል አቶ ባልኩ ኩሙ በቃለ መጠይቅ ወቅት ገልጸውልኛል፡፡

በዲዚ ብሔረሰብ አንዲት ልጃአገረድ ክብሯን ጠብቃ በድንግልና ስታገባ በባህሉ ቦታ የሚሰጣትና ቤተሰቦቿም እጅግ የሚኮሩባት ሲሆን ሴት ልጅን ከጋብቻ በፊት አስገድዶ ክብረ ንፅህናዋን የወሰደ በጥንት የዲዚ ባህል ለባላባቱ ሰባት ከብቶች፣ ለልጂቱ ቤተሰቦች አንድ ኮርማ በሬ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ከቅርብ አመታት በፊት በተለይም ከ40 ዓመት ወዲህ ጥፋተኛው ግለሰብ ለልጂቱ ቤተሰቦች ኮርማ በሬ የሚከፈል ሲሆን ለባላባቱ የሚከፈለው እንደቀረ አቶ ባልኩ አክለው ገልጸዋል፡፡

ለውሳኔዎች እንደ ህግ የሚያገለግለው ባህሉ ሲሆን ተቀጪዎቹ ከብሔረሰቡ ባህል ወግና ልማድ ማፈንገጥ ተገቢ አለመሆኑን እንዲማሩ የሚያስችል የዳኝነት ስርዓት ነው፡፡ እያንዳንዱ አብይ ጎሣ የራሱን አብይ ጎሳ ከማስተዳደር ውጪ በሌላው ጎሳ ስራ ውስጥ ጣልቃ አይገቡም፤ ይህ ደግሞ ሁሉንም የዲዚ ጎሳዎች በበላይነት የሚመራ አንድ ባላባት አለመኖሩን እና እያንዳንዱ የጎሳ መሪም ሙሉ ነፃነት እንዳለው "የዲዚ ሰው" (1997፡25) ይገልጻል፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች በሁለት ጎሳዎች መካከል የከረረ ግጭት ከተፈጠረ ሌሎች ጎሳዎች እርቅ እንዲፈጠር በመሀል በመግባት በአንደኛው ባላባት ወይም በታዋቂ ግለሰብ ግቢ ውስጥ በማደራደር ማስታረቅ/የዳኝነት ስራ ይሰራሉ፡፡ በድርድሩ መሠረት ከስምምነት ላይ ከተደረሰ በኂላ ጥፋተኛው ወገን በሬ/ወይፈን በቅጣት መልክ እንዲያቀርብ ይደረግና የበሬው ወይም የወይፈኑ ስጋ ተጠብሶ በአንድ ማዕድ ሁለቱም እንዲቀምሱት በማድረግ እርቅ ስርዓቱ ይጠናቀቃል፡፡ ከተፈጠረው ግጭት የተነሳ ነፍስ መጥፋት ቢከሰት የገዳዩና የሟች ወገኖችን በማቀራረብ የማስታረቅ እና ባህላዊ የእርቅ ስርዓቶችን የመፈፀም ስራ ይከናወናል፡፡ ጉዳዩ በሽማግሌዎች ከተመረመረ በኂላ ደም ለማድረቅና በቂም በቀል እንዳይፈላለጉ ለማድረግ ሙዳ ስጋ በሁለት ጫፍ ነክሰው በመያዝ እንዲበሉና በጦር መሳሪያ ላይ ተረማምደው እንዲያልፉ ይደረጋል፡፡ እነዚህ ባህላዊ ስርዓቶች ከተፈፀሙ የተከሰተው ደም መፍሰስ ተወግዷል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስርዓቱም በባህሉ "በትኩስ ወተት መታጠብ" የሚል ስያሜ አለው፡፡

## 3.5.2 ባህላዊ አልባሳት

በጥንት ዘመን የዲዚ ብሔረሰብ የሚለብሷቸው ልብሶች ከተለያዩ የቤትና የዱር እንስሳት ቆዳዎች የተዘጋጁ ሲሆኑ እነዚህ አልባሳት የባላባት፣ የወንድና የሴት፣ የሠርግና ያገቡ እናቶች ልብስ ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡

**ሀ/ የሴቶች አልባሳት**

በዚህ ስር የምንመለከታቸው  አልባሳቶች የልጃገረዶች አልባሳትና የአዋቂ ሴቶችን አላባሳት ነው፡፡ የልጃገረዶች አልባሳት፡- የዲዚ ልጃገረዶች የሚለብሱት ከፍየል ቆዳ የሚዘጋጅ ከወገብ በታች አገልድመው የሚለብሱት "ካርን" ይባላል፡፡ "ካርን" የሚለበሰው ለሰርግ ብቻ ሲሆን የምትለብሰውም ሙሽራዋ ናት፡፡ ሌላው ወጣቶች የሚለብሱት "ጠቢል" ሲሆን ከከብት ቆዳ የሚዘጋጅ አጭርና ጉርድ ሲሆን ከወገብ እስከ ጉልበት የሚሸፍን እና በግራና ቀኝ ታፋዎች በኩል ክፍት የሆነ ነው፡፡ ሴቶች ከዚህ በተጨማሪ ለጌጥ ከተለያዩ ብረቶች የተሰሩ አምባሮችን፣ ከመዳብ የተሰሩ ጉትቻና ጨሌ በእጃቸው በጆሮአቸውና በአንገታቸው ላይ ያጌጣሉ፡፡

ሌላው የአዋቂዎች ልብስ "ሳይ/ቂያሉ" በመባል ሲታወቅ የሚዘጋጀውም ከድኩላ ቆዳ ሆኖ በደንብ የተለፋና የለሰለሰ ነው፡፡ የሌሊት አልባሳት "ጎዝል" በመባል የሚታወቁ ሲሆን የከብትን ቆዳ ውስጡን እና ውጩን በደንብ በማልፋትና በማለስለስ የሚዘጋጅ ነው፡፡

**ለ/ የወንድ አልባሳት**

የወንድ አልባሳት የሚገለደም ሳይሆን በአንገት የሚታሰር ሆኖ የባላባትና የሌላ(ባላባት ያልሆነ) ሰው በመሆን ከነብር ቆዳ እስከ ቤት እንስሳት ቆዳ ባሉት ሊዘጋጁ ይችላሉ፡፡ ወንዶች በአምባር የሚያጊጡ ሲሆን ከነሀስ የተሰሩ ሎቲዎችን በጆሮአቸው ያንጠለጥላሉ፡፡  ይህም የጀግንነት ምልክት ነው፡፡ ባላባቶች ለሰርግና ለበዓላት ወቅቶች የነብርና የአንበሳ ለምድ የሚለብሱ ሲሆን ሚስቶቻቸው ደግሞ በጨሌ የተንቆጠቆጠ የፍየል ቆዳ ያገለድማሉ፡፡ ሌሎች የወንዶች አልባሳቶች ከበግ ወይም ከጥጃ ቆዳ በደንብ ተለፍቶና ለስልሶ የሚዘጋጅ ሲሆን ፀጉሩ ያልለቀቀና የፊት እግሩ በረጅሙ ተተልትሎ በአንገታቸው በኩል በማሰር እንደ ቀን ልብስ የሚለበስ ሲሆን "ቡል" ተብሎ ይጠራል፡፡

በሠርግና በበዓላት ወቅት የሚለበሱ አልባሳት ያሉ ሲሆን "ኢ-ባቺ" እና "ኢ-ኩወል" በመባል ይታወቃሉ፡፡ ኢ-ባቺ ከነብር ቆዳ የሚዘጋጅና ወገብ ላይ የሚገለደም ሲሆን ኢ-ኩወል በተመሳሳይ መልኩ ከነብር ቆዳ የሚዘጋጅ ሆኖ የነብር ቆዳው አገፋፈፉ በሙሉ ቁመትና ከእነጭራው ሆኖ ውስጡ በደንብ የለሰለሰ ነው፡፡  መሀሉን በመብሳት እንደካባ

የሚለበስ ሲሆን የነብር አንገትና የፊት እግር በደረት ላይ ሲያርፍ ጭራው ከበስተጀርባ በኩል ሆኖ ይለበሳል፡፡

ሁሉም የብሔረሰቡ አባላት በሌሊት ልብስነት የሚለብሱት "ኦይቲ-ባቺ" የተሰኘ ሲሆን ከትልቅ የከብት ቆዳ ውስጡን እና ውጩን በማልፋትና በማለስለስ እንደ ብርድልብስ የሚለበስ ነው፡፡ የአልባሳቱን ቀለማት በተለመከተ ከነብር ቆዳ ከሚዘጋጁት አልባሳት በስተቀር ሌሎች ከተለያዩ የቤት እንስሳት ቆዳ የሚዘጋጁ በመሆናቸው በአዲስነታቸው የዳሌቻነት መልክ ሲኖራቸው እየቆየ በሚለበሱበት ወቅት ወደ ቡናማነት ይለወጣሉ፡፡

### 3.5.3 ባህላዊ የአመጋገብ ስርዓት

የዲዚ ብሔረሰብ እንደ አብዛኛዎቹ የደቡብ ኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰብና ህዝብ ዋነኛ የምግብ ምንጩ እንሰትና የእንሰት ተዋጽኦዎች ናቸው፡፡ ከአንሰት በተጨማሪ ባህላዊ ምግቦችና መጠጦችን ከጥራጥሬ፣ ከስራስር፣ ከአትክልት፣ ከማር፣ ከእንስሳት ተዋጽዎች ወዘተ ይዘጋጃሉ፡፡ እነዚህ ምግቦች ምግብ ከመሆናቸው በተጨማሪ የማንነቱ መገለጫም ጭምር ናቸው፡፡

በዲዚ ባህል "አት" የሚባል ከማሽላ ኪጆ ወይም ኪጆውና ገብስ በሶ አብሮ የተዘጋጀ ተወዳጅ ባህላዊ ምግብ አለ፡፡ አት ለእንግዳ የሚቀርብ ተወዳጅ ምግብ ሲሆን አዘገጃጀቱ ከባድና አድካሚ ስለሆነ አይዘወተርም፡፡ አት የሚበላው በእርጎ ሲሆን በጎመንም ይበላል፡፡ አት የምታዘጋጅ ሴት ታታሪና ባሏን አክባሪ ተደርጋ ትወሰዳለች፡፡

የእንሰት ስር የሆነው "አምቾ" ተቀቅሎ ከወተትና ከጎመን ጋር የሚመገቡት ሲሆን በሰርግ ጊዜ ለታዳሚ በወተት የሚቀርብ የክብር ምግብ ነው፡፡ አምቾ በትንንሹ ተከትፎ በጎመን፣ በስጋና በቦለቁ "ጋዡ" (የአምቾ ገንፎ) ይዘጋጅበታል፡፡

ከእንሰት ቆጮ የሚዘጋጅ ሲሆን በዲዚ ብሔረሰብ ዘንድ "የእህል ንጉስ" ወይም "ኢትሳርን" የሚል ስያሜ አለው፡፡ የስያሜው መነሻ እንሰት ድርቅን የመቋቋም አቅም ስላለው ድርቅ እንኳ ተከስቶ ሌላ እህል ከአካባቢው ሲጠፋ ቆጮ የማይጠፋ ከመሆኑ የተነሳ ነው፡፡ ባላባቶችና የባላባት ወገኖች ቆጮ አይመገቡም፡፡

ዲዚዎች ከበቆሎና ከማሽላ ኪጆና ገንፎ አዘጋጅተው ይጠቀማሉ፡፡ ካችና ጎደሬ ለብሔረሰቡ ምግብነት የሚውሉ ሲሆን ማርም ለምግብነት (በአብዛኛው እንደ ማባያ) ይውላል፡፡ በከባድ ስራ ለደከሙ፣ በወሊድ ወቅት ብዙ ደም ለሚፈሳቸው አራስ ሴቶች የከብት ደም (የላም እና የበሬ) ከቦርዴና ከወተት ጋር በማቀላቀል ያጠጧቸዋል፡፡ በዲዚ

ባህል እራት ሁሉም የቤተሰብ አባላት የሚመገቡ ሲሆን ቀን በየራሳቸው ተመግበው ሊውሉ ይችላሉ፡፡

በአመጋግብ ስርዓቱ በማዕረግ፣ በፆታና በዕድሜ ተለይቶ ምግብ የሚቀርብ ሲሆን በምግብ ሰዓት ጮክ ብሎማውራት፣ ምራቅ መትፋት፣ ቁጭ ብድግ ማለት፣ አይንን ማንከራተት፣ በሁለት ጉንጭ መብላት  እንዲሁም ሌሎች እየተመገቡ የሙዚቃ መሳሪያዎችን መጫወት የተከለከለ ነው፡፡ ሴት ከባሏ ጋር ቀርባ አትመገብም፡፡ ልጆችም ከአባታቸው ጋር አይመገቡም፡፡ ይህም ለአባትየው ወይም ለቤቱ መሪ ክብር ለመስጠት ነው፡፡ እናትና ልጆች አብረው መመገብ ይችላሉ፡፡ በዲዚ ባህል በቀን ሁለት ጊዜ  ጧትና ማታ መመገብ ያዘወትራሉ፡፡ ሴቶች ባሎቻቸውን ስለሚያከብሩ ምርጥ ምርጡን የሚያቀርቡ ሲሆን እነሱ ደግሞ ባሎቻቸው ተመግበው ሲጨርሱ ይመገባሉ፡፡ በዲዚዎች ደረቅ ምግብ አይፈቀድም፡፡ የሚጠጣ ነገር የግድ አስፈላጊ ነው፡፡  ቦርዴ(ሙግ) ካገኙ እስከ ሶስት ቀናት ካለምግብ ሊቆዩ  እንደሚችሉ "የዲዚ ሰው" (1997፡15) ተገልጾ ይገኛል፡፡ ይህ መጠጥ እንደምግብነት ያገለግላል፡፡

በዲዚ ብሔረሰብ ባህላዊ መጠጦች ያሉ ሲሆን ጥቅል ስማችው "ሙጉ" በመባል ይታወቃል፡፡ ከእነዚህ መጠጦች የብሔረሰቡ ዋነኛ መጠጥ *"ኩቹ-ሙጉ" (ዲዚ ሙጉ)* የሚባለው ነው፡፡ አዘገጃጅቱም የጎነቆለ ማሽላ ተስጥቶ ከደረቀ በኋላ ይፈጭና ሙቅ ተሙቆ በገንዳ ወይም በትልቅ ማሰሮ ይደረጋል፡፡ አዘገጃጀቱ በባለሙያ ሴቶች ያለ ብቅል እንዲፈላ ተደርጎ ሲሆን ከአንድና ከሁለት ቀን በኋላ መፍላቱ ሲረጋገጥ ለመጠጥነት ይውላል፡፡ ኩቹ ሙጉ ረጅም ጊዜ ሳይበላሽ የመቆየት አቅም ያለው ሲሆን እየቆየ ሲሄድ ጣዕሙና ተወዳጅነቱ ይጨምራል፡፡

ከኩቹ ሙጉ በተጨማሪ ሌሎች "ዶርጅ"፣ "ያን"፣ "ጮንዱ" ተብለው የሚጠሩ መጠጡች ያሉ ሲሆን ሲሆን ከተለያዩ የእህል አይነቶች በገብስ ብቅል እንዲፈሉ ተደርገው የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ እነዚህ ባህላዊ መጠጦች ለደቦ (ለህብረት ስራ)፣ ለበዓላት፣ ለሰርግና ለመሳሰሉት ዝግጅቶች ተብለው የሚዘጋጁ ሲሆን ለቤተሰብ ከምግብ በኋላ እንደ ማወራረጃ አንዳንዴም እንደምግብነት ያገለግላሉ፡፡

### 3.5.4 ባህላዊ የሙዚቃ መሳርያዎች

ዲዚዎች የእስትንፋስና የክር  የሙዚቃ መሳርያዎች አሏቸው፡፡ በባህሉ ሙዚቃ በሰርግ፣ በሃዘን፣ በስራና በግዳይ ጊዜ ይቀርባል፡፡ በዲዚዎች የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ የሙዚቃ መሳርያዎች ናቸው፡፡ አብዛኞቹም በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚገለገሉባቸው ናቸው፡፡

"ጋዝ" የሚባለው የሙዚቃ መሳርያ  እንደበገና የሚደረደር ባለ አምስት ክር ሲሆን የመጨረሻው ትልቁ  ሲሆን "ኪበ" የሚባለው ደግሞ ከ "ጋዝ" ቀጥሎ ትልቁ ክራር ነው፡፡ "ኮንች"  በደረጃ ከትልቁ ክራር ሶስተኛው ሲሆን "ባር" ደግሞ  በጣም ትንሹ ክራር ነው፡፡

"ጊያቡ"/ጋሻ፡- በክንድ ላይ በሚታሰር "ቼርም" በሚባል አምባር በመምታት ቃና ያለው ድምጽ   በማሰማት ይዘፈንበታል፡፡ ለለቅሶም ሆነ ለሰርግ እንዲሁም በግዳይ ወቅት ይጠቀሙበታል፡፡ "ጋርዝ"   ጦር  ማለት ሲሆን እየተሰበቀ ይሸለልበታል፡፡

"ሄር"፡- ቃጭል ሲሆን ሴቶች በሁለቱም እግሮቻቸው ቁርጭምጭሚት እስከ ባት ድረስ ባለው አካባቢ ላይ በማሰር  እና እግሯን በመርገጥ እንደ ጃዝ ያለ ድምጽ በማውጣት የሚዘፍኑበት ነው፡፡ ኒሙጎልን፡- /ጡሩንባ/ የእስትንፋስ መሳርያ ሲሆን የተለያዩ ድምጾችን በማሰማት ይዘፈንበታል፡፡ "ታርቡ"፡- /ከበሮ/ በእጅ ወይም በእንጨት በመምታት ይዘፈንበታል፡፡

### 3.5.5 የጋብቻ ስነ ስርዓት

የዲዚ ብሄረሰብ የጋብቻ  ስርዓት ከለቅሶ ስርዓቱ ጋር ግንኙነት ያለው ሲሆን ይህም የጋብቻ የሚፈጠሩ ዝምድናዎችን እና በባህሉ ውስጥ ያላቸውን መዋቅር ለማወቅ የሚያችል ነው፡፡ በብሄረሰቡ ሰርግ "ቦዝ" በመባል ይጠራል፡፡ በዲዚ ብሄረሰብ ሶስት አይነት የጋብቻ  ስነ ስርዓት ያለ ሲሆን አንደኛው በቤተሰብ ስምምነት፣ ሁለተኛው በጠለፋ ሲሆን ሶስተኛው ደግሞ በውርስ የሚከናወኑ ናቸው፡፡ በቤተሰብ ስምምነት የሚባለው የጋብቻ አይነት ቤተሰቦች ልጅህን ለልጄ ተባብለው ልጆቻቸውን የሚድሩበት ሁኔታ ነው፡፡ በዚህ የጋብቻ ስርዓት ውስጥ ልጅህን ለልጄ የሚለው ጥያቄ አወንታዊ ምላሽ ካገኘ የጥሎሽ ስነ ስርዓት ይከናወናል፡፡

ቀደም ባሉት ጊዜያት በቤተሰብ ስምምነት የሚፈጸም ጋብቻ ሲሆን ለጋብቻው ከ35-40 ከብት  ጥሎሽ ይሰጥ የነበረ ሲሆን በአሁን ሰዓት ደግሞ ከ3-5 ከብት ወይም አንድ ሺህ ብር እና ከዚያም በላይ ጥሎሽ ይሰጣል፡፡ ሁለተኛው የጋብቻ አይነት ደግሞ ጠለፋ ሲሆን መንስዔውም የጥሎሽ መብዛት እንደሆነ የሚገመት ሲሆን በጥሎሽ አሰጣጡ ላይ ትልቅ ጭቅጭቅ የሚያስነሳ ቢሆንም በሽማግሌዎች እንዲስማሙ ይደረጋል፡፡

በዲዚ ብሄረሰብ ሌላው ለየት ያለ ጋብቻ የሚባለው የውርስ ጋብቻ የሚባለው ሲሆን ታናሽ ወንድም  ታላቁ ከሞተ የታላቁን ሚስት ይወርሳል፡፡ በሌላ በኩልም ልጅ የእንጀራ እናቱን ወርሶ የአባቱን ልጆችና እህት ወንድሞቹን የሚሰበስብበት መንገድ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው ሴቲቱ ወጣት ከሆነች ሌላ ባል አግብታ ዘር እንዳታበላሽ  እና እህት ወድሞቹ እንዳይጎዱ ታስቦ ነው፡፡ ታናሽ ወንድም የታላቁን ወድም በሚያገባበት ጊዜ ሴቲቱ አትጠየቅም፡፡ የወንድምህን ልጆችና እህት ወንድሞችህን ያዛቸው አሳድጋቸው ተብሎ አብሯት እንዲያድር ይደረጋል፡፡ የሴቲቱ ፈቃድ ያላስፈለገበት ምክንያት የከብት ጥሎሽ የተከፈለባት በመሆኑ እምቢ ማለት ስለማትችል ነው፡፡ ሴቲቱ በምንም መልኩ አይወርሰኝም ካለች ለጥሎሽ የተሰጠው ከብቶች ተመላሽ ይደረግና የፈለገችውን አግብታ መኖር ትችላለች፡፡

### 3.5.6 የሃይማኖት ተቋማትና ሀገረሰባዊ ዕምነቶች

የዲዚ ብሄረሰብ  አባላት የተለያዩ ሃይማኖቶችን የሚከተሉ ሲሆን በአብዛኛው የሃገረሰባዊ ዕምነት ተከታዮች ናቸው፡፡ እነዚህም ሀገረሰባዊ ዕምነቶቻቸው "ሚያንጉ"፣ "ኮይ" እና "ቤንቲ" በመባል ይጠራሉ፡፡ በእነዚህ ሀገረሰባዊ እምነቶች ውስጥ ባላባቶች ወይም "ቡርጂዎች" ከፍተኛውን ሚና የሚይዙና የዕምነቱ  መሪም ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ከእነዚህ ሀገረሰባዊ እምነቶች ውጪም አንዳንድ የብሄረሰቡ ተወላጆች  የኦርቶዶክስ ክርስቲያን፣ የፕሮቴስታንት እና የእስልምና እምነቶችን  የሚከተሉም አሉ፡፡

## 3.6 ባላባታዊ የአስተዳደር ስርዓት "ቡርጅ ያብ"

ባላባት በዲዚ ቋንቋ "ቡርጅ ያብ" የሚል ቃል ይጠራል፡፡ "ቡርጅ ያብ" የሚለውን ቃል በቀጥታ ባላባት ብሎ የተረጎመ መዝገበ ቃላት ያላገኘሁ ሲሆን ብሄረሰቡ የቃሉን ትርጉም በነገሩኝ መሰረት ባላባት ብዬ ተርጉሜዋለሁ፡፡  በዲዚ ብሄረሰብ ዘንድ ከሚከወኑ የለቅሶ ስርዓቶች መካከል  የባላባቶች የለቅሶ ስርዓት አንዱ ነው፡፡ ብሄረሰቡ በባላባታዊ ስርዓት የተመሰረተ ነው፡፡ ባላባት፣ የባላባት ወገኖች እንዲሁም ተራና ዝቅተኛ ክፍሎችም አሉት፡፡  ይህ ክፍፍል በዝርያና በኢኮኖሚ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በባላባታዊ የአስተዳደር ስርዓት ውስጥ ባላባቶች ማህበረሰቡን በመልካም አስተዳደርና በማህበረ ባህላዊ ህግ መሰረት ያስተዳድራሉ፡፡

ብሄረሰቡም ለባላባቶች  ወይም ለጎሳ መሪዎች የተለየ ቦታና ክብር ይሰጣል፡፡ ህዝቡም ለባላባቱ ታዛዥና በተጠራ ጊዜ ቀድሞ ደራሽ ነው፡፡ በቀደሙት አመታት በዲዚ

ብሄረሰብ ውስጥ በርካታ ባላባቶች የነበሩና ያስተዳድሩ የነበረ ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች አሁን ቁጥራቸው አናሳ ሆኗል፡፡ ከነዚህ ምክንያቶች መካከል ወራሽ(ተተኪ ባላባት) ማጣት አንዱ ነው፡፡ ወራሽ ለመሆን ደግሞ የባላባት ወገን ከመሆንም በተጨማሪ ሀብት አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡

በማጂ ወረዳ ሁለት ታላላቅ ባላባቶች አሉ፡፡ እነሱም "ማጂ ገዢ" እና "ኩሪ" የተባሉ ባላባቶች ናቸው፡፡ የእነዚህ ባላባቶች የዘር ግንድ አመጣጡ ከትግራይ እንደሆነ "የዲዚ ሰው" (1997፡13) የሚለው የብርሃኑ አይሳብ ጽሁፍ ይገልጻል፡፡ እነዚህን ሁለት ባላባቶችን ጨምሮ "አዲካስ"፣ "ጀባ ቡርጂ" እና "ጋዝ ቡርጂ" የተባሉ ባላባቶች ከትግራይ ተነስተው በጋሙጎፋ አድርገው ልዩ ስሙ "ባኮ" በተባለው ስፍራ ሰፍረው እንደነበረ ጽሁፉ ያስረዳል፡፡

ከዚህም በመቀጠል እነዚህ ባላባቶች በአንድ ላይ ተስማምተው መኖር ባለመቻላቸው "አዲካስ" ወደ አዲካስ የተባለው ቦታ ሲሄድ "ጀባ ቡርጂ" ደግሞ ጀባ ወደ ተባለው ሄዷል ይላሉ፡፡ ማጂ ገዢ፣ ጋዝ ቡርጂ፣ አዲካስና ኮሎ ቡርጂ አብረው የመጡ በመሆናቸው እንደዝምድና ተቆጥሮ እስከዛሬ ድረስ በመካከላቸው ጋብቻ አይፈጸምም፡፡

በማጂ ወረዳ ማጂ ገዢ እና ኩሪም ተከባብረውና ተቻችለው በመኖር ላይ ይገኛሉ፡፡ በተለያዩ ጊዜያት ሁለቱ የድንበር ግጭቶች ውስጥ ይገቡ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ተራርቀው እና የራሳቸውን ድርሻ ይዘው ባላባትነታቸውን አስጠብቀው መኖር ጀመሩ፡፡ ማጂ ገዢ "ዲልት"(ዶልግ) በሚባለው ስፍራ ላይ ይኖራል፡፡

ማጂ ገዢና ኩሪ በስራቸው ሌሎች ባላባቶችን ያስተዳድራሉ፡፡ እነሱም በማጂ ገዢ ባላባት ስር "ኦር ቡርጂ"፣ "ዱርና"፣ "ሳይ ኪያዝ"፣ "ሙይ ገዢ"፣ "ኩል ቡርጂ" እና "ገልከም" የተባሉ ባላባቶች ሲኖሩ ኩሪ የተባለው ባላባት ደግሞ "ጎብቲያል"፣ "ከርሲ ኪያም" እና "ሲስክ ኡሽ" የተባሉ ባላባቶችን ያስተዳድራሉ፡፡

የታች ባላባቶች ተጠሪነታቸው ለታላቅ ባላባቶች ሲሆን በአካባቢያቸው ደግሞ የሚከበሩና የተለያዩ ስርዓቶችን የሚፈጽሙ ናቸው፡፡ ታናናሽ ባላባቶቹ በአካባቢያቸው ያለውን ግብር ለታላቅ ባላባቶች የማስገበር፣ ለተለያዩ ስርዓቶች ወይም ደንቦች ማስፈጸሚያ የሚሆን ከብቶችን ማዘጋጀት እንዲሁም በአካባቢያቸው ያለውን ችግር

በራሳቸው አቅም የመፍታት ሃላፊነት አለባቸው። እነዚህ ሁለት ደረጃ ያላቸው ባላባቶች በመደጋገፍ እና በመከባበር የዲዚን ህዝብ ያስተዳድራሉ።

እነዚህ የታች ባላባቶች በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ክብርና እንክብካቤ ቢኖራቸውም ለታላላቅ ገዢዎቻቸው ተገዢዎች ናቸው። ይህን ባላባታዊ ስርዓት አስመልክቶ አቶ ቸሬ አኮ እንደገለጹት፡-

*በዲዚ ባህል ከባላባት በላይ የሚከበር ሰው የለም። ህዝቡም በጣም ያከብራል። ይፈራል። ይታዘዛል። የተባለውን ያደርጋል። ባላባት ድርቅ አጥፊ፣ ዝናብ አምጪ ነው። ሰው እስታራቂ ፈራጅ ነው። ሁሉም ሰው ይወደዋል ያከብረዋል። ባላባት ከሌለ ስርዓት የለም። ኑሮ፣ ህይወት የለም።* (ቃለ መጠይቅ፡ 10/06/06ዓ.ም) በማለት ብሄረሰቡ ለባላባት ያለውን ክብር ገልጸውልኛል።

ባላባቶችና የባላባት ወገኖች ከተራና ከዝቅተኛ ክፍሎችም ካሉት የማህበረሰቡ አካላት በተለያዩ ስርዓቶቻቸው ይለያያሉ። ከእነዚህ ልዩነቶች መካከል ቋንቋ፣ ምግብ እና አመጋገብ፣ ዘፈን እንዲሁም የቀብር ስርዓቶቻቸው ወ.ዘ.ተ ተጠቃሾች ናቸው።

ባላባቶች ከሌላው የማህበረሰቡ አካላት የሚለዩት ከላይ እንደተገለጸው በምግብ በኩል የሚታየው አንዱ ሲሆን ባላባቶችና ወገኖቻቸው በግ፣ ፍየል፣ ዶሮ፣ እንቁላል እንዲሁም ቆጮ አይመገቡም። የሚመገቡትም የከብት ስጋ ለዛውም ፍሪምባ፣ ታላቅና ታናሽ እና ሽንጥ ብቻ ናቸው። አቶ ሰንበት ቻሞ በቃለ መጠይቅ ወቅት እንደተናገሩት

*ባላባት ትንንሽ ነገር አይበላም። በግ፣ ፍየል፣ ዶሮ ስጋቸው ትንሽ ስለሆነ ለተራው ሰው ይተዋል። እነሱ ደግሞ ከተራው ሰው እኩል አይመገቡም። ከብት ትልቅ ስለሆነ ይበላሉ። ከከብቱም ቢሆን ታላቅና ታናሽ ነው። ይህን የሚያደርጉት ክብራቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ ከመሆኑም በተጨማሪ ባላባቱ ቆጮ፣ እንቁላልና ከላይ የቀረቡትን እንሰሳት ከበሉ ይታመማሉ ወይም ይሞታሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ነው።* (ቃለ መጠይቅ 11/06/06 ዓ.ም)

ባላባቶች የእህል ዘሮች ከበሰሉ ወዲያ ይመገባሉ። በጥሬው ግን ገብስ፣ ጤፍንና ስንዴን አይነኩም። ይህም ማለት እነዚህን የእህል ዘሮች ሳይበስሉ በእጃቸው አይነኩም። የመጠጫያና የመመገቢያ እቃዎቻቸውም ከሌላው የተለዩ ናቸው። ወ/ሮ ማርያሜ ኒያንግ

ስለ ባላባቱ ምግብና የአመጋገብ ሁኔታ እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፡፡ *"ባላባቱ ከቤተሰቡ ጋር አብሮ አይበላም፡፡ የሚመገበውም ለብቻው ነው፡፡ ምግቡ የሚቀርበውም በተለየ ዕቃ ነው፡፡ አንድ አንድ ጊዜ የቡና ቁርስ ሲቀርብ ለባላባቱ መጀመርያ ተቀንሶ ከተቀመጠ በኋላ ሌላው ሰው ይሠጣል፡፡ ይህ የሚሆነው ባላባቱን ለማክበር ነው፡፡"* (ቃለ መጠይቅ፡ 11/06/06)

በባላባቱ አቅራቢያና አጠገብ ሽክም ተሸክሞ ማለፍ አይቻልም፡፡ ከአጠገባቸውም መቀመጥ እንዲሁ ክልክል ነው፡፡ ባላባቶች አፈር አይነኩም፣ አያርሱም እንዲሁም ምንም አይነት ስራ አይሰሩም፡፡ በዘፈን በኩልም እንደ "ቦሲ"[2] ያሉትን አይጫወቱም፡፡ በሰርግ ጊዜ የባላባት ሲሆን በከበሮ ይታጀባል፡፡ ለሌላው ግን አይፈቀድም፡፡ ባላባት ወደ ተራው ሰው ቤት አይሄድም፡፡ ይህም የሚሆነው ባላባቱ ወደ ተራው ሰው ቤት ከሄደ እንደተዋረደ ተደርጎ ስለሚቆጠር ነው፡፡

በቋንቋና በቃላት ደረጃም ልዩነት አላቸው፡፡ ለምሳሌ ባላባቱ ይጠጣል ለማለት "ጫፍ ደጉ" ተብሎ የሚነገር ሲሆን ለተራው ሰው ግን "በይ ደጉ" ተብሎ ይነገራል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ባላባቱ ተኟቷል ብሎ ለማለት "ቾስኮ" የሚባል ሲሆን ለተራው ግን "ቦኪጎ" ይባላል፡፡ እነዚህ ቃላት ለባላባቱና ለባላባቱ ቤተሰቦች ብቻ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ለባላባቱ ያለውን ክብር ይገልጹበታል፡፡ ሌላው ሰው እነዚህን ቃላት ቢጠቀም ባላባቱን እንደናቀና እንዳዋረደ ተቆጥሮ ቅጣት ይጣልበታል፡፡

በባህሉ ማንኛውም ሰው ወደ ባላባቱ ቤት ሲሄድ ሰግዶ ይቀመጣል፡፡ ቀጥሎም በእምብርክክ ቁጢጥ ብሎ ይቀመጥና ያጨበጭባል፡፡ ባላባቱም የእጁን መዳፍ(ኩሙ)፣ ጉልበቱን፣ ቅልጥሙን (ቸልትን)፣ የእግሩን መዳፍ(ጊያሱ ቀያፊ) እያሳዩ እንደደረጃቸው እንዲስሙ ያደርጋል፡፡ ከዛም የሚፈልጉት ይደረግላቸዋል፡፡ ህዝቡም ያከብራቸዋል ፡፡ ይታዘዛቸዋል፡፡ ይህንን በማድረግ ለባላባቱ ያላቸውን ክብር ይገልጻሉ፡፡

ባላባቱም ለህዝቡ የሚያበረክታቸው ዋና ዋና ተግባራት አሉ፡፡ እነሱም አንደኛ ፀሃይ ሲበረታ (የዝናብ እጥረት ሲኖር) ዝናብ ማዝነብ፣ ሁለተኛ ዝናብ ሲበዛ (ያለወቅት ሲዘንብ) ዝናብ ማቆም፣ ሶስተኛ የአካባቢው ሰዎች ሲጋጩ ማስታረቅ፣ ለአካባቢው ደንብ ወይም ባህላዊ ስርዓት አልታዘዝ ያለን ሰው መቅጣት ወ.ዘ.ተ ባላባቱ የሚያከናውናቸው ግዴታዎች ናቸው፡፡

---

[2] ተቃራኒ ጾታዎች ጭናቸውን በቡጢ በመመታታት እና በመዝፈን የሚጫወቱት የፍቅር ጨዋታ ነው፡፡

## ምዕራፍ አራት፡ የዲዚ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በዲዚ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት አከዋወን ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ክፍል በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ እንዲሁም በቡድን ውይይት የተገኙ መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

ሞት በዲዚ ብሄረሰብ ዘንድ "ሹቡ" የሚል መጠርያ አለው፡፡ በብሄረሰቡም አንድ ሰው ሲሞት ወደ ፈጠረው አምላኩ ተመልሶ እንደሄደ ተደርጎ ይታመናል፡፡ ሟች አምላኩ በፈቀደለት ጊዜ ምድር ላይ ኖሮ መልካም ስራን ሰርቶ አምላክ ወዳዘጋጀለት ቦታ ሊወስደው ፈቀደ የሚል አስተሳሰብ አለ፡፡ አቶ ቸሬ አኮ እና ብሄረሰቡ ስለ ሞት ያለውን አስተሳሰብ እንዲህ በማለት ይገልጹታል፡፡

> *ሞት በዚህ ብሄረሰብ (በዲዚ) ዘንድ ስናየው ሟች ወደ ፈጠረው አምላክ በድጋሚ እንደመመለስ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ፈጣሪ ሲፈጥረን በዚህ አለም ላይ ኑሩ፣ ስሩ፣ ብሉ፣ ጠጡ ብሎ ነው፡፡ ከዛም ደግሞ ሰውየው ሲሞት በምድር ላይ ያለህ ህይወት ይበቃል ሲባል ነው፡፡ በርግጥ አንድ ሰው ሲሞት ወደ ፈጠረው አምላኩ ሲሄድ ማዘን የለብንም፡፡ ነገር ግን አብረነው የኖርነው፣ አብረን የበላነው የጠጣነው፣ ብዙ ነገር ያሳለፍነው ሰው እስከመጨረሻው ሲለየንና እንደማይመለስ ስናውቅ በጣም እናዝናለን (ቃለ መጠይቅ፡11/06/06) ፡፡*

ከላይ የቀረበው ሃሳብ ሞት ይህን አለም ትቶ ወደማይመለሱበት መሄድ እንዲሁም ከሚወዱት ተለይቶ መቅረት የሚል ትርጓሜ እንዳለው ያሳያል፡፡ አቶ ታደመ ኮሞሩት የሞትን ጽንሰ ሃሳብ ሲገልጹ *"ሞት ማለት ከዚህ አለም ላይ ፈጽሞ መለየት ማለት ነው፡፡ በአካልም በመንፈስም ማለት ነው፡፡ አምላካችን ሲፈጥረን በዚህ አለም ላይ የምንኖርበትን ጊዜ ወስኖ ነው፡፡ የምንሞተውም ይህ አለም ይበቃችኋል ሲል ነው፡፡ እሱ እንደፈጠረን እሱ ይወስደናል፡፡" ብለዋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፡12/06/06)*

በዲዚ ብሄረሰብ ለቅሶ “የብ” በመባል ይጠራል፡፡ በዚህ ስርዓት ላይ የሚከወኑ ክዋኔዎች የተለያዩ ትርጓሜዎችንና ትዕምርቶችን ያዘሉ ሲሆን ስርዓቱ የሚከናወነው የሟችን ማንነት ዕድሜ፣ ጾታና ማህበራዊ ደረጃ መሰረት በማድረግ ነው፡፡

የዲዚ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔን በአራት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡ የባላባት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ (ዳቡ)፣ የአዛውንቶች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ(ታል)፣ የጎልማሶች እና የወጣቶች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ (ያብ ባርዝ ሹቡ) እንዲሁም የሕፃናት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔዎች (ኩም) ናቸው፡፡

በዲዚዎች ዘንድ ሟች የሚሰጠው ቦታ ወይም ማህበራዊ ደረጃ ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ የለቅሶ ስርዓቱ ነው፡፡ ማህበራዊ ደረጃ ሟች በብሔረሰቡ ዘንድ ያለውን የስራ ድርሻ ይመለከታል፡፡ ስራውም የእምነት መሪ፣ የአካባቢ አስተዳዳሪና የሐገር ሽማግሌ ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ ሰው የስራ ድርሻው የአካባቢ አስተዳዳሪ ከሆነ የባላባት የለቅሶ ስርዓት “ዳቡ” ይደረግለታል፡፡

ሁለተኛው የመክፈያ መንገድ ደግሞ የሟች እድሜ ነው፡፡ ሟች በእርጅና ምክንያት ሲሞት/ስትሞት እንዲሁም የልጅ ልጆች ያፈራ/ራች እንደሆነ “ታል” የሚባለው የአዛውንቶች የለቅሶ ስርዓት የሚከናወንላቸው ሲሆን እነዚህ አዛውንቶች በአማካይ እድሜያቸው ከ70 ዓመት በላይ ይሆናል፡፡ የልጅ ልጅ ለማፍራት ያልደረሱ ነገር ግን ልጅና ትዳር ያላቸው ጎልማሶች እና ለአቅመ አዳምም ሆነ ለአቅመ ሔዋን የደረሱ ወጣቶች ሲሞቱ “ያብ ባርዝ ሹቡ” እንዲሁም ህጻናት ማለትም ዕድሜያቸው ከ(0-10) አመት ያላቸው ሲሞቱ ደግሞ የሕፃናት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ “ኩም” በማለት ይጠሩታል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት የለቅሶ አይነቶች እንደ ሟቹ አይነት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔያቸውም ይለያያል፡፡ የብሄረሰቡ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔዎች በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት በተሰበሰቡ መረጃዎች በተገኘው መሰረት ከዚህ በታች እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

### 4.1 የባላባቶች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ (ዳቡ)

የዲዚ ብሄረሰብ ለባላባቶች ካለው ከፍተኛ ክብር የተነሳ የለቅሶ ስርዓታቸውን እስካሁን ድረስ ሳይቀይር እና ሳያቋርጥና እየከወነው ይገኛል፡፡ ይህ የለቅሶ ስርዓት እንደየአካባቢው እና እንደ የባላባቶቹ የሚለያይ ሲሆን ይህ ልዩነት የሚታየው ደግሞ በስርዓተ ቀብር ወቅት ላይ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የለቅሶ ስርዓታቸው ከዚህ እንደሚከተለው የሚቀርብ ሲሆን ልዩነት የሚታይባቸው ስርዓቶችን የባላባት ማንነቶችን በመጥቀስ ከቅድመ ቀብር እስከ ድህረ ቀብር ያለውን ጊዜ በማሳየት ይሆናል፡፡

### 4.1.1 የኑዛዜ ስርዓት "ጋዚ"

በዲዚ ብሄረሰብ አንድ ባላባት ካልሞተ በስተቀር በላዩ ላይ ሌላ ባላባት አይወርስም ወይም አይቀየርም፡፡ ምክንያቱም ባላባት ክብር ነው፡፡ ምን አልባትም ባላባቱ እድሜው ሲገፋ ፣ የተለያዩ ስርዓቶችን (ደንቦችን) መፈጸም ሳይችል ሲቀር፣ በጠና ሲታመም እንዲሁም በባላባቱ ልጆች መካከል ጠብና ግጭት ተፈጥሮ መፍታት ሳይችል ሲቀር በማህበረሰቡ ዘንድ ባላባቱ መድከሙ ይረጋገጣል፡፡ በዚህ ጊዜም ባላባቱ ቤተዘመዶቹንና ደንብ ሰሪዎችን[3] ወይም "ዳንቢ ቀይዳዝ" በመጥራት የኑዛዜ ስርዓት ለመፈጸም መፈለጉን ይናገራል፡፡ ቀንም ይቆረጥለታል፡፡ የሚቆረጠው ቀን እንደባላባቱ የጤና ሁኔታ የሚወሰን ሲሆን ስርዓቱን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ነገሩችን ለማዘጋጀት የሚበቃ ጊዜ ግን ያስፈልጋል፡፡ ባላባቱ ደክሟልና ነገ ይሁን አይባልም፡፡

አቶ ታደመ ኮመሩት የኑዛዜ ስርዓት የሚፈጸምበት መንገድ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡ *"በባህላችን የኑዛዜ ስርዓት አለ፡፡ ባላባቱ የኑዛዜ ስርዓት በሚፈጽሙበት ጊዜ ትልቅ ድግስ ያዘጋጃሉ፡፡ ደንብ ሰሪው፣ ገይማው ሁሉ ይሰበሰባል፡፡ ዘመድ ሁሉ እንዲመጣ ያደርጋሉ፡፡ ሁለት ቀን ወይም ሶስት ቀን ሊቆዩ ይችላሉ፡፡ በኑዛዜው ስርዓት ወቅት ወራሹን ሊያስታውቅ ይችላል፡፡"* (*ቃለ መጠይቅ*፡ 11/06/06)

---

[3] ደንብ ሰሪዎች ከማህበረሰቡ የተለዩ እና የባላባቶቹ አገልጋይና ስርዓቶች የሚፈጽሙ ናቸው፡፡ እነዚህ የማህበረሰቡ አካላት ኮይዝገንዲ፣ ባልያብ፣ አይያብ፣ ቲያልም፣ ካርዝን፣ገይማ እና ሱላ ቤስን ተብለው በተለያዩ ስያሜዎች ይጠራሉ፡፡ በተለይ በለቅሶ ስርዓት ላይ ከፍተኛ ስርዓት የሚከውኑት ካርዘን የሚባሉት ደንብ ሰሪዎች ናቸው፡፡ ካርዘን ሰው ሲሞት የሚገንዝ፣ በውርስ ጊዜ በሚች ጆሮ ውስጥ ደምና ወተት የሚጨምር ፣የእዝን ቤት የሚጠርግ ፣የቀብር ጉድጓድ የሚጠቁም ናቸው፡፡ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስዱ ናቸው፡፡

ባላባቱ ለኑዛዜው ስርዓት ማስፈጸሚያ የሚሆን ከብት ያርዳል፣ በማህበረሰቡ ተወዳጅ የሆነውን መጠጥ ቦርዴ[4] እንዲሁም አምቾ[5] ማዘጋጀት ይጠበቅበታል፡፡ ትልቅ ድግስ መደገስ ግዴታው ነው፡፡ የቀጠሮው ቀን ሲደርስ የባላባቱ ቤተሰቦች እና ደንብ ሰሪዎች (አስፈጻሚዎች) ድግሱን ተካፍለው በልተው ጠጥተው ይጨርሳሉ፡፡ ግብዣው ከአንድ ቀን በላይ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዛም በባላባቱ አማካይነት እንዲሰበሰቡ ያደርጋል፡፡

በአብዛኛው ባላባቶች ኑዛዜያቸውን የሚያቀርቡት ስለ ውርስ ጉዳይ እንዲሁም ስለ አቀባበራቸው ጉዳይ መሆኑን አቶ ዘለቀ ገሩ እንዲህ በማለት ገልጸዋል፡፡

> *ባላባት ብዙ ጊዜ ኑዛዜ አያከናውንም፡፡ ቢያከናውንም ደግሞ ስለ ውርስ እና የአቀባበር ሁኔታ ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ባላባት የሚያወርሰው ነገር የለውም ቢኖረውም ያው ወራሽ የሚሆነው ተተኪ ባላባት ስለሆነ ነው፡፡ አሁን አሁን ግን በልጆች መካከል ግጭት እየተፈጠረ በመሆኑ ለወራሽ ባላባት ይበቃዋል የሚለውን ትቶ ለሌሎች ልጆቹ ማከፋፈል ጀምረዋል፡፡* (ቃለ መጠይቅ፡ 10/06/06)

የባላባት የውርስ (አልጋ ወራሽነት) ጉዳይ ደግሞ ባላባቱን፣ የባላባቱን ቤተሰብ እንዲሁም የቀበሌውን ኗሪ ሁሉ የሚመለከት ነው፡፡ ባላባቱ ይህ ልጄ ይውረስ ስላለ ብቻ ልጁ አይወርስም፡፡ ሁሉም ተሳታፊዎች ይሆናሉ፡፡ በአቀባባር ስርዓቱም ላይ እኔ ስሞት ብዙ ከብት አትረዱ ወይም እረዱ፣ በጆሮዬ ውስጥ ደምና ወተት አትጨምሩ ወይም እንደ

---

[4] ቦርዴ ከማሽላ፣ ከበቆሎ፣ ከበቀለ ማሽላ፣ ከገብስ ብቅል፣ከጠመጅ እና ከቀይ ጤፍ የሚዘጋጅ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ ስንዴ ይጨመርበታል፡፡ ከዚህ ከላይ የተጠቀሱት እህሎች ከተፈጩ በኋላ የቦርዴ እርሾ ተደርጎበት ተቦክቶ ለአንድ ቀን ይቀመጣል፡፡ የቦርዴ እርሾ የሚባለው በፊት ከተዘጋጀ ቦርዴ ተቀንሶ የተቀመጠ ነው፡፡ በማግስቱ የተቦካው በቆጮ ቅጠል እየታሰረ በትልቅ እንስራ ውስጥ ይቀቀላል፡፡ ይህም ረጅም ሰዓት ይወስዳል፡፡ በአብዛኛው ጠዋት ከተጣደ እስከ ማታ ድረስ መብሰል ይጠበቅበታል፡፡ ቀኑን ሙሉ ከበሰለ በኋላ በሰሌን ላይ ተደርጎ ይታሻል፡፡ ከዛም በውሀ ተበጥብጦ ይደፈደፋል፡፡ በሶስተኛው ቀን የስንዴ ወይም የገብስ ብቅል ተድረጎ በሞቀ ውሀ ከተበጠበጠ በኋላ በቆሳ(ቦርዴ ማጥለያ) ይጨመቃል፡፡ ከዛም ተመጠጥነት ይደርሳል፡፡ የብሄረሰቡ አባላትም ቦርዴን ዘወትር ለመጠጥነት ይጠቀማሉ፡፡

[5] ኡዱ(አምቾ) የሚዘጋጀው ከቆጮ ቂጥ(ጋጅ) ነው፡፡ ኡዱ የሚዘጋጀው የስንሰቱ ስር ተቆርጦ ከወጣ ከስር ያለውን ክፍል በማጣራት አራት መዓዘን ባለው ቅርጽ ተቆርጦ ነጩን ክፍል ብቻ በኬሙ(በማሰሮ) መቀቀል ነው፡፡ አምቾ ጥንካሬ ስላለው በደንብ ማገዶ ይፈልጋል፡፡ ይህ ምግብ በወንዶችም በሴቶችም ሊዘጋጅ ይችላል፡፡

አማራ ቅበሩኝ[6]፣ ቤተክርስቲያን ወስዳችሁ ቅበሩኝ የመሳሰሉት የሚሉ ኑዛዜዎች በብዛት የሚስተዋሉ ናቸው፡፡

ባላባቱ ያሰበውንና የሚፈልገውን ከተናገረ በኋላ ደንብ ሰሪዎች እና ቤተዘመዶች ይወያዩባቸዋል፡፡ ኑዛዜው ትክክለኛ እና ሁሉም የሚስማሙበት ከሆነ እሺ እንዳሰቡት ይሁንልዎ ብለው ከድግሱ የተረፈውን በልተው ጠጥተው ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ፡፡ ያልተስማሙበት ወይም ባላባቱ ሲሞቱ ችግር የሚፈጥር መስሎ ከታያቸው ደግሞ እንዲህ ቢሆን የሚሉትን ሃሳብ ያቀርባሉ፡፡ ሁሉም ከተስማሙ ለባላባቱ ረጅም እድሜ ተመኝተው ስርዓቱን ይፈጽማሉ፡፡

ከኑዛዜ በኋላ የባላባቱ የጤና መታወክ እየከፋ ሲሄድ ዝግጅት ይደረጋል፡፡ ለቀብር ማስፈጸሚያ የሚሆኑ ምግቦች ( ለቦርዴ ማዘጋጃ የሚሆን ብቅል፣ በሬ፣ የተለያዩ የእንስት ምግቦች፣ ኪጆ[7] ወ.ዘ.ተ) የሚዘጋጁ ሲሆን ለባላባቱም ከሁሉም ጊዜ የበለጠ ከፍተኛ እንክብካቤ ይደረግላቸዋል፡፡ እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውም ልጆች፣ የልጅ ልጆች፣ የባላባቱ ዘመዶች፣ ጎረቤቶች ናቸው፡፡ ጎረቤቶችም ሆኑ ልጆች ለባላባቱ ማስታመሚያ የሚሆን ከብት በማረድ ለባላባቱ ያላቸውን ክብር ይገልጻሉ፡፡

### 4.1.2 ከቀብር በፊት

በዲዚ ባህል መሰረት ባላባት ሲታመም ከሌላው ሰው እኩል “ታሚል” ተብሎ አይገለጽም፡፡ ሌሎች ታመዋል ለማለት “ጻብተጉን” የሚል ቃል የሚጠቀሙ ሲሆን ለባላባት ደግሞ “ቆዥደኮ” ይባላል፡፡ ባላባቱን “ጻብተጉን” ብሎ መናገር ማዋረድ በመሆኑ ይህንን ቃል የተጠቀመ ሰው በአካባቢው ፊት ይነሳል፡፡ ከፍ ካለም ይቀጣል፡፡ ባላባቱ ሲሞት እንዲሁ ለተራው ሰው የሚጠቀሙትን ቃል “ሸቦ” ማለት አይችሉም፡፡ በምትኩ

---

[6] በማህበረሰቡ ዘንድ የአማራ አቀባበር የሚባለው ሟች ከሞተ በኋላ በጨርቅ ተገንዞ እና በሳጥን ተደርጎ ቤተክርስቲያን የሚቀበረውን ነው፡፡

[7] ጢል(ኪጆ)፡- ከበቆሎ እሸት ወይም ከደረቀ ማሽላ የሚዘጋጅ ሲሆን ከበቆሎ እሸት የሚዘጋጀው የበቆሎውን እሸት በደንብ አልመው ከተነለቀጠ በኋላ በበቆሎ ቅጠል ጠቅልሎ በኬሙ (እንስራ) ውስጥ በመደርደር መቀቀል ነው፡፡ ከደረቀ ማሽላ የሚዘጋጀው ደግሞ ማሙ የሚባል የማሽላ አይነት ተለቅሞ ከተፈጨ በኋላ በውሀ ይቦካ እና በእንሰት ቅጠል በመጠቅለል በኬሙ ከተቀቀለ በኋላ በአጉቂዠስ(እርጎ) ይበላል፡፡

“ቻኖ” ይባላል እንጂ፡፡ በቃላቱ ፍቺ መካከል የትርጉም ልዩነት የሌለ ሲሆን ቃላቱ መጠርያ ልዩነት ከየት የመነጨ እንደሆነ አቶ ዘለቀ ገሩ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

> *ባላባቱ ሲታመሙም ሆነ ሲሞቱ እንደ ተራው ሰው “ሽቦ” እና “ጻብተጉን" ብሎ ማለት ባላባቱን መሳደብ ነው፡፡ ለባላባቱ ትልቅ ውርደት ነው፡፡ ያስገርፋል፡፡ ባላባቱ ስለሚከበሩ የምንጠቀመውም ቃል እነሱን የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡ ህዝቡም ስለሚያከብር ለሌላው ሰው የሚጠቀመውን ለባላባቱ አይጠቀምም፡፡* (ቃለ መጠይቅ፡ 11/06/06)

ባላባቱ እንደታመሙ ማንኛውም ሰው ወደ ቤታቸው በመሄድ “አባታችን እንደምን አድረዋል?” ብሎ መጠየቅ ይችላል፡፡ ባላባቱ “ቢሞቱም ደህና ናቸው”፣ “እንቅልፍ ላይ ናቸው” ተብሎ ይመለሳል፡፡ ባላባቱ ከሞቱ ከኂላ በቤት ውስጥ ያሉ “ኮይዝን”[8] የሚባሉ ሰዎች አስከሬኑን ያስተካክላሉ፡፡ አስከሬኑን ቀጥ አድርገው በጀርባው ካስተኙ በኂላ “ቱች” የተባለውን የባላባቱን ጸጉር ይላጯሉ፣ ጥፍሩን ይቆርጣሉ፡፡ ከዛም በበሬ ግምባር ቆዳ ጠቅልለው ያስቀምጣሉ፡፡ እጥበት አያከናውኑም፡፡ ከዛም “ገይግን”[9] የተባለ የእንሰት ቅጠል በእምብርቱ ላይ ያስቀምጣሉ፡፡ ይህም የሚሆነው እንሰት የተከበረ በመሆኑና ለሚቹ ጥሩ ነገር በመመኘት ነው፡፡ ከዚህ በኂላ ከብት ታርዶ በቆዳው እስኪጠቀለል ድረስ በአዲስ ኩታ (ጋቢ) ጠቅልለው “ቦልቴ” በሚባል በቤቱ ውስጥ ባለ ከፍ ወዳለ መቀመጫ (እንደ መደብ ያለ) ይቀመጣል፡፡

የባላባቱ መሞት ለሶስት ወይም ለአራት ቀናት በሚስጥር ለህዝቡ ሳይነገር ይጠበቃል፡፡ ይህም የሚሆነው ወራሹን ለማዘጋጀት ሲባል ነው፡፡ በዲዚ ባህል ልጅ ታላቅ ስለሆነ ብቻ አይወርስም፡፡ ብዙውን ጊዜ ሽማግሌዎች መክረውበት ይህ ሰው ያስተዳድረናል፣ ምትክ ይሆናል ብለው የሚያስቡትን ሰው “ቼርባርዝ” (አልጋ ወራሽ) ብለው ያቀርባሉ፡፡ የወራሹን አመራረጥ አስመልክቶ አቶ ታደመ ኮመሩት

> *በድሮ ጊዜ ወራሽን ማዘጋጀት የሁሉም ድርሻ ነበር፡፡ ባላባቱ ይህ ልጄ ይውረስ ቢልም የቀበሌው ሰው ካላተስማማበት ይቀራል፡፡ አሁን አሁን ግን ባላባቱን የደገፈ እና በርከት ያለ ከብት ወይም ሀብት ያለው ከሆነ ሊወርስ ይችላል፡፡ የባላባት ልጅ ይወርሳል የሚለው ግን ግድ የለውም ፡፡ ማንኛውም የባላባት ዘመድ የሆነ ሊወርስ ይችላል፡፡ ነገር ግን ከዘመዶችም*

[8] ባቡ፣ ላሊባብ እንዲሁም ኮይዝን የሚባሉት ሰዎች የባላባቱ አገልጋይና ባላባቱ ሲሞት ይህን ስርዓት የሚፈጽሙ ናቸው፡፡

[9] ገይግን የሚባለው ከእንሰት የሚገኝ ሲሆን ከአምቾ ዙርያ የሚገኝ ቅጠል ነው፡፡

*ሆኑ ከልጆቹ ቅድሚያ የሚሰጣቸው አሉ። በውሳኔው ውስጥ ግን ህብረተሰቡ ከፍተኛ ሚና አለው።* በማለት ገልጸዋል። (ቃለ መጠይቅ፡ 9/06/06)

ሟች ከመቀበሩ በፊት የሚከወኑ ዋና ዋና ጉዳዮች አሉ። እነሱም ውርስ፣ የአንጀት ማንበብ ስርዓት፣ የውሀ መርጨት ስርዓት ፣መርዶ፣ የአስከሬን ማቆያ ስፍራ ማዘጋጀት፣ አዲስ የለቅሶ ቤት ማዘጋጀት እንዲሁም የአስከሬን ሽኝት  ናቸው።

ከላይ የቀረቡት ክዋኔዎች እስከሚከናወኑ ድረስ አስከሬኑ በአስከሬን ማቆያ ቤት ይቆያል። ባላባት ሲሞት አስከሬኑ በመኖርያ ቤት ብዙ ቀን መቆየት ስለማይችል አዲስ ያስከሬን ማረፊያ ቤት ይዘጋጃል። ይህ ያስከሬን ማቆያ ስፍራ "ዲርሙ" ሲባል አስከሬኑ እስኪቀበር ድረስ የሚቀመጥበት ጎጆ ቤት ነው። ይህን ጎጆ ቤት የሚያዘጋጁት ገይማ የተባሉት የባላባቱ አገልጋዮች ሲሆኑ ቤቱም  አስከሬኑን ለማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን ደንብ ሰሪዎች እና የአስከሬኑ ጠባቂዎች እንዲቀመጡበት ሰፋ ተደርጎ ይሰራል።



ፎቶግራፍ 2 የአስከሬን ማረፊያ ቤት "ዲርሙ"

#### 4.1.2.1 ውርስ (ቄዝ)

ውርስ[10] በዲዚ ብሄረሰብ በተለይ የባላባት ውርስ ከተለመደው የውርስ ስርዓት የተለየ ሲሆን ብሄረሰቡ "ቄዝ" ብሎ የሚጠራው የባላባቱን የስልጣን ሽግግር (አልጋ ወራሽነት) ነው፡፡ ይህ ሽግግር ስልጣንን፣ ንብረትን፣ ህዝብን እንዲሁም ሚስቶችን ጨምሮ ለተተኪ ባላባት የሚተላለፍበት ስርዓት ነው፡፡ በዚህ የውርስ ስርዓት ውስጥ የንብረትም ሆነ የስልጣን ሽግግሩ ክፍፍል የሚታይበት አይደለም፡፡

አንድ ባላባት ከዚህ አለም በሞት ሲሰናበት በሱ ቦታ የሚተካው ወይም ወራሽ የሚሆነው የሟች ወንድ ልጅ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡ ይህ ወንድ ልጅ ታላቅ ወይም ታናሽ ሊሆን ይችላል፡፡ ለውርስ ስርዓቱ ማህበረሰቡ ያበጀው መስፈርት ያለ ሲሆን ወራሹ በጥንቃቄ ይመረጣል፡፡

ከመስፈርቶቹም መካከል አንደኛ ባላባቱ ከአንድ በላይ ሚስቶች ካሉት በመጀመርያ ከነክብረ ንጽህናዋ ያገባት ሴት የወለደችው የመጀመሪያ የወንድ ልጅ ካለ፣ ሁለተኛ ወራሹ በወተት ስርዓት "ኤጉ ባስ"[11] ጊዜ የእንገር ወተት የተመገበ ከሆነ፣ ሶስተኛ ሟች ባላባት በኑዛዜ እከሌ እኔን ይውረስ፣ የተለያዩ ደንቦችን ስፈጽም እኔን ይመለከት ነበር፣ ጎበዝና ጠንካራ ልጄ ነው ብሎ ያስተላለፈው እንደሆነ ነው፡፡ በክብረንጽህና የተወለደ ልጅ ከሌለ የመጀመርያው የወንድ ልጅ ወራሽ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ምን አልባት የመጀመርያው ልጅ እድሜው ገና ከሆነ ወይም ምግባረ ብልሹ ከሆነ የአካባቢው ሽማግሌዎች በመመካከር ባህሉን እና ስርዓቱን የሚያውቅና በአካባቢው ህብረተሰብ ተቀባይነት ያለውን የሟች ወንድም ካልሆነም የሟች የቅርብ ዘመድ (የባላባት ዘር) ይወርሳል እንጂ ከባላባት ዘር ውጪ መውረስ አይችልም፡፡

---

[10] ውርስ ብዬ የተጠቀምኩት በብሄረሰቡ ዘንድ ቄዝ የሚባለውን ስርዓት ለመወከል ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ብሄረሰብ ውርስ ከአማርኛ ቋንቋና ፍችው ጋር ተያይዞ የሚነሳውን የሟችን የንብረትና የስልጣን ክፍፍሎሽን የሚያመለክት አይደለም፡፡

[11] "ኤጉ ባስ" የወተት ስርዓት በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ ስርዓት ከብት ስትወልድ የሚፈጸም ነው፡፡ በባህሉ ደንብ ሳይሰራ ወተቱን መጠጣት አይቻልም፡፡ ለስርዓቱ ሲባል በትንሽ ቅል ውስጥ ወተቱ እየታለበ ይቀመጣል፡፡ ይህ ቅል ሲሞላ በሌላ ቅል ላይ ይታለባል፡፡ ሁለተኛው ቅል "ባርከን/ባቱ" በመባል ይታወቃል፡፡ የወተት ስርዓቱን የሚፈጽመው ብዙውን ጊዜ የቤቱ አባወራ ነው፡፡ ስርዓቱ የሚፈጸመው ጧት ወይም ማታ ሊሆን ይችላል፡፡ በደምብ ቅል ውስጥ የተቀመጠውን ወተት ደንብ በሚሰራበት ቦታ ላይ ምስጋና በማድረስ የወተት ቁርባን ያቀርባል፡፡ "ሙይ" ወይም ጋጣውን እንደ ሰማይ ኮከቦች ከብቶች ይሙሉ እያለ በመመረቅ ወተቱን በጥቂቱ በደንብ መስርያው ላይ ያፈሳል፡፡ (ለደንብ ስርዓት በተመረጠው ቦታ ) ከስርዓቱ የተረፈውን ወተት ለመጀመርያ ወንድ ልጅ (ወራሽ ይሆናል ተብሎ ለሚታሰብ ልጅ) ይሠጠዋል፡፡ እሱም ለማንም ሳያካፍል ይጠጣል፡፡ የሚጠጣበት እቃም "ኒያሉ ኮፍ" በማለት ይጠራል፡፡ "ኒያሉ" ማለት እንገር ማለት ነው፡፡ በሌላ ቅል የታለበውን ወተት የቤተሰቡ አባላት፣ ዘመዶችና ጎረቤቶች ይጠጣሉ፡፡ ጠጥተውም ሲያገሱ በሬ ትውለድ፣ ሌላ ጥጃ ደግም ትውለድ በማለት ላሚቱን ይመርቋታል፡፡ በባህሉ የወተት ስርዓቱ ካላተፈጸመ ወተት መጠጣት አይቻልም ነበር፡፡ አሁን አሁን ግን እየቀረ መጥቷል፡፡

በባላባቱ ስርዓት ላይ ሴት ልጅ መውረስ አትችልም፡፡ ይህም የሆነበትን ምክንያት አቶ ዘለቀ ገሩ እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፡፡

*በባላባቱ የውርስ ስርዓት ላይ ሴት አትወርስም፡፡ ምክንያቱም ይህ ከቀደምት አባቶቻችን የወረስነው ነው፡፡ በሌላው ግን ሴት መውረስ ትችላለች፡፡ የባላባቱ የተለያዩ ደንቦችንና ስለሚፈጽሙና ከፍተኛ ሃላፊነት ስለሚኖርባቸው እና ጫና ስለሚበዛባቸው ወንዶች ወራሽ ይሆናሉ፡፡ ሴቶች ደግሞ ወንዶቹን የሚደግፉ ናቸው* (ቃለ መጠይቅ 10/06/06) ፡፡

ይህ የውርስ ስርዓት የተለያዩ ክዋኔዎችን ያልፋል፡፡ ይህ ስርዓት ደግሞ የውርስ ደንብ ይባላል፡፡

### 4.1.2.2 የውርስ ደንብ

የአንድ ባላባት ውርስ ሲከናወን ከፍተኛ ስርዓት (ደንብ) ይፈጸምለታል፡፡ ይህን ደንብ የሚያስፈጽሙት ደንብ ሰሪዎች “ገይማ” የተባሉት የማህበረሰቡ አካላት ናቸው፡፡ የውርስ ስርዓቱ የሚጀምረው ሟች ከሞተ በኋላ ነው፡፡ ሟች የመረጠው ወራሽ ካለ ህዝቡ ወይም ሽማግሌዎቹ እንዲወያዩበት ይደረጋል፡፡ የሟች ህይወት ማለፍ ለሁሉም ህዝብ በይፋ አይነገርም፡፡ በአካባቢው ላሉ ሽማግሌዎች እና ደንብ ሰሪዎች ብቻ ይነገራቸዋል፡፡ ይህም የውርስ ስርዓቱን እንዲያስፈጽሙ ነው፡፡ ሽማግሌዎች ከተሰበሰቡ በኋላ በሰፊው እንዲወያዩ ይደረጋል፡፡ ስለ ውርሱ ጉዳይ ሁሉም ያሰበው መናገር ይቻላል፡፡ በዚህ ወቅት የተለያዩ ሃሳቦች ሊነሱ ይችላሉ፡፡ ሽማግሌዎቹ በአንድ ሃሳብ እስኪስማሙ ድረስ ውይይቱ የሚቀጥል ይሆናል፡፡ በውይይቱ ወቅት ሴቶች አይሳተፉም፡፡ ሴቶች የማይሳተፉበት ምክንያት በውርስ ስርዓተ ክዋኔው የሚኪያሄደው በወንዶች እንደሆነና የሴቶች ሚና ለውርስ ስርዓቱ ማከናወኛ የሚሆኑ ምግቦችን ማዘጋጀት እንደሆነ በቡድን ውይይት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡



ፎቶግራፍ 3 ሽማግሌዎች ወራሹን ለመመምረጥ ውይይት ሲያደርጉ

ሽማግሌዎች በወራሹ ላይ ከተስማሙ በኋላ ውርሱ የሚከናወንበት (ደንብ የሚሰራበት) ቦታ ይመረጣል፡፡ ይህ ስርዓት በማንኛውም ቦታ አይከናወንም፡፡ ለብቻው የተከለለ ስፍራ አለው፡፡ በዚህ ስፍራ ሽማግሌዎች፣ ደንብ ሰሪዎች፣ የባላባት ቤተሰቦች፣ እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላት ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በኋላ በደንብ ሰሪው "ገይማ" አማካይነት ወራሽ ከወገቡ በላይ ያለውን ልብስ እንዲያወልቅ ይደረጋል፡፡ በመቀጠልም በወገቡ ዙርያ እንዲሁም በትከሻው ላይ የእንሰት ቅጠል እንዲያስር ይደረጋል፡፡ ጦርም በእጁ እንዲይዝ ይደረጋል፡፡ የባላባት ወገኖች ሁሌም ጦር ይይዛሉ፡፡ የጀግንነትና የባላባት ወገን መሆናቸውን የሚገልጹበት መንገድ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው እንሰት በማህበረሰቡ ከፍተኛ የሆነ ክብር ያለው በመሆኑ ለስርዓቱ ማስኬጃ እንደተመረጠ በቡድን ውይይት ወቅት ለመረዳት ችያለሁ፡፡

ወራሹ ከተዘጋጀ በኋላ ትንሽ ጎድጓዳ ስፍራ በመፈለግ ወይም በማዘጋጀት ዙርያውን የእንሰት ቅጠል ያለብሱታል፡፡ ወራሹም በእዚህ ላይ እንዲቆም ይደረጋል፡፡ በመቀጠል ገይማው በእግሩ ላይ ውሃ ያፈሳል፡፡ የዚህ ክዋኔም ትርጉም በወራሹ ዘመን አካባቢው እንዲለመልም፣ እርጥብ እንዲሁም ሰላም እንዲሆን በመመኘት ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ለደንብ መስርያው የተዘጋጀው ፍየል በወራሹ አማካይነት እንዲታረድ ይደረጋል፡፡ ለደንብ መስርያው የምትዘጋጀው ፍየል ሴት ስትሆን የምትታረደው በቢለዋ ሳይሆን ወራሹ በያዘው ጦር ነው፡፡ በጦር የሚታረድበት ምክንያት ደግሞ ከተለመደው እርድ የተለየ በመሆኑ ነው፡፡ በመቀጠል የታረደው ፍየል ደሙ እየፈሰሰ ወራሽ በጭንቅላቱ

እዲሽከም እና በደም የመታጠብ  የመንጻት ስርዓት እንዲፈጽም ይደረጋል፡፡ ይህም የወራሹ ልብ ንጹህ እንዲሆን እንዲሁም ሰላማዊ አስተዳደር እንዲገጥመው ታስቦ መሆኑን አቶ ታደመ ኮሞሩት በቃለ መጠይቅ ጊዜ ገልጸዋል፡፡



ፎቶግራፍ 4 ለውርስ ደንብ በታረደው ፍየል ደም ወራሹ ሲታጠብ

ይህ ስርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ የፍየሉ አንጀት እንዲነበብ ይደረጋል፡፡ አንጀቱ ተነቦ ወራሽነቱ  እስኪረጋገጥ ድረስ በእንሰት ቅጠሉ ላይ እንዲቆም ይደረጋል፡፡

### 4.1.2.3 የአንጀት ማንበብ ስርዓት "ኢብ-ጋብስ"

ወራሽ ባላባትም ሆነ አስወራሽ (ደንብ ሰሪዎች) ወደ ተግባር ከመግባታቸው በፊት ደንብ "ኢብ-ጋብስ" ይሰራላቸዋል፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ የቀድሞ ባላባት በህይወት እያለ ለአስወራሾች አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት አድርጎ  የማወራረስ ስርዓት ያላከናወነ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ አንዳንድ ባላባቶች ስርዓቱን ከመሞታቸው በፊት ያከናውናሉ፡፡ ይህ ግን በአብዛኛው የተለመደ አይደለም፡፡

የታረደው ከብት አንጀት በጥንቃቄ በተዘጋጀለት የተለየ ማስቀመጫ "ፀንዲ"[12] ተደርጎ በአዋቂዎች ይነበባል፡፡ በአንጀት ማንበብ ስርዓቱ ወቅት አንጀት አንባቢዎች "ይን-

[12] ፀንዲ ከሃረግ ተጠላልፎ በጌሾ እንጨት እንደ ቅርጫት ስራ ተሰርቶ በዝርግ ቅርጽ ተደርጎ በክብ መልክ ይሰራል፡፡ በአብዛኛው እህል ለማበጠርያ፣ ለመመገቢያ እንዲሁም ለቆሻሻ መጣያ ያገለግላል፡፡ ለአንጀት ማንበበቢያ የሚያገለግለው ፀንዲ በስፋቱ ከፍ ያለ ሲሆን በተለይ በአንጀት አንባቢዎች፣ ባላባቶችና ደንብ ሰሪዎች ቤት አይጠፋም፡፡

ጊያዱ"[13] ወራሽ መውረስ እንደሚችልና እንደማይችል፣ የዝናብ ሁኔታን፣ የአዝመራ(የምርት ሁኔታ)፣ ቀጣይ ዘመን ጥጋብ ወይም ርሀብ እንደሆነ፣ ጦርነት ካለ የትና መቼ እንደሚከሰት፣ በቤተሰብ መካከል የሚከሰት ችግር (ሞት) ካለ፣ ወራሽ ምን ያህል አመት እንደሚኖር(እንደሚገዛ) ወ.ዘ.ተ የሚመለከቷቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡



ፎቶ ግራፍ 5 አንጀት ማንበብ ስርዓት

በባላባቱ የለቅሶ ስርዓቱ ላይ የአንጀት ማንበብ ስርዓቱ  የሚከናወነው የወራሹን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እንደሆነ አቶ ባልኩ ይገልጻሉ፡፡

> *አንጀት የሚነበበው እኛን የሚያስተዳድረውን ባላባት መውረሱን አምልካችን መፍቀድ አለመፍቀዱን ለማወቅ ነው፡፡ አንጀቱ ፈቀደ ማለት ወራሹን አምላክ ፈቅዷል ማለት ነው፡፡ አንጀቱ ባይነበብ ደግሞ እሱ ያልፈቀደው ነገር ስለሆነ በሃገራችን፣ በህዝቡ ላይ ችግር ይፈጠራል፡፡  ይህ ደግሞ ከአያት ቅድመ አያቶቻችን የወረስነው ስርዓት በመሆኑ  አንድ ባላባት ሲሞት አንጀት ይነበባል፡፡ ባላባቱ አንጀት ሳይነበብ የወረሰ እንደሆነ ጥሩ አይሆንም፡፡* (ቃለ መጠይቅ፡ 10/06/06)

አንጀቱ ከተነበበ እና ወራሽነቱ ከተረጋገጠ በኋላ ለደንብ ማከናወኛ የታረደው የፍየል ቆዳ በወራሹ ጭንቅላት ላይ ይታሰራል፡፡ ይህም ወራሽነቱን የሚያመለክት ነው፡፡

---

[13] አንጀት አንባቢዎች የተለየ ስጦታ ያላቸው እና የተከበሩ ሰዎች ናቸው፡፡ በተለያዩ ስርዓቶች ላይ ይህን ስርዓት ይፈጽማሉ፡፡ በማህበራዊ ግንኙነቶች ላይ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ በዚህ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች የተለየ ሙያ እንዳላቸው ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ይህንንም ሙያ ያገኙት ከቀደምት አባቶቻቸው ነው፡፡

በተጨማሪም ቆዳው ቀበቶ በሚመስል ቅርጽ ተሰርቶ በወገቡ ላይ የሚታሰር ሲሆን በቀጭኑ ተቆርጦ ደግሞ በቀኝ እጁ ላይ ይታሰርለታል፡፡ በቀኝ እጅ ላይ የሚታሰረው የወራሽነት ምልክት ሲሆን ከዚህ በኋላ አምባር እንዲያስር ይደረጋል፡፡ ሰዎች ይህን በማየት ባላባትነቱን የሚለዩበት መንገድም ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

ከዚህ በመቀጠል ከማሽላ "ማሙ" የተሰራ ሙቅ በሾርቃ[14] ተደርጎ ይቀርባል፡፡ ማሽላ የተመረጠበትን ምክኒያት አስመልክቶ አቶ ባልኩ ኩሙ በቃለ መጠይቅ ጊዜ እንደገለጹት *"ማሽላ የታወቀው እዚህ ማጂ ላይ ነው፡፡ ህዝቡ በብዛት ያመርተዋል፡፡ አባቶቻችን የማሽላ ሙቅ ይጠቀሙ ነበር፡፡ እኛም እናደርገዋለን፡፡"* (ቃለ መጠይቅ፡ 11/06/06) የማሽላው ሙቅ የውርስ ስርዓቱን ለታደሙት ሁሉ ትንንሽ የእንሰት ቅጠል ቁራጮች በገይማው አማካይነት ይሰጣቸውና ወራሹን በማስቀደም በቅጠሉ ላይ ትንሽ ትንሽ ይደረግላቸዋል፡፡ በመጀመርያም ወራሽ ቀምሶ ይተፋል፡፡ ከዛም በመቀጠል ሁሉም አንድ ጊዜ ቀምሰው ይተፉትና ቀሪውን ይጥሉታል፡፡ የዚህ ስርዓት ትርጉም ሃገራችን ለምለም እንዲሁም በረከት ይሁን ብሎ ለመመረቅ እንደሆነ አቶ ዘለቀ ገሩ በቃለ መጠይቅ ወቅት ገልጸዋል፡፡



ፎቶግራፍ 6 ወራሽ ለውርስ ደንብ የተዘጋጀውን የማሽላ ሙቅ ለመቅመስ ሲዘጋጅ

በዲዚ ባህል መሰረት የባላባት ውርስ በሁለት መንገድ ይከናወናል፡፡ የመጀመርያው የውርስ ስርዓት ባላባቱ ከሞተ በአራተኛው ቀን ድንብ ተሰርቶ የባላባቱ ጥፍር "ሽሽም" እና

[14] ሾርቃ ከድፍን ቅል የሚዘጋጅ የመጠጥ ማቅረቢያ ቁስ ሲሆን ቅሉ በግማሽ ተቆርጦ ፍሬው ከወጣ በኋላ ታጥቦ ለመጠጫነት ያገለግላል፡፡ በአብዛኛው ለቦርዴ መጠጫነት ያገለግላል፡፡

ጸጉር "ቱች"[15] ይቆረጥና አንጀት ለማንበብ በታረደው ፍየል ወይም በሬ ጭንቅላት ቆዳ ተጠቅልሎ ይቀመጣል፡፡ በመቀጠልም አስከሬኑ በመቀበርያው ቦታ ይቀበራል፡፡

አስከሬኑ ከተቀበረ በኋላ ለውርሱ ስርዓት ማከናወኛ በቂ መሰናዶ ይደረጋል፡፡ ሀገሬው ለውርሱ ከየቤቱ እህል በማዋጣት ቦርዴ ይጠመቃል፡፡ የወራሹ አጥርና ጊቢ ይታደሳል፡፡ አዲስም ይሰራል፡፡ በነዚህ ቀናትም ወራሹ ምርጥ ምርጥ ምግቦችን ተመግቦ ግርማ ሞገስና ውበት እንዲያወጣ ይቀለባል፡፡

የውርሱ ቀን ጥሪ የተደረገላቸው ሰዎችና አቻ ባላባቶች ይሰበሰባሉ፡፡ ለአራት ቀናት እየበሉ እየጠጡ ይቆያሉ፡፡ በበሬ ጭንቅላት ቆዳ ተጠቅልሎ የተቀመጠው የሟች ባላባት ጥፍርና ጸጉር ወደ ቀብር ስፍራ ከመወሰዱ በፊት በሬ ታርዶ አንጀት ይነበባል፡፡ አንጀቱ ትክክል ከሆነ ስጋው ይቀቀልና ስጋውን ይበሉታል፡፡ የተበላው ስጋ አጥንቱ ይሰበሰባል ፡፡ በአራተኛው ቀን የባላባቱ ሞት በይፋ ሲነገር ይህ አጥንት ይበተናል፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ተለቅሶ የተገነዘው የሟች ባላባት ጥፍርና ጸጉር ተወስዶ ይቀበራል ወራሹም የአባቱን ስም ወርሶ ቀየውን ማስተዳደር ይጀምራል፡፡ የሟችን ሁሉንም ነገር ይወርሳል፡፡ ከእናቱ በስተቀር ሁሉንም የአባቱን ሚስቶች ሚስት ማድረግ ይችላል፡፡

ሁለተኛው የውርስ ስርዓት የሚከወነው የባላባቱ መሞት ተደብቆ ለአራት ቀናት ከቆየ በኋላ ወራሽ ተፈልጎ ነው፡፡ የቀኑን ብዛት የሚወስነው የውርሱ ስርዓት ነው፡፡ ወራሹም እንደታወቀ ሬሳው ለተጨማሪ አራት ቀናት ጸጉሩም ሆነ ጥፍሩ ሳይቆረጥ ይቀመጣል፡፡ የባላባቱ መሞት በይፋ ከመነገሩ በፊት ደንብ ይሰራል፡፡ "አርድ-ቃዥ"[16] የተባለ በሬ ይታረድና አንጀቱ በአዋቂዎች ይነበባል፡፡ መውረሱ ከታወቀ የበሬው ስጋ ተቀቅሎ ይበላና አጥንቱ እስከ መርዶው ድረስ ይሰበሰብና ይቀመጣል፡፡ በአራተኛው ቀን ባላባቱ መሞቱ ያነገራል፡፡ በዚህ ሰዓት አጥንቱ ተበትኖ መሪር ሃዘን ይሆናል፡፡

በስምንተኛው ቀን ደንብ ተደርጎ ሬሳው ከተሸኘና ከተቀበረ በኋላ የአባቱን ወይም የባላባቱን ስምና ስልጣን ውርሶ የአካባቢው ባላባት ሆኖ ያስተዳድራል፡፡ ማንኛውም ባላባት ሲወርስ አዲስ ሚስት ክብር ያላት "ኤጄል ኸሪ" ማግባት ይኖርበታል፡፡ ሌሎቹንም የአባቱን ሚስቶች ከወላጅ እናቱ በስተቀር ወርሶ ሚስቶቹ ያደርጋል፡፡ የውርስ ስርዓቱ

---

[15] የባላባት ወገን ከመሃል አናቱ ሳይቆረጥ የሚያሳድገው ጸጉር

[16] ለደንብ ስርዓቱ ማስፈጸሚያ የሚታረድ (መስዋዕት የሚቀርብ) በሬ ነው፡፡

ከተከናወነ ከኋላ ወራሽ አዲስ የተበሳ ቅል ይይዛል። በዚህም ውሀ ይቀዳል። ውሃውም በእግሩ ስር ይፈሳል። ሽማግሌዎቹም "ባንተ ጊዜ ሃገራችን እርጥብ ይሁን" ብለው ይመርቁታል። ይህ የውርስ ስርዓት ከተከናወነ በኋላ የሚቀጥለው ስርዓት የውሃ መርጨት ስርዓቱ ነው።

### 4.1.2.3. የውሀ መርጨት ስርዓት (ቼድ)

ይህ ስርዓት ከላይ የቀረቡት የውርስ ደንቦች ተከናውነው ካለቁና ወራሹ ከተገኘ በኋላ የሚከወን ነው። በአዲስ ቅል ውስጥ የተዘጋጀ ውሃ በቆጮ ላይ ኮባ ላይ በመጨመር አስከሬኑ ያለበትን ቤትና የጭፈራ ቦታ ፣ አካባቢውን በሙሉ እንዲሁም ለለቅሶ የታደሙትን ሰዎች በተደጋጋሚ ይረጫሉ። ይህ የውሃ መርጨት ስርዓት የሚከናወነው አዲስ ባላባት መተካቱን ለማመልከት፣ የአዲሱ ባላባት ዘመን እርጥብ ፣ ለምለም፣ አረንጓዴና ሰላም እንዲሆን ለመመኘት፣ በሽታና ችግር እንዲጠፋ ለማድረግ እንደሆነ በቡድን ውይይት ጊዜ ለማወቅ ተችሏል። ይህ ስርዓት በውሃ የሚፈጸምበትን ምክንያት አቶ ባልኩ ኩሙ *" ውሀ የሁሉ ነገር መድሀኒት ነው። ንጹሁ ነገር ነው። የቆሸሸ ነገር ያጸዳል። በሽታ ያጠፋል። እኛም የምንጠቀመው በአካባቢያችን የመጣውን ሞት ለማጥፋት እና ለማራቅ ነው። ሁሉ ነገር መልካም የሚሆነው ውሃ ሲኖር ነው።"* ( ቃለ መጠይቅ:11/06/06)



ፎቶግራፍ 7 የውሃ መርጨት ስርዓት

እነዚህ ከላይ የቀረቡት ስርዓቶች ከተከናወኑ በኋላ የባላባቱ ሞት ይፋ እንዲደረግ ይሆናል፡፡ መርዶ “ዱፉ ኮርክን” ይነገራል፡፡

በዲዚ ባህል መሰረት ባላባት የሞተ ቀን ቢታወቅም በይፋ ከመናገር ይልቅ በሚስጢር ለመያዝ ይሞከራል እንጂ ሞተዋል ተብሎ ወዲያው አይነገርም፡፡ ባላባቱ ከሞቱ ወራሾቹ እስኪለዩ እና ዝግጅት እስኪጠናቀቅ ድረስ ታመዋል በሚል ሽፋን ረዘም ላለ ጊዜ ይቆያሉ፡፡

የመርዶው ቀን ሟች በሞተ በአራተኛው ቀን ወይም በስምንተኛው የሚሆን ነው፡፡ የመርዶውን ቀን ልዩነት የሚወስኑት ነገሮች ከውርስ እና ከባላባቱ አስከሬን ሽኝት ጋር ተያይዞ በሚነሱ ነገሮች ነው፡፡ በአራተኛው ቀን መርዶ የሚሆንበት ምክንያት ሟች የሞተው ምርት በተሰበሰበበት፣ ቤተሰቦቹ እና ወራሹ በተገኙበት ወቅት ያረፈ እንደሆነ ከሆነ ሲሆን ባላባቱ ምርት ባልተሰበሰበበት ፣ በርሃብ  እንዲሁም ወራሹ ባልተዘጋጀበት ወቅት ከሆነ ደግሞ መርዶው በስምንተኛው ቀን ነው፡፡ በዚህ ወቅት የባላባቱ ጥፍርና ጸጉር ተቆርጦ በበሬ ግንባር በተገፈፈ ቆዳ ተጠቅልሎ ሲቀር አስከሬኑ ይቀበራል፡፡ በአብዛኛው ግን በአራተኛው ቀን የሚቀበር ነው፡፡ አራቱን ቀናት በሙሉ ሬሳው “አይትባቼ” በከብት ቆዳ ተሸፍኖ ይቆያል፡፡

በአራተኛው ቀን የባላባቱ ሞት ሊነገር ሲታሰብ እንድ የተቀጠቀጠ በሬ “ኦርዱ ቅኧ” ታርዶ በአዋቂዎች አንጀት ይነበባል፡፡ አንጀቱ ከመራና ሁሉም ነገር ትክክል ከሆነ ስጋው ይቀቀላል፡፡ አንጀቱ ካልመራ ግን ስጋው ይጣላል፡፡ አንጀቱ እስኪመራ ድረስ ከብት ይታረዳል፡፡ አንጀቱ የመራው ከብት ስጋ ተቀቅሎ በዚህ ስርዓት ላይ ለተገኙት ሰዎች ይሠጣል፡፡ ሰዎቹ ስጋውን በልተው ይጨርሳሉ፡፡ ስጋውን የሚበሉት ፈጣሪ የውርስ ስርዓቱን ተቀብሎታል፣ ሰላም ሆኗል በማለት ነው፡፡ ስጋው ተበልቶ እንዳለቀ የተበላው ስጋ አጥንት ተሰብስቦ በእጅ ይያዛል፡፡

በመርዶው ሰዓት በሽተኛውን ባላባት የሚጠይቁ ሰዎች ከቤት በስተጀርባ ሆነው አባታችን በጎ ናቸው? ብለው ሶስት ጊዜ አከታትለው ይጠይቃሉ፡፡ ከቤት ውስጥ ያለው የባላባቱ አስከሬን ጠባቂ “ቤስን ገይማ” ሶስት ጊዜ በጎ ናቸው የሚል ምላሽ ከሰጠ በኋላ በአራተኛው ከዚህ አለም ተሰናብተውናል የሚል ምላሽ በሚሰጥበት ጊዜ አጥንቱን በእጃቸው የያዙ ሰዎች የያዙትን አጥንት ይበትናሉ፡፡

ከዚህ በኋላ ቃጭሉም፣ ከበሮም ጡርምባም ይጮሃል፡፡ በዚህም በይፋ የአካባቢው ነዋሪ የባላባቱን መሞት እንዲሰማ ይደረጋል፡፡ ለታላላቅ እና ለታናናሽ ባላባቶች እንዲሁም ለሀገሬው ህዝብ በሙሉ የሀዘን መልዕክት ይላካል፡፡

መርዶው ከተነገረ በኋላ በአካባቢው በጀግንነት የሚታወቁ የባላባት ዘሮች ወደ ደን ውስጥ ገብተው የዋንዛ እንጨት ወግተው ይመለሳሉ፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት የባላባቱን እና የአካባቢውን ጀግንነት ለመግለጽ ሲባል መሆኑን አቶ ታደመ ኮመሩት ገልጸዋል፡፡

> *የባላባቱ ወንድሞች እና ጀግኖች ዋንዛ ወግተው፣ ጦራቸውን እየሰበ እና መሳርያ እየተኮሱ ወደ ለቅሶው ቦታ ይመጣሉ፡፡ ዋንዛ የሚሰበቀው ባላባቱ ጀግና የጀግና ዘር መሆኑን ለመናገር ነው፡፡ አባቴ እንደነገረኝ ከሆነ ከዚህ ቀደም ይህ ስርዓት የሚከወነው ሰው በመውጋት ወይም በመግደል እንደሆነ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ጎጂ ባህል በመሆኑ ቀርቷል ፡፡ አሁን አይደረግም፡፡ በሰው ፋንታ ዋንዛ ሆኗል፡፡ የዋንዛ እንጨት የተመረጠበት ምክንያት ዋንዛ እንደ ሰው ስለሚቆጠር ነው፡፡ የዋንዛ እንጨት በዲዚ ባህል መሰረት አይቆረጥም፡፡ አንድ የዋንዛ እንጨት የቆረጠ አንድ ሰው እንደገለ ይቆጠራል ( ቃለ መጠይቅ፡10/06/06)፡፡*

ለቀስተኛው ሁሉ ይሰበሰባል ሁሉም የቻለውን ያህል ይዞ ይመጣል፡፡ የባላባት ወገኖች ከብቶች ያመጣሉ፡፡ ሌሎች ሰዎች ደግሞ ባላባቱን የሚያስታውሱ ጦር፣ ጋሻ፣ ከበሮ፣ ጡርምባ፣ በእግር ላይ የሚታሰር ቃጭል እንዲሁም ሴቶች ደግሞ ለንፍሮ የሚሆን እሸት ይዘው ይመጣሉ፡፡ ወንድ የሟች ባላባት ዘመዶች ፊታቸውን ከሰል እና ኖራ በማደባለቅ ተቀብተው የሚመጡ ሲሆን ሴቶች ደግሞ ነጠላቸውን በወገባቸው ላይ ያስራሉ፡፡ ይህም የሃዘን ምልክት በመሆኑ ነው፡፡ በአካባቢው በጠቅላላ ሀዘን ይሆናል፡፡ በዕለቱ እርሻ አይታረስም፣ ከብትም ቃጭል አታጠልቅም፡፡ ምንም አይነት ስራም አይሰራም፡፡ በዚህ ቀን ማንም ሰው ቤቱ አይቀመጥም፡፡ አቶ ቸሬ አኮ የመርዶውን ቀን አስመልክቶ እንደገለጹት፡-

> *ባላባት የሞተ ቀን ሁሉም ለቅሶ ይሄዳል፡፡ ልጆችም ሆኑ ሽማግሌዎች አይቀሩም፡፡ ቢቀሩ እንኳን አቅም ያነሳቸው ሽማግሌዎች፣ አራስ የሆነች እናት እና ህጻናት ናቸው፡፡ በዚህ ቀን የቀረ ከማህበራዊ ጉዳዮች ይገለላል፡፡ በባላባቱ ቀብር የቀረ ለሱ ማንም አይሔድለት፡፡ ማን ይቀብረዋል?፡፡ ባላባት ሲሞት እንኳን ተራው ሰው አቻ ባላባቶች እንዲሁም ታላቅ*

*ባላባቶች ይገኛሉ፡፡ በእለቱ ላልተገኘ ሰው ቢታመም የሚጠይቀው አይኖርም፡፡ መልዕክት እንኳን ቢፈልግ ማንም አይላከውም፡፡ ለባላባቱ ለቅሶ ያልሄደ ተብሎ ይሰደባል (ቃለ መጠይቅ፡ 11/06/06)፡፡*

አቶ ቸሬ እንደገለጹት በባላባቱ ለቅሶ ማንም መቅረት አይችልም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቀብሩ ስርዓት ወቅት አቻ ወይም ታላቅ ባላባቶች ካልተገኙ ስርዓቱ አይፈጸምም፡፡ ምን አልባትም በባላባቶቹ መካከል ጸብ ተፈጥሮ የነበረ ከሆነ በቀብር ስርዓቱ ላይ እንዲገኝ በማሰብ አንድ ከብት እንዲካስ ይደረጋል፡፡ ባላባቱ በቀብር ስርዓቱ ላይ መገኘት ያልቻለው በጽኑ ህመም እንዲሁም ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ከሆነ ገይማው በለቅሶው ቦታ የባላባቱን ጦር ይዞ ይሄዳል፡፡ በዚህም ባላባቱ እንደተገኘ ተቆጥሮ ስርዓተ ቀብሩ ይከናወናል፡፡ ይህን ሃሳብ አቶ ዘለቀ ገሩ በቃለ መጠይቅ ጊዜ እንዲህ በማለት ገልጸውታል፡፡

*ባላባት ሲሞት ለሁሉም መልዕክት ይላካል፡፡ ማንም አይቀርም ፡፡ ከፍተኛ ችግር ካላገጠመው በቀር፡፡ ሌሎች ባላባቶችም እንዲሁ፡፡ ለምሳሌ ኩሪ ቢሞት ማጂ ገዢ ካልሄደ ኩሪ አይቀበርም፡፡ ማጂ ገዢም አልሄድም ያለበትን ምክንያት እንዲናገር ይደረጋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በባላባቶች መካከል ጸብ ሊፈጠር ይችላል፡፡ በወሰን ሊጋጩ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ አንዱ ባላባት አልሄድም ሊል ይችላል፡፡ ለቀብሩ ሁሉም ባላባቶች መገኘታቸው ካልተረጋገጠ የሟች ባላባት የቅርብ ዘመዶች መልዕክት ይላካሉ፡፡ በዚህ ወቅት ባላባቱ በዚህ ጊዜ አስቀይሞኛል፣ አስከፍቶኛል ብሎ ይመልሳል፡፡ ባላባቱም በቀብር ስርዓቱ ላይ መገኘት ስላለበት ከብት ይከፈለዋል፡፡ ከዛም ቂሙን ያነሳል፡፡ በቀብሩም ላይ ይገኛል፡፡ ሁሉም ባላባት ካልተገኘ ግን ቀብሩ ሊራዘም ይችላል፡፡ ( ቃለ መጠይቅ፡ 11/06/06)*

በዕለቱ እንባ አውጥቶ ማልቀስ የተከለከለ ነው፡፡ ሀዘኑን መቋቋም አቅቶት የውስጡን ቢተነፍስ እንኳን እንዲያቆም ይገደዳል እንጂ ለቅሶውን መቀጠል አይችልም፡፡ ከዚህ ይልቅ ሃዘኑን በለቅሶ ጭፈራ መወጣት ይኖርበታል፡፡ የለቅሶ ጭፈራውም ከሙዚቃ መሳርያ አጠቃቀም ጀምሮ እስከ ግጥምና ዜማ ድረስ ራሱን የቻለ ዜማ ያለው ነው እንጂ በዘፈቀደ አይጨፈርም፡፡

በቀብሩ ቀን ከበሮ "ታርቡ"፣ ክራር "ባር"፣ ጡርምባ "ኒሙጎልን"፣ እጅ ቃጭል "ኸሪ" ጦር "ጋርኺ" እና ጋሻ "ጊያሉ" እንዲሁም በገና "ጋዝ" በመያዝ ይጨፍራሉ፡፡ በእጅ የሚመታ የከብቶች ቃጭል "ካሽ" በዕለቱ ሴቶች ይጫወታሉ፡፡ ቃጭሉም የሚመጣው

ከባላባት ዘመዶች ነው፡፡ የእጅ ቃጭሉም የሚዘጋጀው የከብቶች የአንገት ቃጭል ተሰብስቦ በጉሎ እንጨት ላይ በማንጠልጠል ነው፡፡

የጉሎ እንጨት የተመረጠበት ዋናው ምክንያት የጉሎ ዛፍ በቀላሉ መብቀል እና መስፋፋት ስለሚችል የባላባት ዘር እንዲበዛ እንዲሁም እንዲስፋፋና ስርዓቱ ቀጣይነት እንዲኖረው  ታስቦ መሆኑን አቶ ዘለቀ ገሩ ገልጸውልኛል፡፡



ፎቶግራፍ 8 የከብት ቃጭል (ካሽ)

የከብት ቃጭሉን የሚያጮሁት ሴቶች ሲሆኑ ወንዶቹ ደግሞ በከበሮ፣ በክራር እና በጡርምባ ያጅቧቸዋል፡፡ ይህ ቃጭል ባላባት ብቻ ሲሞት በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ለአገልግሎት የሚውል ሲሆን ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ባላባት ሲሞት እንኳን ሰው ከብቶችም ያለቅሳሉ የሚለውን ሃሳብ ለማሳየት ነው፡፡



ፎቶግራፍ 9 የሚች ቤተሰቦች ከበሮ፣ ክራር እና ጦር ይዘው እየጨፈሩ

ለቅሶው በሙዚቃ መሳርያዎች በመታጀብ የሚቀርብ ሲሆን ሚች ባላባትን ለማወደስ ደግሞ ቃል ግጥሞችን ይገጥማሉ፡፡ ይህን ቃል ግጥም የሚያቀርቡት የባላባቱ ዘመዶች ሲሆኑ ቃል ግጥሞቹ የባላባቱን ደግነት፣ ጀግንነት፣ እንዲሁም መልካም አስተዳዳሪነት የሚገልጹ ናቸው፡፡ በለቅሶው ጭፈራ ሁሉም ሰው ተሳታፊ ይሆናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የባላባቱን የዘር ግንድ አመጣጥ እንዲሁም ባላባቱ ያስተዳደረባቸውን እና ድል ያደረገባቸውን ቦታዎች በመጥቀስ ውዳሴውን ያቀርባሉ፡፡ ከዚህ በታች የሶስት ባላባቶች የውዳሴ ቃል ግጥሞች ይቀርባሉ፡፡

## ለማጂ ገዢ “ማጂ ኪያብም” የሚቀርብ የውዳሴ ቃል ግጥም

| ዲዚኛ | አማርኛ ትርጉም |
| --- | --- |
| ኢባብ ዘኩ ኢይክን ኢድዎ | የባላባቶች ግርማ ሞገስ የሆንክ |
| እንጌብዝ ጌርቦዮ ክርስቲት ኪያብም ዳድ አልቱ | ለጥማቴ መጠጥ የሆንክ የክርሲ ኪያም[17] ልጅ ጀግና የተሰኘኸው |
| አአትንኪ አይትንዴብ መዝደኪ አይትን ማን ዘኮዮ | የተወለዱ ከብቶችን አሳዶ የሌላውን |

[17] በማጂ ወረዳ የሚገኝ ታዋቂ ባላባት

| | |
|---|---|
| | ክብት ለመመኘት የሚቃጣው |
| የኔ ጎቤ ጎቢስ አትን ዳዱዎ ኢዎ ኢወችና ኪኑድዎ | ያገር ያለህ! ለሃገር የተወለድክ ልጅ እንደ ዱር ነብር |
| አጎል ዋክ ሽር የን አይ አል ገፍንዳዝ | ከላይ ለመጣ የማንትንበረከክ ደፋር |
| | ለዚህም ክብር የተሰጠህ |
| ማጂ ኩሪና ጎቤንቃዝ ኡካ | የማጂ የኩሪና የሃገሪቱ አጎት የሆንክ |
| ኢንጌብዝካ አጌር ቦዳድካ | ለእርካታዬ መጠጥ የጌርቦይ[18] ልጅ |
| ዳሞትኪ ኪያብም ዳድ አልትግ | የዳሞት ኪያብም ልጅ አልት[19] |
| የትክንጊ ኮይቶዝ ዳሞትክንክ ኪይ ከይሲና | ለእናትህ ዘመዶች አጋር የሆንክ |
| | የዳምት[20] ከይሲ |
| አልግ ኪ ጾኒናክን አብም | የኦልግ ጾኒ[21] ዘመድ |
| ከ ኒያክዝ ኢዝክን አብ አልጋንት ሱብን | ወንድ የሆንክ አይንህ እንደእሳት የሚቀላ |
| ያርን ዱብን ዋይ ቻቻ”!! | ጠላት ሲመጣ ተነስተህ ጠባቂ የሆንክ |

ከላይ በቀረበው መሰረት ባላባቱ በሞቱ ጊዜ ውዳሴ ይቀርባላቸዋል፡፡ ይህን ክዋኔ የሚከውነው አንድ ሰው ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ በቅብብል ነው ፡፡ በስርዓቱ ላይ ያለ ማንኛውም ስው ለሚች ባላባት ውዳሴ ላቅርብ ካለ አይከለከልም፡፡ አንዱ ውዳሴውን ጨርሶ ሲያበቃ የሙዚቃ መሳርያዎች መጨወት እና መሳርያ በብዛት ይተኮሳል፡፡ ይህም ክዋኔው እንዲደምቅና ውዳሴውን ሁሉም በጸጥታ እንዲያዳምጡት የሚያደርግ ነው፡፡

## የ “ኩሪ ዲርሙ” ለሬታውራሪ ኩሪ የሚቀርብ ሙገሳ

| ዲዚኛ | የአማርኛ ትርጉም |
|---|---|
| አትክንጌና ሲሴ ባሽኪ ጾኒና ባዝና ባት ቻክና | አሁን ልበል ትሰማለህ ወይ? ባሽኪ፣ጾኒና ባዝና ባት ቻክና[22] የተሰኘህ |

[18] የባላባት ስም ነው

[19] ስያሜውን የውሰድከው ለማለት ነው

[20] የባለባት ስያሜ ሲሆን እንዳንዴም ባላባት የሚለውን ቃል ለመግለጽ ይጠቀሙበታል

[21] በስልጣን ተዋረዱ ውስጥ የሚገኝ አንድ ባላባት

| | |
|---|---|
| ኮሊቻክቃዝ ቶዝ ዱይት ያብ ዳድ | የነ ኮሊቻድ[23] ዘመድ የዱይት[24] ሰዎች ልጅ |
| አባብ ኮንግ ኮክንት ኪይሴና ዱጂ | ወደ ጎዳና ወጥተህ የመንገዱ አለቃ የሆንክ |
| ኢስ ገሲዝን ይዝን ኮድን ዱርን ኬዝቁጻ | የእህሎች መጀመሪያ ላንተ የተፈቀደልህ |
| ቻቡ ገሊ አይት ዳድካ | የለምለም ሳር እናት የከብቶች ጌታ |
| ቸሊግ ኪ ኮምት ዳይ ቻይካስን ባብ አለቃ | የቸሊግ[25] ንግስት ልጅ የቻይ ካስን[26] |
| ባልን ዴብድን ኬዝቴ ቸች ዚኩ ዳድ | በወኔ ወጥተህ የሁሉም ጠባቂ ጀግና |
| እንኮዬ!!!! | እናት የሆንክ!!! |

ፊታውራሪ ኩሪ የቀረበው ሙገሳ እንደሚያመለክተው ባላባቱ ከሌላው ሰው በምን እንደሚለዩ የሚያመለክቱ፣ ባላባቱ የተገበሯቸውን ታላላቅ ድርጊቶች የሚገልጹ፣ የባላባቱን ጀግንነት የሚያሳዩ፣ ድል ያደረገባቸውን ቦታዎች፣ የባላባቱን ቀደምት ታላላቅ ጀግና ዘሮች በማንሳት ያወድሳሉ፡፡

## የኦር ቡርጂ ውደሳ

| ዲዚኛ | የአማርኛ ትርጉም |
|---|---|
| ናብዳድ ኦኩ አኒባብቲኪ ኤክሳይታት ጋላሴሪንግቃዝ | የናብ ልጅ አጎት ባላባት የተሰኘህ የሳይ[27] ቆነጃጅት የሆኑትን የተመኘህ |
| ኢኮምቱቃዝ ውች ማንኪጥ | ንግስት የሆኑትን የተመኘህ |
| አዳዱ ኮይዝና ቿምቃዝናኑቲጊታ አይቴ | እንደ መብረቅ የቿምች ጌታ |
| አጌቴ-------የለዬ | ቀብራራው |
| ጎቤንታት ዚም ጎድን ጌድኖ | ሀገሩ እየመሸብኝ ነው የምለው |
| ጎንታኡንት ዳድኮ የሌዬ | አንተ የጎንታ ወጣት ልጅ |

---


[22] የተሰመረባቸው የባላባት ስሞች ናቸው
[23] ታዋቂ ባላባት ነበሩ
[24] የባላባቶች መቀበርያ ስፍራ
[25] በወረዳው የሚገኝ አካባቢ
[26] በአካባቢው የሚገኝ የባላባት ስም ነው
[27] በወረዳው የሚገኝ ቦታ

| | |
|---|---|
| አዳርግክ ከይሴና ዳድ ዳልምዴ | ዳርጋ[28] ባላባት ልጅ ዳግ[29] የነቀልክ |
| አዳጊ ኢ ኮይዝ አምብና ዳዬ | የዳጊ ኮይዝ ቤተ ልጅ |
| አዳዴ ቃንካዜ ኢስካ ኢንስንካ | እናንተዬ እህልና ማር |
| ኦይትካ ታዳዝ ኢስታዝ ኤክዳችት | ከብትንም የሚሠጥ ደችት ላሉትም ነብር የሚሰጥ |
| ወክ ጉቢን ዴብድንታድን ተኢንቻ | እንደ እትብት ቀብር የሆንክ ተነስተህ ግን ገናና የሆንክ |

የኦር ቡርጂም ውደሳ ከላይ ከቀረቡት ከሁለቱ የተለየ አይደለም፡፡ ከላይ የቀረቡት የሶስት ባላባቶች ሙገሳዎች እንደሚያመለክትቱት የሙገሳው ትኩረት የሚች ባላባት ደግነት፣ ጀግንንት እንዲሁም ቀደምት ዘሮች ላይ ነው፡፡

የባላባት ዘሮች በተቻላቸው አቅም ከየቤታቸው ያሏቸውን የሙዚቃ መሳርያዎች እና የጦር መሳርያዎች ይዘው በመምጣት ጭፈራውን ማድመቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለቅሶው ደማቅ ካልሆነ የባላባቱ ዘር ይወቀሳል፡፡ ሴቶች እግራቸው ላይ የሚያደርጉትን "ኸሪ" የሚባል ቃጭል የሚያስሩ ሲሆን ወንዶች ደግሞ ከበሮ፣ ክራር፣ ጥሩምባ ጋሻ፣ ጦር እንዲሁም የነብር ቆዳ በመያዝ በመያዝ ይጨፍራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ወራሽ ባላባት ከአጃቢዎቹ ጋር በመሆን አንድ ጊዜ ወደ አስከሬኑ አንድ ጊዜ ደግሞ ወደ ጭፈራው እያለ ይጨፍራል፡፡ ከዛም ደግሞ በመቀመጫው ላይ አረፍ ይላል፡፡ ወራሹ ለጭፈራ በሚነሳበት ጊዜ ሁሉም በእልልታና ሆታ ይቀበሉታል፡፡ ክራሩም ሆነ ቃጭሉ ይደምቃል፡፡ ሁሉም ሰው ይጨፍራል፡፡ ካሽ የሚያጮሁት ሴቶች እንዳይደክማቸው እየተቀያየሩ ያጮሃሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ለቅሶው ደማቅ ይሆናል፡፡






[28] የአካባቢ ስም

[29] የእንሰት ዘር

ጋሻ ኽሪ ጡሩምባ የነብር ቆዳ



ጦር ከበሮ ጠመንጃ ክራር

ፎቶግራፍ 10 ለቀስተኞች ከቤታቸው ይዘው የሚመጧቸው ቁሳዊ ባህሎች

የአካባቢው ሰው በቡድን በቡድን እየሆነ ይመጣል፡፡ ይህም የሚሆነው ለቅሶው ደመቅ እንዲል ነው፡፡ ለቀስተኛው እየበረከተ ሲመጣ አዲስ የለቅሶ ቤት ይዘጋጃል፡፡ ይህ የለቅሶ ቤት "ይስክ" በመባል ይጠራል፡፡ የባላባቱ ቤተሰቦች ከቤታቸው ወጥተው በዚህ ቤት ይቀመጣሉ፡፡ አዲሱ የለቅሶ ቤት ባላባቱ በሞቱ በሶስተኛ ወይም በአራተኛ ቀን የሚሰራ ነው፡፡ በዚህ ቤት ውስጥ በጨርቅ ወይም በእንሰት ቅጠል አስከሬኑን አስመስለው ያስቀምጣሉ፡፡ በዚህ ቤት የባላባቱ ሚስት እና ቤተዘመዶች ተሰባስበው ያለቅሳሉ፡፡ ይህ ቤት የሚሰራበት ቦታ "ሙክት ባብዥ" ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህም የሾላ ዛፍ ስር እንደማለት ነው፡፡

በመቀጠልም የአስከሬኑን ከፈን[30] እንደ አስከሬን በመጠቀም በአዲስ እርጥብ ቆዳ ይገነዛል፡፡ የተገነዘውም ከፈን የባላባቱ ወንድሞችና ወራሽ በእግራቸው ረገጥ ረገጥ አድርገው በሙክት ባብዠ ፊት ለፊት ሁለት ቆጮ በመትከል በቆጮው መካከል ይቀብሩታል፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት የቤተ ዘመድ ሀዘን የቀንሳል ተብሎ ስለሚታሰብ ሲሆን ሁለት ቆጮ መተከሉ ደግሞ የዲዚ ብሄረሰብ ከቆጮ ጋር ያለውን ቁርኝት ለመግለጽ እንደሆነ በቡድን ውይይት ጊዜ ተናግረዋል፡፡

[30] የአስከሬን መሸፈኛ ጨርቅ



ፎቶግራፍ 11 አዲስ የለቅሶ ቤት "ይሰክ"

ለቀስተኞች እየተሰበሰቡ ሲሄዱ እና ሲበረክቱ የሚች ጎረቤቶችና የቅርብ ዘመዶች አስከሬን መሸኛ የሚሆን ምግብ ያዘጋጃሉ፡፡ በተለይ በባላባት ሞት ጊዜ እርድ ስለማይጠፋ ስጋው በብዛት ይቀቀላል፡፡ አምቾም እንዲሁ ይዘጋጃል፡፡ ለባላባቱ ሞት ቀድሞ የተዘጋጀ ቦርዴ ካለም ይበጠበጣል፡፡ ሁሉም በልቶ ጠጥቶ መሄድ አለበት፡፡ በምግብ ዝግጅቱ ወቅት ስጋው የሚቀቀለው ተከትፎ ሳይሆን ከፍ ከፍ ተደርጎ ነው፡፡ ይንንም የሚያደርጉት ጊዜ ለመቆጠብና ለለቀስተኛ ለማደል እንዲያመች ታስቦ ነው፡፡



ለመመቀቀል ተቆራረጠ ስጋ



ለአንድ ለቀስተኛ የሚታደል ስጋ በቃጫ ታስሮ፣



ቆጮ



ቦርዴ፣



የበቆሎ፣ የማሽላ፣የነቆሎና የደንጎሎ እሸት ተቀቅሎ



አምቾ

ፎቶ ግራፍ 12 ለለቀስተኞች ማስተናገጃ ከሚዘጋጁ ምግቦች መካከል

አብዛኛው ለቀስተኛ ከየቦታው መሰብሰቡ ከታወቀ በኂላ በወራሹ አማካይነት የመጣች አንድ መሲና ጊደር ተቀጥቅጣ ትታረዳለች፡፡ ከብትን ቀጥቅጦ ማረዱን አስመልክቶ አቶ ዘለቀ ገሩ እንደተናገሩት፡-

> *በዕለቱ ከብት በቢለዋ አይታረድም፡፡ ይህ ባህሉ የሚያዘው ነው፡፡ በመሆኑም ለለቅሶ የመጣው ከብት ሁሉ ተቀጥቅጦ ከሞተ በኂላ በቢለዋ አንገቱ ይቆረጣል፡፡ የሚቀጠቀጠው በድንጋይ ወይም በእንጨት ነው፡፡ ይህን የሚያከናውን የተመረጠ ሰው አለ፡፡ በተጨማሪም ከሟች ጋር ያለውን የጠበቀ ዝምድና ለማመልከት ነው፡፡ ተቀጥቅጣ የታረደቻው መሲና ትታረድና አንጀቷ ይነበባል፡፡* (ቃለ መጠይቅ፡ 11/06/06)

መሲና ከብት የተመረጠበት ምክንያት መሲና ከብት መውለድ ስለማትችል የሟች ባላባቱም የአስተዳደር ዘመን ያበቃ መሆኑን ለማመልከት እንዲሁም ለወራሹ እና ለህዝቡ ሰላም ይሆናል በሚል ነው፡፡ በቆዳውም አስከሬኑ ለመጨረሻ ጊዜ እንዲጠቀለል ይደረጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቆዳው ትንሽ ከበሮ ይሰራል፡፡ ይህ ከበሮም በቀብር ቦታው ላይ በትራስጌ በኩል ስለሚሰቀል ነው፡፡ ከበሮው የሚሰራበት ምክንያት ባላባቱ በህይወት ዘመናቸው በሙዚቃ መሳርያነቱ በብዛት ሲገለገሉበት የቆዩ መሆናቸው እና ከበሮና ክራር የዲዚ ብሄረሰብ የደስታም ሆነ የሃዘን ጊዜ መሳርያ መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡



ፎቶግራፍ 13 ከበሮ ሲሰራ

አስከሬኑ ከመውጣቱ በፊት በአዲሱ ወራሽ ባለባት መሪነት እየዞሩ ይጨፍራሉ፡፡ ከቅርብም ሆነ ከሩቅ የሚመጡ የባላባት ወገኖች እየጨፈሩ ይዘው ያመጡትን ወይፈንና

ጊደር ቀጥቅጠው በማረድ ደሙን በጡሩምባ (በቀንድ) በመቅዳት በሚች ጆሮ ውስጥ አራት ጊዜ በጣታቸው ይጨምራሉ፡፡ ይህም የሚከወነው አንተ በህይወት እያለህ እንዳበላኸኝ እንዳጠጣኸኝ እንተም በደረቁ አትሂድ ብለው ነው፡፡

አስከሬኑን የሚሸከሙ ሰዎች ከቤተዘመድ ውስጥ ከተመረጡ በኋላ አስከሬኑን በሳጥን ሳይሆን ቃሬዛ የሚመስል “ኮይ” በተባለ አልጋ ወደ ቀብር ስፍራው ይጓዛል፡፡ ሬሳውን እንዲነኩ የተፈቀደላቸው ብቻ ይነካሉ፡፡ ህዝቡም እያለቀሰ እንዲሁም እየጨፈረ ከአስከሬኑ ኋላ ይከተላል፡፡ የተመረጡ ሰዎች አስከሬኑን ይዘው ሲወጡ መጀመርያ ከበሮ ይመታል፡፡ በማስከተል ጡሩንባ፣ ቀጭል፣ ክራር፣ ለጀግንነት ተምሳሌት ደግሞ ጦር ይሰበቃል፡፡ መሳርያ/ጥይት/ በተደጋጋሚ ይተኮሳል፡፡ መሳርያ በመተኮሱ ላይ ሴቶችና ህጻናት ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ ጥይት መተኮስ አሁን አሁን እየተከለከለ እንደሆነ አቶ ዘለቀ ገሩ ይናገራሉ፡፡

> *ባላባት ሲሞት ጥይት ይተኮሳል፡፡ ወንዱም ሴቱም ይተኩሳል፡፡ አሁን ግን ከላይ ከወረዳው አስተዳደር ጽህፈት ቤት መሳርያ እንዳይተኮስ የሚል መመርያ ደርሶናል፡፡ ምክንያቱ ምንድን ነው ስንላቸው ጥይት ያባክናል፣ የሚገዛው በውድ ስለሆነ ነው አሉ፡፡ እኔ አሁን የቀበሌ ሊቀመንበር ነኝ፡፡ መሳርያ እንዳይተኮስ ተናግሬያለሁ፡፡ ግን የባላባት ወገኖች አሻፈረኝ ብለው ይኸው ይተኮሳሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉትም ለቅሶውን ለማድመቅና ባህሉ እንዳይቀር ነው፡፡ መከልከል ተከልክሏል፡፡ ( ቃለ መጠይቅ፡ 11/06/06)*



ፎቶግራፍ 14 የባላባት ዘመድ የሆነችው ሴት መሳርያ ስትተኩስ



ፎቶግራፍ 15 ጉዞ ወደ ቀብር ስፍራ

የባላባቶች የቀብር ቦታ “ዱይ” ወይም “ኤርም” በመባል የሚጠራ ሲሆን በደን የተሸፈነ ጫካ ነው፡፡ የብሄረሰቡ  አባላት ደኖችን በከፍተኛ ሁኔታ  ይጠብቃሉ፡፡ ከነዚህ ምክንያች መካከል ደግሞ ደኖቹ የባላባቶች ደንብ መስርያ እና የባላባቶች መቀበርያ በመሆናቸው ነው፡፡ በዚህ “ዱይ” በተባለ ቦታ ውስጥ ዛፍ  የቆረጠ እንዲሁም ያቃጠለ ሰው ከገንዘብ እስከ ሞት ድረስ ሊቀጣ ይችላል፡፡  በዚህ ቦታ ከባላባቱ ደንብ ሰሪዎች ውጪ ማንም ሰው መሄድ  አይችልም፡፡ ባላባቱም ቢሆን፡፡ ከሄዱ መጥፎ ነገር ያጋጥማቸዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ከዚህም ውጪ መቃብሩን ጠባቂ ነብር አለ ስለሚባል ሰው ለመሄድ አይደፍርም፡፡ አቶ ቸሬ አኮ የመቃብር ስፍራውን አስመልክቶ እንዲህ በማለት ገልጸዋል፡፡

> *ዱይ በሚባለው አካባቢ ማንም ሰው መሄድ አይችልም፡፡ ይህ አባቶቻችን የነገሩን ነው፡፡ አንደውም ነብር ሁሉ አለ ይባላል፡፡ አባቴ ሲነግረኝ በድሮ ጊዜ የባላባቱን መቃብር ለመጎብኘት የሄዱትን ሰዎች ነብሩ እዛው እንደበላቸው ነው፡፡ በዛ ስፍራ እንጨት መስበርም ሆነ ሳር ማጨድ ተከለከለ ነው፡፡ ድሮ ድሮ እስከሞት ያስቀጣ ነበር፡፡ እኛ ወጣት ሆነን ደግሞ ቅጣቱ ግርፋት ነበር፡፡ አሁን ደግሞ ገንዘብም ከብትም ሆኗል፡፡ ነገር ግን በዚያ ቦታ እየሄደ የሚያስቸግር ሰው የለም፡፡* (ቃለ መጠይቅ፡ 10/06/06)

### 4.1.3 ጊዜ ቀብር

አስከሬኑ ሲሸኝ አዲሱ ወራሽ ባላባት አስከሬኑን መሸኘት /መቅበር/ ስለማይችል የተወሰኑ ሰዎች ከአዲሱ ወራሽ ባላባት ጋር ይቀራሉ፡፡ መቅበርያው ቦታ ለመድረስ  ትንሽ ሲቀር ሁሉም ሰው ወደኋላ  እንዲመለስ በገይማዎቹ አማካይነት ትዕዛዝ ይሠጣል፡፡ ከዚህ በኋላ አስከሬኑን እና አንዲት ጊደር ይዘው የሚሄዱት  ደንብ ሰሪዎች “ገይሞች” ናቸው፡፡ ይህች ጊደር ደንብ ሰሪዎቹ አስከሬኑን ቀብረው ሲጨርሱ የሚበሉት ነው፡፡  ባላባቱ የሚቀበሩበት ሳጥን ካለ በሳጥን ከሌለም በከብቱ ቆዳ እንደተጠቀለለ ይቀበራል፡፡

የተለያዩ የባላባት የቀብር ቦታዎችን አስመልክቶ በቃለ መጠይቅ ወቅት የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በማጂ ወረዳ ካሉት ባላባቶች ውስጥ የሶስት ባላባቶች የአቀባበር ስርዓት የሚለያይ መሆኑ ነው፡፡ ይህን መረጃ በምልከታ ማስደገፍ አለመቻሌ ደግሞ የመረጃ ክፍተት እንዳይፈጠር ስጋት አሳድሮብኛል፡፡  መረጃውን በምልከታ መከታተል ያልተቻለበት ምክንያት በቀብሩ ስፍራ ማንም ሰው መገኘት

ስለማይችል ነው፡፡ ይህ ክልከላ የቀብር ቦታውን አጠቃላይ ድባብ በሚገባ እንዳልገልጽ እንቅፋት የሆነብኝ ሲሆን የሶስቱን ባላባቶች የአቀባበር ሁኔታን አስመልክቶ የቀብር ቦታውን ከሚያውቁ ሰዎች እና ከባላባት ቤተሰቦች የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ነው፡፡

የባላባት የአቀባበር ሁኔታ እንደ ባላባቶቹ የሚለያይ ሲሆን "ኦር ቡርጂ" የተባሉት ባላባት ጥቅጥቅ ባለ ደን ውስጥ ትልቅ ዛፍ ስር፣ የቀድሞ ባላባት አስከሬን የነበረበት ዛፍ ግንድ ላይ አስደግፈው እንዳይወድቅ በሃረግ በማሰር ያቆሙታል እንጂ አፈር ቆፍረው አይቀብሩም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ደግሞ ባላባቱ በህይወት እያሉም ሆነ ሲሞቱ አፈር አይነካቸውም፡፡ ከአስሬኑ ራስጌ አዲስ የተሰራ ከበሮና ክራር ተሰቅሎ ይቀመጣል፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት ከበሮና ክራር የዲዚ ብሄረሰብ የደስታም ሆነ የሃዘን ጊዜ መሳርያ መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡ አቶ ባልኩ ኩሙ የባላባቱን ቀብር እንዲህ በማለት ገልጸዋል፡፡

> *ኦር ቡርጂን የምንቀብረው ኤርም በተባለው ስፍራ ነው፡፡ የሚቀበረውም አፈር ተቆፍሮ ሳይሆን ዛፍ ላይ በቁመቱ ተደርጎ እንዳይወድቅ በሀረግ በማሰር ነው፡፡ ሳጥን ካለ በሳጥን ሳጥን ከሌለ ደግሞ በ "ጎኑ"[31] ተደርጎ በዛፉ ላይ በደንብ ይታሰራል፡፡ ሀረጉ ጠንካራ ነው፡፡ ባላባቱ አፈር ውስጥ የማይቀበርበት ምክንያት ባላባቱ እኮ አፈር አይነካቸውም፡፡ እንደኛ አርሰው ቆፍረው አይበሉም፡፡ በዛፉ ላይ የሚደረጉትም አፈር እንዳይነካቸው ነው፡፡* ( *ቃለ መጠይቅ*፡ 10/06/06)

[31] ጎኑ የሚባለው ቶሎ ከማይበረበር ጠንካራ ከሆነ ከትልቅ ዛፍ የሚዘጋጅ ሲሆን ሁለት ሜትር ቁመት ያህል ከተቆረጠ በኋላ ውስጡ ይቦረቦራል፡፡ በጥንቃቄ ከተቦረቦረ በኋላ አስከሬኑን ውስጥ ባማስገባት ከላይ በሌላ እንጨት ይደፍኑታል፡፡ ቀደም ባሉት ጊዜያት ሰው የሚቀበረው በዚህ ነበር ፡፡ አሁን ግን ሳጥን መስራት ጀምረዋል፡፡ ይህ ጎኑ የሚባለው ቁስ በብዛት ለከብቶች የውሀ ማጠጫ ሆኖ ያገለግላል፡፡



ፎቶግራፍ 16 የኦር የባላባት ቀብር

“ሳይ ኪያዝ” የተባለው ባላባት  ደግሞ የሚቀበረው አስከሬኑን በከብት ቆዳ በመጠቅለል በንብ ቀፎ ውስጥ ተደርጎ  በትልቅ ዛፍ ላይ በማስቀመጥ ነው፡፡ ይህ የሆነበትን ምክንያት በቡድን ውይይት ወቅት እንደገለጹልኝ በአካባቢው የንብ ምርት በብዛት እንዳለና ለንብ ከፍተኛ ክብር ስላላቸው ቀብራቸውን በንብ ቀፎ ውስጥ አድርገዋል ይላሉ፡፡

በማህበረሰቡ የሚገኙ ሌሎች ባላባቶች ደግሞ ቀደምት ባላባቶች በተቀበሩበት መቃብር ውስጥ የሚቀበሩ ናቸው፡፡  መቃብሩ የሚዘጋጀው በመጀመርያ በአዋቂዎች የቀዳሚው ሟች ባላባት መቃብር ስፍራ እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡  አጽሙ እስኪገኝ ድረስ አፈሩ ይቆፈራል፡፡ አጽሙ ሲገኝ እጅን በትኩስ የፍየል ደም ታጥቦ ይወጣል፡፡ ሁሉም ይለቀማል፡፡ ሁሉም ወጥቶ ሲጨርስ  አዲሱ ሬሳ በጉድጓዱ ውስጥ ይገባል፡፡ በዛም ከላይ የቀዳሚው ባላባት አጽም ይደረጋል፡፡  በመቀጠልም እንጨት በርብራብ መልክ ይደረግና  አፈሩ ይመለሳል፡፡

### 4.1.3 ድህረ ቀብር

አስከሬኑ ከተቀበረ በኋላ ያሉት አራት ተከታታይ ቀናት የሃዘን ቀን በመሆኑ ቤተዘመድና ጎረቤት እንዲሁም ከሩቅ የሚመጡ ሰዎች ሁሉ ለቅሶ ይደርሳሉ፡፡ ማልቀስ ግን አይፈቀድላቸውም፡፡ እንደ ተለመደው በለቅሶ ጭፈራ ሀዘናቸውን መወጣት ግን

ይፈቀድላቸዋል፡፡ ለለቀስተኛ የተዘጋጀውን ምግብ እየበሉ ይቀመጣሉ፡፡ ምግቡ ካልበቃ ሌላ እርድ ይፈጸማል፡፡ የተቀቀለው ስጋ በቃጫ እየታሰረ ይቀርብላቸዋል፡፡ ቢለዋ ያገኘ በቢለዋ፣ ጩቤ ያለው በጩቤ የሌለው ደግሞ በጥርሱም ቢሆን እየነጩ ይበላል፡፡ ቦርዴውንም ይጠጣሉ፡፡ አራቱንም ቀናት ግን ወደ ዋናው ቤት ሳይገቡ አዲሱ አስከሬኑ የተሸኘበት ቤት በመቀመጥ ይጨፍራሉ፡፡

የባላባቱ ሞት ከተሰማበት ቀን ጀምሮ በነዚህ አራት ቀናት ውስጥ የአካባቢው ሰው ስራ አይሰራም፡፡ በከብቶች አንገት ላይም ቃጭል አይታሰርም፡፡ ከአራተኛው ቀን በኋላ አዲሱ ባላባት ወደ ቀድሞ ሚች ባላባት ቤት ሲገባ የሃዘኑ የመጨረሻ ቀን በመሆኑ ሁሉም ወደ የስራው ተሰማርቶ የዘወትር ተግባሩን ያከናውናል፡፡ ባላባቱ ወደ ሚች ባላባት በሚገባበት ጊዜ ሚች ባላባት የተለየ የክብር ልብስ ካለው ይለብሳል፡፡ የሚች ባላባት ሚስቶች እና ቤተሰቦቹ በቤቱ በር አካባቢ ቆመው በጭፈራና በእልልታ ይቀበሉታል፡፡

ባላባት ሲሞት አርባ ወይም ሰማንያ ቀን ተጠብቆ ተስካር አይወጣለትም፡፡ ሁሉም ነገር በስምንት ቀናት ውስጥ ይጠናቀቃል፡፡ ወራሽ የሚች ባላባትን ሀብትና ንብረት ወርሶ ማስተዳደር ይጀምራል፡፡ የሚች ባላባትን ሚስት/ቶች ለራሱ ማግባት ወይም የተወሰኑ ንብረት ሰጥቶ ከቤቱ ማስወጣት ይችላል፡፡ ይህ ካልሆነ ደግሞ አገልጋዮቹ ሊያደርጋቸው ይገባል፡፡

## 4.2 የአዛውንቶች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ (ታል)

በዚህ ክፍል የአዛውንቶች የለቅሶ ስርዓት ይቀርባል፡፡ በብሄረሰቡ የአዛውንቶች የለቅሶ ስርዓት የሚወክለው የብሄረሰቡ አካላት ዕድሜያቸው ከሰባ አመት በላይ ሆነው የልጅ ልጅ ለማፍራት የደረሱትን ነው፡፡ ለነዚህ የብሄረሰቡ አካላት የሚከወነው የለቅሶ ስርዓት እንደሚከተለው ነው፡፡

አንድ አዛውንት ከሞተ በማህበረሰቡ ከባድ ሃዘን ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ትልቅ ሰው በብሄረሰቡ ዘንድ የሚከበር በመሆኑ ነው፡፡ እነዚህ ሽማግሌዎች በዕድሜ ታላቅነት፣ ጀግና እና የሃገር ተጠሪ ሆነው አገልግለዋልና ነው፡፡

## 4.2.1 ቅድመ ቀብር

አንድ አዛውንት እድሜው ለሞት ሲቃረብ ወይም ህመም ሲጠናበት የተለያዩ ክንውኖች ይከናወናሉ፡፡ ከነዚህም ክዋኔዎች መካከል አንዱ የኑዛዜ ስርዓት ነው፡፡ ይህ ስርዓት የሚከወነው በአዛውንቱ ወይም በቤተሰቡ ፍላጎት ላይ በመመስረት ነው፡፡ የኑዛዜ ስርዓቱ ውርሱን የሚመለከት ሲሆን ይህም አዛውንቱ ያለውን ንብረት ለልጆቹ እንዲሁም ለልጅ ልጆቹ የሚያከፋፍልበት ስርዓት ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ በሞቱ ወቅት ምን አይነት ስርዓት እንደሚከናወንለት የሚያሳውቅበት መንገድ ነው፡፡ ይህ ስርዓት በሚከናወንበት ወቅት ከላይ እንደተጠቀሰው እንደባላባቱ የኑዛዜ ስርዓት ከፍ ያለ ድግስ የሚደረግ ባይሆንም ለስርዓቱ መከወኛ የሚሆን መለስተኛ ድግስ ይደረጋል፡፡ ቦርዴ፣ አምቾ፣ ቡና የመሳሰሉት በስርዓቱ ወቅት ለምግብነት የሚቀርቡ ናቸው፡፡ የኑዛዜ ስርዓቱ የሚፈጸመው በቤተሰቦችና አዛውንቱ በመረጧቸው ሽማግሌዎች ነው፡፡ ውርሱ ሁሉንም የሚያስማማ ሆኖ ከተገኘ ሌሎች ስርዓቶች ይደረጋሉ፡፡

አዛውንቶች ሲታመሙ በልጅ ልጆቻቸው ይጠበቃሉ፡፡ በሽታቸው እየፀና ከሄደ ቤተሰቦቻቸው ለለቅሶው ማስፈጸሚያ የሚሆን ምግብ ያዘጋጃሉ፡፡ አዛውንቶቹ የእድሜ ባለፀጎች በመሆናቸው እንዲሁም የልጅ ልጆቻቸውን ለወግ ለማዕረግ በማብቃታቸው ከፍተኛ የሆነ ዝግጅት ይደረጋል፡፡

የአዛውንቱ መሞት እንደተሰማ ቤተሰቦች አስከሬኑን ያስተካክላሉ፡፡ የግንዘት ስርዓቱ የሚከናወነው በሚች ቤተሰቦች ወይም ቤት ውስጥ በሚገኙ “ባቡ” ወይም “ላሊባብ”[32] በሚባሉ ሰዎች አማካይነት ነው፡፡ ቤተሰቡ የሚገንዘበት ምክንያትም የሚችን ገመና ለመሸፈን እንዲሁም ከቤተሰቡ ውጭ ሌሎች ማወቅም ሆነ ማየት የሌለባቸው በመሆኑ ነው፡፡ የአገናነዝ ሁኔታው እጥበት የሌለው ሲሆን የአገናነዙ ሁኔታ በቁመት

---

[32] እነዚህ ሰዎች የአዛውንቱ አገልጋይና ተንከባካቢ ናቸው፡፡

ሳይሆን ቁጢጥ በማድረግ ነው፡፡ ከዚህ በመቀጠልም በአንድ አዲስ የበሬ ቆዳ ወይም በእንሰት ቅጠል ተጠቅልሎ ይገነዛል፡፡

በቡድን ውይይት ወቅት እንደ ተመለከትኩት በአሁኑ ወቅት አዛውቶችን በበሬ ቆዳ ገንዞ መቅበር እየቀረ መሆኑን እና በጋቢ(ኩታ) መቅበር እንደጀመሩ የገለጹ ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ ደግሞ የኑሮ ውድነት እንዲሁም ሽማግሌዎች ለዚህ ብለው አንድ በሬ እንዲሁም በቅርብ ታርዶ የተቀመጠ እርጥብ ቆዳ የሚያስቀምጡ ባለመሆናቸው ነው፡፡ የግንዘት ስርዓቱ ከተከናወነ በኂላ ቤት ውስጥ በሚገኝ እና "ቦልቴ" በሚባል ከፍ ያለ ቦታ ላይ ያስቀምጡታል፡፡

የግንዘት ስርዓቱ ከተከናወነ በኂላ ሽማግሌዎች የአዛውንቱን ሞት ለማርዳት ወደ ልጅ እና የልጅ ልጆች ይላካሉ፡፡ የአዛውንቱን ሞት ሁሉም የልጅ ልጆች እንዲሰሙ ይደረጋል፡፡ በቀብር ስርዓቱ ላይ ሁሉም መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ምክንያቱም የለቅሶ ስርዓቱን የሚፈጽሙት  እነርሱ በመሆናቸው ነው፡፡

የልጅ ልጆች ከየቦታው እስኪሰበሰቡ ድረስ የሟች ቤተሰቦች ወራሹን ያዘጋጃሉ፡፡ ለወራሽነት የተመረጠውም  ሰው የሟችን ቤተሰብ  ማስተዳደሩን እና  የአባቱን መልካም ተግባር ለማከናወን በአስከሬኑ በፊት ቃል ይገባል፡፡ እስከሚቀበርም ድረስ ከአስከሬኑ አጠገብ ይቀመጣል፡፡ ሟች ሴት ከሆኑ የውርስ ስርዓት የሚከናወንላቸው አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ሴቶች ማህበረሰቡ የንብረት ባቤትነት የሚሰጣቸው አይሆኑም፡፡ ነገር ግን ሟች ወንድ ከሆኑ የቤት አስተዳዳሪ እንዲሁም የቤቱ መሪ በመሆናቸው ወራሽ ያስፈልጋቸዋል፡፡

የልጅ ልጆች መርዶውን ሰምተው ይመጣሉ፡፡ ለለቅሶው ስርዓት ማስፈጸሚያ የሚሆን ሁሉም አንድ ከብት ይዘው መምጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ ያላደረገ የልጅ ልጅ እንደሌለ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ልጆችና የልጅ ልጆች ወደ ለቅሶው ቤት ሲመጡ በጊቢው ውስጥ ያሉ እንሰት፣ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም ቤቱንም ጭምር ያወድማሉ፡፡ ላንተ/ ንቺ ያልሆነ ለማንም አይበጅ እያሉ ያለቅሳሉ፡፡ አቶ ዘለቀ ገሩ እንደተናገሩት

*ሁሉም ከየቤታቸው እያለቀሱ እየጨሁ ይመጣሉ፡፡ ልክ እቤቱ ጋር ሲደርሱ ወንዱ ሮጦ ከቤቱ አናት ላይ ይወጣና የቻለውን ያህል ያፈራርሳል፡፡ ሳሩንም ሆነ እንጨቱን*

*ያወላልቃል፡፡ ሴቷም እንዲሁ በጊቢው ውስጥ ያገኘችውን ቆጮውንም፣ ጎመኑንም ሁሉንም ውድምድም ታደርጋለች፡፡ ጊቢው በሙሉ ምስቅልቅሉ ይወጣል፡፡ እንዲህ የሚደረገው ያለባቸውን ሃዘን ለመወጣት ሲሆን አያት ከመሞቱ በፊት በጎ ነገር ካልሰራና በድኒቸው ከሆነ የሚያወድሙት ነገር ይቀንሳል፡፡ እነሱም ግዴለሽ ይሆናሉ፡፡ ከውስጣቸው በደንብ ባያዝኑም ከብቱን አምጥተው አርደው ቀብረው ይሄዳሉ፡፡* (ቃለ መጠይቅ፡ 11/06/06)

ከአቶ ዘለቀ ሃሳብ እንደምንረዳው የሚችን ቤትና ንብረት የሚያወድሙት ሃዘናቸውን ለመወጣት ብለው ነው፡፡ ይህ ስርዓት በአሁን ወቅት በመንግስት የተከለከለ እንደሆነና እነሱም የሚስማሙበት መሆኑን በቡድን ውይይቱ ወቅት ለመረዳት ችያለሁ፡፡ በቡድን ውይይት ወቅት ይህ ስርዓት እንዳይከወን መከልከሉ ያላስደሰታቸው ሁለት ሰዎች ሲሆኑ ሌሎቹ ሰባት ሰዎች ደግሞ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል ስለዚህ ቢቀር መልካም ነው በማለት መከልከሉን ደግፈዋል፡፡ አቶ ባልኩ ኩሙ የስርዓቱን መከልከል ከማይደግፉት መካከል ናቸው ፡፡ እሳቸው እንደገለጹት

*የታል ስርዓት እንደቀድሞው እየተከወነ አይደለም ፡፡ የዚህ ምክንያቱ ብዙ ነው፡፡ አንዱ የኑሮ ውድነት ነው፡፡ ሁለተኛው ለለቅሶ ከብት የሚያመጣ የለም፡፡ አብዛኛው አራሽ ወይም ነጋዴ ሆኗል፡፡ ሌላው ደግሞ መንግስት ይህን አድርጉ ይህን አታድርጉ በማለት የለቅሶው ስርዓት እየጠፋ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ትክክል አይመስለኝም፡፡ እኔ በእድሜዬ ሳየው ስርዓቱ በጣም ተቀይሯል፡፡ በተለይ ደግሞ የታል፡፡ የባላባቱስ እንደምንም በሁለትም በሶስትም በሬ ይከናወናል፡፡ አንድ አዛውንት ሲሞት የቀበሌው አስተዳዳሪ ወይም አንድ ሚሊሻ በአካባቢው አይጠፋም፡፡ ለምን ለመከልከል ነው፡፡* (ቃለ መጠይቅ፡ 11/06/06) በማለት በምሬት ተናግረዋል፡፡

ማህበረሰቡ ይህ ስርዓት በሚከናወን ወቅት ጥፋቱን ለመቀነስ የሚከውነው የራሱ ስርዓት እንዳለው አቶ ባልኩ ኩሙ ይገልጻሉ፡፡

*ልጆች እና የልጅ ልጆች ሲመጡ ቤቱንም ሆነ አትክልትቱን እንደሚያጠፉት ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ሀዘን መስበርያ ብለው የሚያቀርቡትን ቦርዴ እና ቆጮ በጊቢው መግቢያ በር ላይ ይዘው ይጠባበቃሉ፡፡ ምን አልባትም የሟች ቤተሰቦች ይህን ነገር ማድረግ ቢረሱ ጎረቤቶች ተጠንቅቀው ቦርዴውንና ቆጮውን ይዘው ይጠባበቃሉ፡፡ ልጆቹም እያለቀሱ ሲመጡ ሃዘኑን ቀነስ አድርጉት እያሉ ምግቡ እንዲቀምሱት ያደርጋሉ፡፡ ልጆቹም መሬት*

*ላይ በመውደቅ በመጮሀ ብቻ ሀዘናቸውን ይወጣሉ። ይህን ሳያደርጉ ከጠበቋቸው ግን ውድምድም ያደርጉታል።* (ቃለ መጠይቅ፡ 11/06/06)

የልጅ ልጆችና ልጆች እየጮሁ በማልቀስ ፣ በጥፍር ፊትን በመቧጠጥ እና በማድማት፣ በዘዴ በደረት መሬት ላይ በመውደቅ ሃዘናቸውን ይገልጻሉ። የሟች ወንድና የሴት ልጆች ከቀብር በፊት "ታል" የተባለውን ስርዓት ይፈጽማሉ። የተገኘውን ጥጃ ወይም በሬ በመንዳት የታል ዘፈን እየዘፈኑ ወደ ለቅሶው ቤት ይሄዳሉ።

ታል ዘፋኞችና ሌሎች ሰዎች ከጊቢ ውጪ ይሆናሉ። ታል ይዞ የሄደው ልጅ ከአንድ ሌላ ሰው ጋር በመሆን አራት ጊዜ ወደ ጊቢው ገባ ወጣ በማለት ይመለሳል። ይህ ስርዓትም "ኮል ኦፐም" ይባላል። ምርቃት ሊመረቅ ወይም በረከት ሊቀበል ነው ማለት ነው። ከአራተኛው ዙር በኋላ ከአጃቢዎች ጋር በመሆን ወደ ጊቢው ይገባል። የቤቱ ደጃፍም ላይ ይቆማል። "ቤስን" የተባለው ሰው ከቤት ውስጥ ይወጣና ውሀ ይረጫቸዋል። ብዙ ተባዙ ብሎ ይመርቃቸዋል። የምርቃት ስርዓቱ ከተፈጸመ በኋላ ከብቱን በድንጋይም ሆነ በጦር መትቶ በቢለዋ በማረድ ደሙን በእንጨት ጡርንባ፣ በሾርቃ አሊያም በእጁ ቀድቶ ለወራሹ አራት ጊዜ ይሰጠዋል።



ፎቶግራፍ 17 ለታል ማስፈጸሚያ የታረደው ከብት ደም በሾርቃ ሲቀዳ

ወራሹም ደሙን በአስከሬኑ የቀኝ ጆሮ ውስጥ ይጨምራል። የዚህ ስርዓት ትርጉም ባዶህን አትሰናበተኝ፣ እንዳበላሁህ እንዳጠጣሁህ እኔንም ባርከኝ፣ እንዴት በደረቁ ትሸኘኛለህ ለማለት ነው። የሴቷ ልጅ ይህን ካልፈጸመ በሟቾቹ አካባቢ መብላት

መጠጣት አይችልም፡፡ የሚያደርገው ካጣ ወይም ከብት ከጣ የከብት ቃጭል ወስዶ በወራሽ እግር ስር አስቀምጦ ይመረቃል፡፡ ብር፣ ሽክላ እና ድንጋይም ማቅረብ ይችላል፡፡

## 4.2.2 ጊዜ ቀብር

ከላይ የቀረበው ስርዓት ከተከናወነ በኋላ የሟች የቀብር ቦታ ዝግጅት ይከናወናል፡፡ የቀብር ቦታው የሚዘጋጀው በተለያየ መንገድ ነው፡፡ በተለይ ቀደም ባሉት ጊዜያት ማህበረሰቡ የተለያዩ ሃገረሰባዊ እምነቶችን በሚከተልበት ወቅት የቀብር ስርዓቱ ባህላዊነቱን የጠበቀ ነበር፡፡ ይህ ስርዓት በከተሞች አካባቢ የቀረ ቢሆንም በገጠሩ አካባቢ ግን አሁንም ደረስ ይተገበራል፡፡ የክርስትና እምነት እየተስፋፋ ማህበረሰቡ መጠመቅ ሲጀምር እና በአካባቢው ቤተክርስቲያናትን ማነጽ ሲጀምር ሃይማኖቱ እንደሚፈቅደው መሰረት ቤተክርስቲያን ወስደው መቅበር ጀመሩ፡፡

በርካታ የማህበረሰቡ አባላት ሀገረሰባዊ እምነት የሚከተሉ በመሆናቸው በቀደምት ስርዓታቸው መሰረት የማህበረሰቡን ባህል ተከትለው የቀብር ስርዓታቸውን ያከናውናሉ፡፡ ይህ የቀብር ስርዓት ከባላባቶች የቀብር ስርዓት የሚለይ ሲሆን በተለይ አዛውንቶች የሚቀበሩት በቤታቸው ጓሮ ውስጥ ነው፡፡

ይህን የቀብር ቦታ የሚያዘጋጁት የሟች የቅርብ ዘመዶችና ቤተሰቦች ሲሆኑ ከቤቱ በጀርባ በር በኩል ከ20 እስከ 25 ሜትር ርቀት ላይ የቀብር ቦታውን ይቆፍራሉ፡፡ የቀብር ጉድጓዱ ከ1.5 ሜትር እስከ 2 ሜትር ድረስ በአማካኝ ይደርሳል፡፡ የቀብሩ ቦታ ከቤቱ ያለው አቅጣጫ እንደ ሟቹ ጾታ የሚለያይ ሲሆን አዛውንቱ ሴት ከሆኑ ከቤቱ በስተግራ ወንድ ከሆኑ ደግሞ በስተቀኝ በኩል ይቀበራሉ፡፡ የመቃብር ስፍራው አቅጣጫ ይህ የሆነበትን ምክንያት አቶ ዘለቀ ገሩ

> *በቀብር ስርዓቱ ወቅት የቀብር ጉድጓዱ አቅጣጫው የሴት በስተግራ ሲሆን የወንድ ደግሞ በስተቀኝ በኩል ነው፡፡ ይህ እንግዲህ ባህላዊው አቀባበር ነው፡፡ ወንድ በስተቀኝ የሚቀበርበት ምክንያት ወንድ የቤቱ መሪ በመሆኑ እና ሴት ደግሞ ተከታይ በመሆኗ ነው፡፡ በባህሉም ወንድና ሴት ሲተኙም ወንድ በስተቀኝ ሴት ደግሞ በስተግራ በኩል ነው ፡፡ ቀኝ መሪ ነው፡፡ ሴቷ የመሪው ደጋፊ ናት፡፡* (ቃለ መጠይቅ፡ 11/06/06) በማለት ሃሳባቸውን ገልጸዋል፡፡

ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለውም ወንዶችን የበላይ ሴቶችን ደግሞ የበታች አድርጎ የማሰብ ሁኔታ እንዳለ ነው፡፡ የቀብር ቦታው ከተዘጋጀ በኋላ አስከሬኑን ከቤት አውጥተው በተዘጋጀው ስፍራ ይቀብራሉ፡፡

### 4.2.3 ድህረ ቀብር

አዛውንቶች ወይም የእድሜ ባለፀጎች ከመቀበራቸው በፊት የልጅ ልጆች ያመጧቸው ከብቶች ታርደው ለለቀስተኛ መመለሻ ተብሎ ይዘጋጃል፡፡ ብዙ ከብት ከታረደ ሟቹ ዘመደ ብዙ እንዲሁም የልጅ ልጆቹ ሲመሰገኑ ይከርማሉ፡፡ አዛውንቶች ሲሞቱ ከስምንት ቀናት እስከ አንድ ወር ለሚደርስ ጊዜ ይታዘናል፡፡ የጊዜውን ልዩነት የሚወስነው የሟቹ ሃብትና ንብረት እንዲሁም የልጅ ልጆች ብዛት ሁኔታ ነው፡፡

ሟቹ ሐብታም ከሆነ የቀብሩ እለት ከታረደው ከብት ውጪ ሌላ ከብት ታርዶ እስከ ስምንት ቀን ድረስ እየበሉ እየጠጡ ሊቆዩ ይችላሉ፡፡ ሐብት ከሌለው ደግሞ ጎረቤቶች በሚያዋጡት ምግብ የሩቅ ሰዎች እንዲሸኙ ይደረጋል፡፡ በለቅሶው ቀናት የሟችን ቤተሰቦችና ወራሹን በማጽናናትና በማላቀስ የውርሱን ሁኔታ እንዲሁም ለሟች ተስካር የሚያበወጡበትን ቀን እየቆረጡ ይቆያሉ፡፡

በዲዚ ብሄረሰብ በተራው ሰው ዘንድ የውርስ ስርዓት የሚከናወነው አባት ሲሞት ብቻ ነው፡፡ አባት ሲሞት የመጀመርያ ልጅ ወራሽ ይሆናል፡፡ ሟች ወንድ ልጅ ከሌለው የሟች ወንድም ወይም የወንድም ወንድ ልጅ ወራሽ ይሆናል፡፡ ወንድ ልጅ ከታጣ ሴት ልጅ በተራው ማህበረሰብ ዘንድ መውረስ ትችላለች፡፡

ሟቹ ሁለትና ከዚያም በላይ ሚስቶች ያገባ ከሆነ የመጀመርያዋ ሴት የወለደችው ወንድ ልጅ ወራሽ "ቂዝባብ" ይሆናል፡፡ ምን አልባትም የመጀመርያዋ ሚስት ቀድማ ወንድ ካልወለደችና ከርሷ በኋላ የመጣችው ወንድ ልጅ ብትወልድ ከዛም የመጀመርያዋ ወደ ኋላ ዘግይታ ብትወልድ የዚች የመጀመሪያይቱ ሚስት ወንድ ልጅ በዕድሜ ታናሽ ቢሆንም እናቱ ታላቅ/የመጀመሪያ/ ስለሆነች እሱ ወራሽ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ታላቂቱ ካለ ክብረ ንጽህና የተዳረች ከሆነ እና ቀጥላ የተዳረችው ደግሞ ክብረንጽህና ኖሯት የወለደችው ከሆነ የታላቂቱ ልጅ እያለ ክብረ ንጽህና ካላት የተወለደው ልጅ ወራሽ ይሆናል፡፡ ወራሹም ከወረሰበት ቀን ጀምሮ በአባቱ ስም የሚጠራ ይሆናል፡፡

ወራሹ የሟችን ተስካር ለማውጣት ይዘጋጃል፡፡ ሟች ሴት ከሆኑ ደግሞ ባል ተስካር ያወጣሉ፡፡ ባል ከሌሉ ደግሞ ልጆች ተስካሩን ያወጣሉ፡፡ ተስካሩ የሚደረገው ለእድሜ ባለጸጎችና ለጎልማሶች/ትዳር/ ላላቸው ነው፡፡ ተስካሩ የሚወጣበት ጊዜ ሟች ከሞተ በአርባኛው ቀን ወይም በሰማንያኛው ቀን ነው፡፡ የተስካሩን ጊዜ የሚወስነው ተስካር አውጪው ባለው አቅም የሚወሰን ነው፡፡ በአብዛኛው በአርባኛው ቀን ተስካር ያወጣሉ፡፡ ለተስካሩ የሚያስፈልገው ቦርዴ የተባለውን መጠጥ ማዘጋጀት ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን በብዛት መዘጋጀት አለበት፡፡ የሚመጣው ሰው ስለማይታወቅ ነው፡፡ በብሄረበቡ ዘንድ ቦርዴ የተባለው መጠጥ እንደ ምግብ የሚያገለግል ነው፡፡



ፎቶ ግራፍ 18 ለተስካር ማውጫ የሚሆን ቦርዴ ሲቀቀል

የተስካሩ ቀን ሲደርስ ዘመድ አዝማድ ሁሉ ቀን ቆጥሮ ይመጣል፡፡ ቤት ውስጥ ሲገባ ማልቀስ ግን አይፈቀድም፡፡ እየተጫወቱ ቦርዴውን ይጠጣሉ፡፡ ወደ ማታ ቤተዘመድ ሁሉ ይሠበሰባል፡፡ ለቀብር የመጣውም ያልመጣውም በዚህ ቀን የሚቀር ዘመድ የለም፡፡ ቦርዴ እየጠጡ ያመሻሉ፡፡ ስርዓቱ የሚጀመረው ጠዋት ሲነጋጋ ሲል ነው፡፡ የሟች ቤተሰቦች አዲስ ሰው እንደሞተባቸው እየጮሁ ማልቀስ ይጀምራሉ፡፡ ቤተ ዘመዱ ሁሉ በመሰባሰብ አዲስ ሬሳ እንደ ወጣ ሁሉም ያለቅሳል፡፡ ይጮሃሉ፡፡ ዳግም ለቅሶ ይሆናል፡፡ ሲነጋጋ ማልቀሱን ያቆማሉ፡፡ ከዚህ በኋላ የተረፈ ቦርዴ ካለ ይጠጣሉ፡፡ ወደ ቤታቸውም ሲሄዱ ለሀዘን ያሰሩትን ክር ይበጥሳሉ፡፡ ሃዘኑ ይበቃችኋል እያሉ የሟችን ቤተሰቦች የሀዘን ክር እንዲበጥሱ ያደርጋሉ፡፡ የሀዘን መጨረሻ ያድረግልን እያሉ ተመራርቀው ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ፡፡ ይህም የሃዘኑ ፍጻሜ ይሆናል፡፡

## 4.3 የጎልማሶች እና የወጣቶች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ

## (ያብ ባርዝ ሹቡ)

ይህ ሶስተኛው የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ አይነት ነው፡፡ በዚህ ስርዓት ውስጥ የሚካተቱት ጎልማሶች ወይም ወጣቶች ሲሆኑ በጋብቻ የተሳሰሩ ወይም ያላገቡ፣ ልጅ የወለዱ ወይም ያልወለዱ፣ እድሜያቸው ለአቅመ አዳም ወይም ሔዋን የደረሱ በአብዛኛው ከ14 ዓመት እና ከዚያ በላይ ያሉትን የብሔረሰቡ አባላት የሚያጠቃልል የለቅሶ ስርዓት አይነት ነው፡፡

ከላይ የቀረቡት የማህበሰቡ አባላት ሲሞቱ ከፍተኛ ሀዘን ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ጎልማሶቹና ወጣቶቹ የህይወትን ውጣ ውረድ ያላዩ፣ ብዙ ነገር የሚጠበቅባቸው፣ በማህበራዊ ህይወታቸውን የሚያጣጥሙበት ጊዜ ላይ የሆኑ፣ ዘሮቻቸውን ያልተኩና የተኩትም ልጆቻቸውን በሚገባ ሳያሳድጉ ጥለው የሄዱ በመሆኑ ነው፡፡ በብሄረሰቡ የወጣቶችና የጎልማሶች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ተመሳሳይ ነው፡፡

### 4.3.1 ከቀብር በፊት

በዲዚ ብሄረሰብ አንድ ጎልማሳ ወይም አንድ ወጣት በጠና ሲታመም ቤተሶቦቻቸው በጣም ይጨነቃሉ፡፡ ጭንቀቱ ከሁሉም የማህበረሰቡ ክፍሎች የበለጠ እና ከፍተኛ ነው፡፡ ህመምተኛው ህምሙ ከጸናና የማይድን መሆኑ ከታወቀ በቤት ውስጥ የተለያዩ ዝግጅቶች ይደረጋሉ፡፡ ከነዚህ ዝግጅቶች መካከልም ምግቦችን ማዘጋጀት እና ዘመዶች እንዲዘጋጁ መንገር የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

ሞቱ ድንገተኛም ሆነ በህመም የመጣ ቢሆንም ለቅሶው ከፍ ያለ ነው፡፡ በምሬት ይታዘናል፡፡ የሟች ቤተሰብ እና ቤተ ዘመድ ብቻ ሳይሆን የአካባቢው ሰው ሁሉ ከልቡ ያዝናል፡፡ በተለይ ደግሞ ሟች በአካባቢው ማህበራዊ ህይወት ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ ካለው ሃዘኑ ይበረታል፡፡ ሁሉም ያለቅሱለታል፡፡

አንድ ጎልማሳ ሲሞት በተለይ ትዳር ያለው(ላት) ከሆኑ ከባድ ድንጋጤ ይሆናል፡፡ ሟች ነፍሱ እንደወጣች ወዲያው ይለቀሳል፡፡ ቤተሰብ፣ ጎረቤት እንዲሁም ዘመድ አዝማድ እንዲሰሙ ይደረጋል፡፡ ሁሉም ሰው ለለቅሶው ይዘጋጃል፡፡ ግን ዝግጅቱ ከአንድ ቀን በላይ አይቆይም፡፡ ቤተሰቦች እና የቅርብ ዘመዶች የአስከሬን መጠቅለያ ጋቢ፣ ከምግብ ደግሞ አምቾ፣ ቦርዴ እንዲሁም እሸት ወ.ዘ.ተ ሁሉም ከቤቱ ያዘጋጃል፡፡

የሟች ቤተሰቦች የሟችን መለየት አይተው ካለቀሱ በኋላ አስከሬኑን ማስተካከል ይጀምራሉ፡፡ ሟች ወንድም ይሁን ሴት አስከሬን መገነዝ የሚችል ሰው ሊገንዘው ይችላል፡፡ ነገር ግን የቤተሰቡ አባል መሆን አለበት ፡፡ ከቤተሰብ ውጪ የራስን ገመና ማሳየት የሚያስነውር ነገር በመሆኑ ነው፡፡ የግንዘት ስርዓቱም የሟችን ልብስ በሙሉ በማውለቅ በጀርባው ቀጥ ብሎ እንዲተኛ ያደርጉታል፡፡ ከዛም ያጥቡታል፡፡ ሟች ከታጠበ በኋላ በአዲስ ጋቢ ይጠቀለላል፡፡ ጋቢው ከአንድ በላይ ሊሆን ይችላል፡፡ የጋቢው ብዛት ሟች እንዳለው ዘመድ ብዛት ይሆናል፡፡ ጎልማሶች በብዜረሰቡ ሲሞቱ ዘመድ አዝማዱ ሁሉ አንድ አንድ ጋቢ ያመጣሉ፡፡ ይህን ካላደረገ ከልብ ወዳጅነቱና ከዘመድነቱ ይሰረዛል፡፡ ወ/ሮ ኮምቱ አኩ  እንደገለጹት

> *አንድ ሰው ሲሞት ዘመዶች ሁሉ ለመገነዣ የሚሆን ጋቢ ያመጣሉ፡፡ አንድ ሰው ብዙ ዘመድ ካለው ለቀብሩ ብዙ ጋቢ ይመጣለታል፡፡ አስከሬኑም በሁሉም ጋቢ ተጠቅልሎ ይቀበራል፡፡ ምንም የሚቀር ጋቢ አይኖርም፡፡ ሁሉም መሬት ይገባል፡፡ ለምሳሌ እንደ ሟች ሰላሳ ጋቢ ቢመጣለት ሰላሳውም አብሮት ይቀበራል፡፡* (ቃለ መጠይቅ፡ 12/06/06)

በርግጥም በግንዘቱ ወቅት በተገኘው ጋቢ ብቻ  ተጠቅልሎ ይቀመጣል፡፡ ዘመድ አዝማዱ አስከሬኑ በሳጥን ውስጥ ሳይጨመር ከደረሱ በሳጥኑ ውስጥ ይጨምራሉ፡፡ ሳጥኑ ተዘግቶ ከደረሱ ደግሞ  በመቃብሩ ጉድጓድ ውስጥ ይጨምራሉ፡፡ ጋቢውን ወደ ሳጥን ውስጥ ወይም ወደ ጉድጓድ ውስጥ ከመጨመራቸው በፊት ክሩን ወይም ጥለቱን ይቆርጡታል፡፡ ይህም የሚሆነው ጥለቱን በአንገታቸው ላይ ስለሚያስሩት ነው፡፡ የጋቢው ጥለት ሰፊ ቢሆንም በቀጫጭኑ ይሰነጣጥቁት እና አንዱን በአንገታቸው ላይ ያስራሉ፡፡ ጋቢ የሌላቸው ቤተዘመዶች የጥጥ ማግ በአንገታቸው ያስራሉ፡፡ ለራሳቸው አስረው የተረፋቸውን ክር በለቅሶ ቤት በራፍ ላይ ያንጠለጥሉታል ፡፡ የሟች ዘመዶችም ያንን እያነሱ በአንገታቸው ላይ ያስራሉ፡፡ የሃዘን ምልክት በመሆኑ የሟች የቅርብ ዘመዶች የግድ ማስር ይኖርባቸዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አንዳንዶች ጥቁር ልብስ ይለብሳሉ፡፡ አብዛኞቹ ግን አይለብሱም ፡፡ በጥቁሩ ልብስ ፈንታ የተቀደደና የቆሸሸ ልብስ ይለብሳሉ፡፡ ይህም በሟች ሞት የተጎዱ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው፡፡ የሟች ቤተሰቦች፣ ዘመዶችና ጎረቤቶች ለለቅሶው ማስኬጃ የሚሆን ምግቦችን በለቅሶው ቤት ውስጥም ሆነ በየቤታቸው አዘጋጅተው ያመጣሉ፡፡



ፎቶግራፍ 19 ለለቀስተኛ መመለሻ የሚሆን አምቾ ሲዘጋጅ

ሁሉም ዘመዶች ከተሰበሰቡ በኋላ የሟችን ደግነት እና መልካም ተግባሮች እያነሱ በአንድነት በጊቢው ወስጥ ያለቅሳሉ፡፡ መጮህ ፊት መቧጠጥ፣ በደረት መውደቅ የሃዘን መገለጫዎች ናቸው፡፡ በዚህ የለቅሶ ስርዓት ላይ እንደ ባላባቶችም ሆነ እንደ አዛውንቶች የሙዚቃ መሳርያዎችን መጠቀም እንዲሁም ግጥም መደርደር አይፈቀደም፡፡ ምክንያቱም ሟቾቹ ያለ ዕድሜያቸው የሞቱ በመሆናቸው ነው፡፡ ሃዘን ማብዛትም ሌላ ሃዘን ያስከትላል ተብሎ በመታሰቡ ነው፡፡

በተለይ ምልከታ ባደረግሁበት አንድ የወጣት ለቅሶ ላይ የሃዘን መግለጫ ስርዓቱ በጣም ከባድ መሆኑን ለመገንዘብ ችያለሁ፡፡ የሞተችው ወጣት ሴት ስትሆን የአስራ ሰባት ዐመት እድሜ ያላት ናት፡፡ የሞቷ ምክንያት ያልታሰበና ድንገተኛ ነው፡፡ ሚዛን አማን በተባለው ከተማ የአስረኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን ህይወቷም ያለፈው በዛው ከተማ ነው፡፡ የቀብር ስርዓቷ ደግሞ የተፈጸመው ቱም በሚባለው ቦታ ነው፡፡

ቱም የዲዚ ብሄረሰብ ወረዳ መቀመጫ ሲሆን የወጣቷ ትውልድና እድገትም በዚሁ ቦታ ነው፡፡ ወላጆቿ የብሄረሰቡ ተወላጆች ናቸው፡፡ ለቅሶው የተሰማው ከሌሊቱ አስር ሰዓት ላይ ሲሆን ጩኸቱና ዋይታው የተለየ ነበር፡፡ አስከሬኑ በአካባቢው የደረሰው ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ላይ ነበር፡፡ አስከሬኑ ወደ ሟች የመኖርያ ቤት ሲገባ የነበረውን ሁኔታ በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም፡፡ ሁሉም ሰው ፊቱን በመቧጨርና በማድማት፣ መሬት

ላይ በመፈጥፈጥ፣ በመጮህ እንዲሁም በተለያዩ ነገሮች ራሳቸውን ሲጎዱ ተመልክቻለሁ፡፡ ይህን ሁኔታ አቶ ታደመ ኮመሩት እንዲህ በማለት ገልጸውልኛል፡፡

> *ዛሬ የተመለከትሽው ነገር በጣም ከባድ ነው፡፡ የሟችን ቤተሰብ በጣም ይጎዳል፡፡ ከዚህ ቀደም አንድ ነፍሰጡር ሴት ወንድሟ ሞቶ ለሃዘኑ ብላ ስትወድቅ ስተነሳ አጉል ነገር ላይ ወድቃ እሷም ሞተች፡፡ ሁለቱንም አብረን ቀበርን፡፡ ይህ ነገር ቢቀር እኔ በበኩሌ ደስተኛ ነኝ፡፡ ራስን በጣም ይጎዳል፡፡ ከሁለቱ ሟቾች በኋላ እንዲህ አይነት ስርዓት እንዳይደረግ በመንግስት ተከልክሎ ነበር፡፡ ነገር ግን ማንም እሺ አይልም፡፡ በባህሉም አንድ ሰው እንዲህ ሆኖ ካላለቀሰ አለቀሰ ስለማይባል ራሱን ይጎዳል፡፡* (ቃለ መጠይቅ፡ 9/09/09)

የሟች አስክሬን የመቀበሪያው ሰዓት ሲደርስ ጩኸቱም ሆነ ፊት መቧጠጡ ይበረታል፡፡ የመቃብር ቦታውና የአቆፋፈር ስርዓቱ በ 4.2.2 ላይ በቀረበው መሰረት የሚከናወን ነው፡፡ በዚህ ቦታ ሃዘኑ ጎዳቸው ሴቶች እንዲሁም እየወደቁ እየተነሱ ያስቸገሩ የሟች ቤተሰቦች በቤት ውስጥ እንዲቆዩ የሚደረግ ሲሆን ሌሎች በቀብር ስፍራው ሄደው ይቀብራሉ፡፡

### 4.4.2 ከቀብር በኋላ

ከቀብሩ በኋላ ሁሉም ተሰብስበው በሟች ቤተሰብ ቤት የተዘጋጀላቸውን ምግቦችና መጠጦች ይመገባሉ፡፡ ሟች የወለደች ከሆነች ባሏ ከሁለት ወር እስከ ሶስት ወር ደረስ በቤቱ ሆኖ ያዝናል፡፡ ይቀመጣል፡፡ ልጅ ከሌላት ግን በቤተሰቦቿ ቤት ለአራት ቀናት ብቻ የሚቀመጥ ይሆናል፡፡ ከዚህ በኂዋላ ሟች ያገባች ከሆነች ባሏ፣ ሟች ወንድ ከሆነ ደግሞ ሚስት በአርባኛው ወይም በሰማንያኛው ቀን ተስካር የሚያወጡላቸው ይሆናል፡፡ የተስካር ማውጣት ስርዓቱ ከላይ በ 4.2.3 እንደቀረበው ይሆናል፡፡ ከዚህ ስርዓት በኋላ የለቅሶው ፍጻሜ ይሆናል፡፡

## 4.4 የሕፃናት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ "ኩም"

የዲዚ ብሄረሰብ የሕፃናት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ከሌሎች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔዎች የተለየ ነው፡፡ ይህን ስርዓት "ኩም" በማለት ይጠሩታል፡፡ ስርዓቱ የሚከናወንላቸው የብሔረሰቡ ተወላጆች በአብዛኛው እድሜያቸው ከዜሮ አመት (ከተወለዱበት ቀን ጀምሮ) እስከ አስር ዓመት ድረስ ያሉትን ነው፡፡ እነዚህ ሕፃናት

በሚሞቱበት ጊዜ የለቅሶ ክዋኔው ከላይ እንደቀረቡት እንደሌሎቹ የለቅሶ ስርዓት አይደምቅም፡፡ ዝግጅትም አያስፈልግም፡፡ ሞቱ እንደተከሰተ ወዲያው ይቀበራል፡፡ ዘመድ እስኪመጣ አይጠበቅም፡፡ እየጮሁ፣ እየወደቁ እና እየተነሱ አይለቀስም፡፡ በተለይ ጥርስ ላላበቀለ ህጻን እምባ እንኳን ማውጣት አይፈቀድም፡፡ እናት ብቻ እንድታለቅስ ይፈቀዳል እንጂ፡፡

የሟቹ እድሜ ከፍ ያለ ከሆነ በተለይ ከአምስት አመት በላይ ከሆነ በመጠኑ ይለቀሳል፡፡ ዘመድ አዝማድ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡ ሟቹ (ቿ)ም እንደሞተ(ች) ለእናትና ለአባት የጉሎ ቅጠል በቃጫ ታስሮ በእጃቸው ላይ ይታሰራል፡፡ ይህ የሚሆንበትም ምክንያትን አስመልክቶ አቶ ታደመ ኮመሩት

> *ህጻናት ሲሞቱ ሁሉም ሰው ላይሰማ ይችላል፡፡ እናትና አባት በእጃቸው ላይ የጉሎ ቅጠል ካሰሩ ልጅ እንደሞተባቸው ይታወቃል፡፡ ለቅሶ ደርሶብኛል ተብሎ መልዕክት አይላክም፡፡ የጉሎ ቅጠል የሚታሰርበት ምክንያትም በቅርቡ ሌላ ልጅ እንዲተካላቸው በማሰብ ነው፡፡ የጉሎ ቅጠል በቀላሉ የሚበቅል ነው፡፡ ይህ ቅጠል ለተለያዩ ጉዳዮች ይውላል፡፡ በዚህም ስርዓት ላይ ለምርቃት ወይም ለበገ ምኞት ይውላል፡፡* በማለት ገልጸዋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፡ 11/06/06)

በዚህ የለቅሶ ስርዓት ላይ ለቅሶ ማብዛት አይፈቀድም፡፡ እናት ብቻ እንዲህ በማለት ታለቅሳለች፡፡

| **ዲዚኛ** | **የአማርኛ ትርጉም** |
|---|---|
| አዳዳኒ | ወይ ልጄ |
| አዳዳኒ | ወይ ልጄ |
| እዳዳሞሽቦ | ልጄ ሞተ |
| ይሬችሺን | ምን አጠፋሁ |
| ይረሻል | ኧረ ምን ይሻላል |

እናት ብቻም ብታለቅስ አፏን በእርጥብ ቆዳ አፍና ነው፡፡ ቀደም ባሉት ጊዜያት እናቶቹ አፋቸውን በእርጥብ ቆዳ አፍነው ያለቅሱ ነበር፡፡ ይህም ካልተገኘ የከብት ቆዳ በውሃ ውስጥ ነክረው አፋቸውን ይይዙ ነበር፡፡ ይህም እርጥብ ነገር ጥሩ ነው፡፡ እናትየዋን ሌላ ይሰጣታል፡፡ ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስታለቅስም ድምጽ አታወጣም ምክንያቱም እናትየዋ ገና መውለድ ስለምትችል ፈጣሪዋን ማማረር የለባትም ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ አምርራ ካለቀሰች ደግሞ ፈጣሪዋ ለወደፊት ልጅ ላይሰጣት ይችላል በሚል ነው፡፡ የቀብር ስርዓቱም

በመኖርያ ቤቱ አቅራቢያ የሚከናወን ነው፡፡ በለቅሶው ወቅት በተገኙ ሰዎች ይከወናል፡፡ ከቀብር በኋላ ሃዘን ያበቃል፡፡ በሶስተኛው ቀን እናት ገበያ ትወጣለች፡፡ ሀዘኗን ትረሳለች፡፡

## 4.5 የዲዚ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ማህበራዊ ተግባራት

በዲዚ ብሔረሰብ ዘንድ ለቅሶ ትልቅ ማህበራዊ ፋይዳ አለው፡፡ በብሔረሰቡ ባህል መሰረት ውርስ ሳያከናውኑ መቅረት፣ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ አለመገኘት እንዲሁም በስርዓቱ ላይ የሚከወኑ ተግባራት አለመፈጸም ከማህበራዊ ኑሮ መገለል እና ከፍተኛ ቅጣት ሊያስቀጣ ይችላል፡፡ ብሄረሰቡ የሚተገብረው የለቅሶ ስርዓት የብሔረሰቡን ማህበራዊ አንድነት የማስጠበቅ፣ የባላባታዊ ስርዓቱን ሽግግር የማስቀጠል እንዲሁም የማህበረሰቡን አመለካከት የመግለጽ ፋይዳው ከፍተኛ ነው፡፡

### 4.5.1 ለቅሶ የባላባታዊ ስርዓት ሽግግር ከማስቀጠል አንጻር

በብሄረሰቡ የባላባታዊ ስርዓቱ ሽግግር የሚከናወነው ሞት ወይም ለቅሶ ሲኖር ነው፡፡ በዚህ የለቅሶ ስርዓት ላይ ሟች ባላባቱ የሚፈጽሟቸው ስርዓቶችና ደንቦችን ተተኪው ባላባት መፈጸም መቻሉን ማህበረሰቡ የሚያረጋግጥበት መንገድ ይሆነዋል፡፡ የባላባቱ ሰርግም ሆነ ሌሎች ባህላዊ ስርዓቶች የለቅሶን ያህል ትልቅ ትኩረት የሚሰጣቸው አይደሉም፡፡ ምክንያቱም የባላባታዊ ስርዓቱ ሽግግር የሚፈጸመው በዚህ ክዋኔ ውስጥ በመሆኑ ነው፡፡ ይህን የስልጣን ሽግግር እና የለቅሶ ስርዓቱን በተመለከተ አቶ ታደመ ኮመሩት

> *የባላባት ለቅሶ ጊዜ በርካታ ክዋኔዎች ይኪያሄዳሉ፡፡ ከዚህ መካከል አንዱ ደግሞ የውርስ ስርዓቱ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት አንዱ ስርዓት ሲያልፍ አንዱ ስርዓት ይተካል ማለት ነው፡፡ ይህ ስርዓት የሚከወነው በለቅሶ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ስርዓቱ ባይኖር መተካካቱም አይኖርም፡፡ በርግጥም በዚህ ስርዓት ውስጥ የውርስ ጉዳይ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡ በዚህም ባላባታዊ ስርዓቱ ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያደርግ ይሆናል፡፡* (ቃለ መጠይቅ፡11/06/06) በማለት ገልጸዋል፡፡

ባላባታዊው የስልጣን ሽግግር ተጠብቆ እንዲቆይ ለቅሶ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ይህም የትኞች ዘሮች የባላባትነት ጥያቄዎች ማንሳት እንዳለባቸውና እና በብሄረሰቡ መካከል የሚነሱ ስልጣንን መሰረት ያደረጉ ግጭቶችን አስቀድሞ ለመከላከል ይጠቅማል፡፡

ባላባቶች በሚሞቱበት ጊዜ ብሔረሰቡ የሚፈጽው የራሱ የስልጣን መተካካት ስርዓት አለው፡፡ በዚህ ስርዓትም ባላባቶች በሚሞቱበት ጊዜ ደግሞ የስልጣን ሽግግሩ ከባላባት የዘር ግንድ እንዲመረጥ ባህሉ ይደነግጋል፡፡ ስልጣንን መሰረት በማድረግ ከሚነሱ አለመግባባቶችን እና ግጭቶችን  በለቅሶው አማካይነት ተፈትተው ከትውልድ ትውልድ ይተላለፋሉ፡፡

## 4.5.2 ለቅሶ ማህበራዊ አንድነትን ከማጠናከር አንጻር

ብሄረሰቡ አንድነቱን ከሚያጠናክርባቸው መንገዶች አንዱ የለቅሶ ስርዓቱ ነው፡፡ ለብሔረሰቡ የእርስ በርስ ግንኙነት መጠናከር እና ማህበራዊ ህይወትን ከማስተሳሰር ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ አለው፡፡ አንድ ሰው ሲሞት በማህበረሰቡ አባላት መካከል የሚፈጸመው መስተጋብ የሚፈጥው አንድ ራሱን የቻለ ማህበራዊ ተቋም ይኖራል፡፡ የማህበረሰቡ አባላትም በዚህ ማህበራዊ ተቋም ውስጥ የሚፈጽሟቸው ማህበራዊ መስተጋብሮች ይኖራሉ፡፡ ይህ ማህበራዊ መስተጋብ የብሄረሰቡን አካላት  የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮችን ለምሳሌ እርሻ፣ ሰርግ፣ ልደት፣ ወዘተ. በጋራ እንዲከውኑ  የማድረግ ተግባር አለው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በለቅሶ ስርዓተ ክዋኔው ወቅት ከሚታዩ መስተጋብሮች መካከል አንዱ በለቅሶው ላይ መገኘት ነው፡፡  በለቅሶ ስርዓቱ ላይ መገኘትም ሆነ መቅረት የሚያሳድረው ተጽዕኖ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡

ወ/ሮ ውልቤ ቡርጂ እንደገለጹት በለቅሶ ምክንያት የሚፈጠሩ መቃቃሮች የመፈታታቸው ጉዳይ ከበድ ያለ እንደሆነ ነው፡፡

> *በዲዚ ባህል አንድ ሰው ሲሞት ለቅሶ እንሄዳለን፡፡ በአካባቢው አንድ ሰው ቢቀር ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ይህ ሰው ምን ሆኖ ቀረ ተብሎ ይታሰባል፡፡ የቀረው ሰው ይወቀሳል፡፡ ከለቅሶው ባለቤት በተጨማሪም ሁሉም ሰው እስከዚህም ይሆንበታል፡፡ ማንም ሰው ሊያስታርቅም አይሞክርም፡፡ ለቅሶ ትልቅ ነገር ነው፡፡ ሰው ያቀያይማል፡፡ ነገር ግን ከፍተኛ ምክንያት ካለ እና ለሽማግሌዎች ከተናገሩ ሽማግሌዎቹ ያስታርቃሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ: 13/06/06)*

ከወ/ሮ ውልቤ ሃሳብ እንደምንረዳው በለቅሶ ምክንያት የሚፈጠሩ ቅይይሞች በቀላሉ የሚፈቱ አለመሆናቸውን ነው፡፡ ለቅሶ ያልደረሰ ሰው ከማህበራዊ ኑሮው ይገለላል፡፡  በተለይ ደግሞ ለባላባቱ ለቅሶ፡፡

## 4.5.3 ለቅሶ የማህበረሰቡን ታሪክ፣ እምነትና አመለካከት ከመግለጽ አንጻር

በለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ የማህበረሰቡ ታሪክ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍበት፣ ስርዓት የሚዋቀርበት እና የሚከወንበትን አጋጣሚ ይፈጥራል፡፡ ብሄረሰቡ ታሪኩን በለቅሶ ክዋኔ ውስጥ የመግለጽ አቅሙ ከፍተኛ ነው፡፡ በስርዓቱ ላይ የሚታዩት ቁሳዊ ባህሎች እና ስነ ቃሎች የማህበረሰቡን ታሪክ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

በለቅሶ ክዋኔው ላይ እምነትን የሚገልፁ ስርዓቶችም በርካታ ናቸው፡፡ ስርዓቶቱ ከሚንጸረቅበት መንገድ አንዱ የእርድ ስርዓት ነው፡፡ ይህን የእርድ ስርዓት ብሔረሰቡ ከመንጻትና መስዋዕት ከማቅረብ ጋር ያያይዘዋል፡፡

በውርስ ስርዓት ወቅትም ሆኑ በሌሎች የለቅሶ ስርኣቶች ላይ የሚፈጸሙ እርዶች ከብሔረሰቡ እምነት ስርዓት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ይህም የሟችን ነፍስ ለማስደሰት እንዲሁም ለፈጣሪ መስዋዕት ለማቅረብ ይታረዳል፡፡ ይህ ባይደረግ ሟችም ሆነ ፈጣሪ በሟች ቤተሰቦች ላይ ችግር ሊያደርስ ይችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡ አቶ ዘለቀ ገሩ እንደሚገልጹት

> *ሰዉ ሲሞት በርከት ያለ እረድ ይፈጸማል፡፡ ይህም የሚሆነው አንድም ለፈጣሪ ሌላም ደግሞ ሰውን ለማስደሰትም ጭምር ነው፡፡ የባላባቶች እርድ ጊዜ ብዙ ከብት ታርዶ በደንብ መስርያው ላይ መሰዋዕት ይቀርባል፡፡ ይህም የአባታችንን ነፍስ በጥሩ ሁኔታ እንዲቀበልልን ነው፡፡ የአዛውንቶች እርድ ጊዜ ደግሞ የልጅ ልጆች ከብት አምጥተው ካለረዱ ሟቹ ይቆጣቸዋል፣ እድሜያቸው አጭር ይሆናል ተብሎ ስለሚታሰብ ሁሉም አምጥቶ ያርዳል፡፡* (ቃለ መጠይቅ፡ 11/06/06)

በስርዓቱ ላይም ከክዋኔው በስተጀርባ የእምነት ጉዳይም መኖሩን መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ለእርድ (መስዋዕትነት) የሚቀርቡት ከብቶች ፍየል፣ በሬና መሲና ከብት ናቸው፡፡

የማህበረሰቡን አመለካከት በስርዓቱ ላይ ስንመለከተው በስርዓቱ ውስጥ ከብትን ቀጥቅጦ ማረድ፣ ጦር ጋሻና የጦር መሳርያዎችን መጠቀም፣ አካልን በመጉዳት፣ መነሳት በመውደቅ፣ ጥቁር በመልበስ፣ የቆሸሸ መልበስ የሟችን ማህበራዊ ደረጃ እና ለሟች ያላቸውን ፍቅር ይገልጻል የሚል አመለካከት አላቸው፡፡

# ምዕራፍ አምስት፡ ማጠቃለያ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በዲዚ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ላይ ገላጭ ትንተና በማድረግ የቀረበ ነው፡፡ መረጃው የተሰበሰበው በሶስት ተፈጥሯዊ መቼቶች ላይ በመገኘት በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት ነው፡፡ የብሔረሰቡ የለቅሶ ዓይነቶች በአራት ክፍሎች ከፋፍሎ መመልከት ማየት እንደሚቻል ተገልጿል፡፡ እነሱም የባላባቶች፣ የእድሜ ባለፀጎች፣ የጎልማሶች እና የወጣቶች እንዲሁም የሕፃናት የለቅሶ ስርዓት አይነቶች ናቸው፡፡

የለቅሶ ስርዓቱም ሚች በብሔረሰቡ ዘንድ ካለው ማህበራዊ ደረጃ፣ ከፆታ እንዲሁም ከእድሜ አንፃር በመነሳት የተለያዩ የለቅሶ ስርዓቶች ይካሔዳሉ፡፡ በነዚህ የለቅሶ ስርዓቶች ላይ የሚከወኑት ክዋኔዎችን ስንመለከት በባላባት የለቅሶ ስርዓት ጊዜ ለቅሶ ፈጽሞ የተከለከለ መሆኑ፣ የተለያዩ ቁሳዊ ባህሎችና ስነ ቃሎች ታጅቦ የሚቀርብ መሆኑ በአንፃሩ ደግሞ ለእድሜ ባለፀጎች የሚከወነው የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ "ታል" በሚባል በጭፈራ ታጅቦ እንደሚከናወን፣ በጎልማሶች እና በወጣቶች የለቅሶ ስርዓት ወቅት ከፍተኛ የሆነ ሃዘን እና ለቅሶ የሚከናወን መሆኑን እንዲሁም በህጻናት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ወቅት አነስተኛ ስርዓት እና ለቅሶ እንደሚኪሄድ ጥናቱ አመላክቷል፡፡

የለቅሶ ስርዓቱ በተለያዩ ዝግጅቶች እና ክዋኔዎች የሚካሄድ ሲሆን ስርዓቱ ከሶስት ቀን እስከ ሰማንያ ቀን ድረስ እንደየ ስርዓቱ የሚከወን ነው፡፡ ለዚህ የጊዜ ቆይታ መሰረቱ ለለቅሶው ስርዓት ማከናወኛ የሚደረጉ ዝግጅቶችን ለማከናወን እና የክዋኔውን ስርዓት ለመፈጸም እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በእያንዳንዱ የለቅሶ ስርዓት ላይ የሚታዩ ቁሳዊ ባህሎች የብሄረሰቡን የአለባበስ፣ የአመጋገብ፣ የአኗኗር ሁኔታዎችን የሚገልጹ መሆናቸውን እንዲሁም በክዋኔው ላይ ከሚከወኑ ስነ ቃሎች መካከል ውዳሴዎችና የሙሾ ግጥሞች የሚቀርቡ ሲሆን ግጥሞቹ የሚቹ (ቿ)ን ማንነት፣ እምነት፣ የዘር ግንድ አመጣጥ ወዘተ የሚገልፁ ናቸው፡፡ የሙሾ ግጥሞቹም በሚች ቤተሰቦች፣ እና ልዩ ችሎታ ባላቸው ሰዎች የሚከወን መሆኑ ተገልጿል፡፡

በብሔረሰቡ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ወቅት የሚታዩ ጉዳዮች( የኑዛዜ ስርዓት፣ የአገናነዝ ሁኔታ፣ የአስከሬን ማቆያ ስፍራ፣ የመርዶ ነጋሪዎች ማንነት፣ የድግሱ ሁኔታ፣ የለቅሶው የቆይታ ጊዜ፣ የቀባሪዎች ማንነት፣ የመቅበርያ ቦታ እንዲሁም የተስካር ሁኔታ ምን እንደሚመስል በዝርዝር ተካቷል፡፡

በለቅሶው ስርዓቱ የሚስተዋለው የኑዛዜ ስርዓት ለሚች የሚከወን የለቅሶ ስርዓትን የሚወስን መሆኑ ተመልክቷል፡፡

የባላባት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ጊዜ የብሄረሰቡ አስተዳደራዊ ስርዓት የሚጠናከርበት እና የስልጣን ሽግግር የሚከናወንበት ሲሆን በወራሽ ምርጫ ጊዜ የብሄረሰቡ አባላት ሚና ከፍተኛ እንደሆነ አመላክቷል፡፡ በተጨማሪም የበኩር ልጅ የአባቱን ስልጣን ለመረከብ ቅድሚያ የሚሰጠው መሆኑ ተገልጿል፡፡ የቀብር ስፍራውም "ዱይ" በመባል የሚጠራና ለብቻው የተከለለ ስፍራ እንደሆነ በጥናቱ ተዳስሷል፡፡

የአዛውንቶች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ በተለየ መልኩ የሚከወነው በልጅ ልጆች መሆኑና የመቀበሪያ ቦታውም ዱይ የሚባል ሲሆን ከሚች የመኖርያ ቦታ ብዙም የማይርቅ እና መቃብር ቦታውም በሚች ጸታ ላይ መሰረት ያደረገ መሆኑን እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ በዚህ የመቃብር ቦታም ሴቶች በስተግራ በኩል ወንዶች በስተቀኝ በኩል እንደሚቀበሩ ተገልጿል፡፡

በወጣቶች የለቅሶ ስርዓት ወቅት ከፍተኛ ሃዘን እንደሚሆን እንዲሁም በህጻናት የለቅሶ ስርዓት ጊዜ ደግሞ ማልቀስ፣ ለለቅሶው ማከናወኛ የሚሆን ዝግጅት እንዲሁም መርዶ እንደማይከናወን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በለቅሶ ስርዓቱ ላይ መነሳት መውደቅ፣ ፀጉርን መላጩት፣ ጥቁር ልብስ ወይም የቆሸሸ ልብስ መልበስ፣ ፊትን ኖራና አፈር መቀባት፣ አንገት ላይ ማግ ወይም የጋቢ ጥለት ማሰር ወዘተ የሃዘን መግለጫ መንገዶች እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

# ዋቢዎች

ሕይወት አበሩ፡፡ "የመኢኔት ብሄረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርአት ክዋኔ፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ የኤም.ኤ ዲማጽ፣ 2003፡፡

ማናዬ እንግዳወርቅ፡፡ "በደብረማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ንጽጽራዊ ጥናት" አዲስ አበባ

ዩኒቨርሲቲ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ የኤም.ኤ ዲማጽ፣2005።

ሞገስ ሚካኤል። "በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ስነስርአት፣ በስርአቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔው።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ የኤም.ኤ ዲማጽ፣2002።

ብርሃኑ አይሳብ፣ ዲስት ያብ /የዲዚ ሰው/፣ 1997።

ታደመ ወርቁ ብላታ፣ "የዲዚ ብሔረሰብ ባህል በማጂ አውራጃ ሚገኙ ብሔረሰቦች አመጣጥና ባህል"፣ ያልታተመ፣ ማጂ አውራጃ 1979።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር። *የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት።* አዲስ አበባ፣ ባናዊ ማተሚያ ቤት፣ 6ኛ ዕትም፣ 1992።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል። *አማርኛ መዝገበ ቃላት።* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1993።

አንደኛው ዙር የቤንች ማጂ ዞን ብሄረሰቦችና ህዝቦች የባህልና የቋንቋ ሲምፖዚየም ጥናት፣ያልታተመ ፣ 2005

አየሁሽ ቶማ። "የወላይታ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ የኤም.ኤ ዲማጽ፣ 2005።

ከበደ ተሰማ /ሌ/ኮ፣ *የማጂ ጎልዲያ ውበት፣* አዲስ አበባ፣ 1953።

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ። *"መጽሃፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሀዲስ"።* አዲስ አበባ። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤1948 ዓ.ም

ውቤ ታደገ። "የቤንች ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ የኤም.ኤ ዲማጽ፣ 2005

ዘላለም ፋንቱ። "የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ በበና ፀማይ ወረዳ።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ የኤም.ኤ ዲማጽ፣ 2004።

ዘሪሁን አስፋው። *የስነ-ጽሁፍ መሰረታውያን*። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣1992።

*የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፕሮፋይል*። በብሔረሰቦች ምክር ቤት በባህልና ቋንቋ ታሪክና ቅርስ ጥናት ተቋም የተዘጋጀ፣ ሀዋሳ፣ ፍቅረ ሳላም ማተሚያ ቤት፣ 2001።

የደቡብ ብሔር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቋንቋና ታሪክ ቅርስ ጥናት ተቋም። *የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ፕሮፋይል*። ሀዋሳ። ፍቅረሰላም ማተሚያ ቤት። 2001።

የዲዚ ብሔረሰብ የአጭር ታሪክና ባህል ጥናት፣ በቤንች ማጂ ዞን ባህልና ማስታወቂያ መምሪያ የተዘጋጀ፣ 1988።

ፈቃደ አዘዘ፤ *የስነቃል መምሪያ፤* አዲስ አበባ፣ ኢተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት መረዳጃ ተቋም፣ 1991።

Abdulla Abdurahman. "Harari Funeral Customs." *Ethnological Society Bulletin*. Ed. Alula Pankhurst vol. 1. No. 1. Addis Ababa, Addis Ababa University press, 2002.

Andargachew Tesfaye. "The Funeral Customs of the Kottu of Harar." *Ethnological Society Bulletin.* Ed. Alula Pankhurst. Vol.1, No. 7. Addis Ababa, Addis Ababa University, 2002.

Bauman, Richard. *Story, Performance and Event*: Contextual Studies of oral Narrative. Cambridge: Cambridge University Press, 1984.

--------------------------. *Verbal Art as Performance.* Rowley, Mass: Newbury House Publishers, 1977.

Brown, Inc Corinne. *Understanding Others Cultures*. Prentice Hall Inc ; Englewood Cliffs N.J, 1963.

David E. Gray. *Doing Research in Real World.* London .SAGE Publications Thousand Oaks ,New Delhi 2004.

Fasika Bellete. "The Death Customs among the Amharas of Šäwa"." *Ethnological Society Bulletin.* Ed Alula Pankhurst Vol. 1 No 7, Addis Ababa, Addis Ababa University Press. 2002.

Finnegan, Ruth. *Oral Poetry: Its Nature, Significance and Social Context.* Cambridge: Cambridge University Press, 1977.

-----------------------. *Oral Tradition and the Verbal Arts: A Guide to Research Practices.* New York: Thomson Publishing Company, 1992.

Goldstein, Kenneth. *A Guide for Field Workers in Folklore*. American Folklore Society by Folklore Associates, INC. 1964.

Hallam, Elizabeth. "Death and the Transformation of Gender in Image and Text" in D. Field, J. Hockey and N. Small (eds.) *Death, Gender and Ethnicity*. London: Rutledge, 1997. PP.108- 124.

Kottack, Phillip. *Anthropology the Explanation and Human Diversity.* McGraw-Hill: Companies inc, 2002.

Sims, Martha. and Martine Stephens. *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Taditions.* Ohio: Utah State University Press. 2005.

*World Book of Encyclopedia*. *World book- Child craft International*, Inc. Vol,5. USA. 1978.

# አባሪዎች


## አባሪ አንድ፡ ለቃለ መጠይቅ የተዘጋጁ ጥያቄዎች

1. የዲዚ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ታሪክ ምን ይመስላል?
2. ለቅሶ በዲዚ ብሔረሰብ ዘንድ እንዴት ይገለጻል?
3. ስንት ዓይነት የለቅሶ ስርዓት ብሔረሰቡ ያካሂዳል?
4. ሰው ሊሞት መሆኑን እንዴት ይታወቃል?
5. መርዶ የሚያረዱት ሰዎቸ እነማን ናቸው?
6. የሩቅ ዘመድ ሳይሰማ የሚቀበርበት ሁኔታ ይኖራል?
7. ሟች ከሞተ በኂላ ምን ይደረጋል? የእያንዳንዱ ቅደም ተከተል ምን ይመስላል?
8. ከቀብር በፊት ምን ይደረጋል? እስከስንት ቀን ሊወስድ ይችላል? እነማን ናቸው ከቀብር በፊት ያለውን ስርዓት የሚያዘጋጁት?
9. አስክሬኑ በምን ይቀመጣል? ከምን ይሰራል? ማን ያዘጋጀዋል?
10. አስክሬን እንዴት ሆኑ ይመጣል? የመጠበቅ ኃላፊነቱ የሚሰጠው ለማን ነው? አስክሬን የሚገንዘው ማን ነው? ለምን?
11. የቀብር ቦታው የት ነው? ለምን እና በማን ተመረጠ?
12. አስክሬኑን ማን ይሸከመዋል? ስንት ሰው ?ለምን ?
13. ሟች ከሞተ በኂላ የለቅሶ ስርዓት የሚከናወነው ወይም ቀብር የሚደረገው በስንት ሰዓት ነው? ለምን?
14. ለእያንዳንዱ የለቅሶ ዓይነት ምን ምን ዝግጂቶች ይከናወናሉ? ትርጉማቸውስ?
15. በየትኛው የእድሜ ክልል ያለ ሰው ሲሞት ነው በጣም የሚለቀሰው? ለምን? ምን ምን እየተባለ ይለቀሳል?
16. በተቃራኒው ሐዘኑ የማይበዛውስ በየትኛው የእድሜ ክልል ውስጥ ያለ ሰው ሲሞት ነው? ለምን?
17. ከለቅሶው ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ቁሶች አሉ? ምን አይነት? ከምን ይሰራሉ? ለምን አገልግሎት ይውላሉ? ከሟች ጋር የሚያገናኛቸው ነገር አለ?
18. ከቀብር በኂላ በኂላ እስከስንት ቀን ይለቀሳል? ምን ምን ዝግጂቶች ይዘጋጃሉ?

## አባሪ ሁለት፡- የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ተ.ቁ | መረጃ አቀባይ ስም | ዕድሜ | ጾታ | ሥራ | መረጃ የተሰበሰበት ቦታ | የሰጡት መረጃ አይነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ታደመ ኮመሩት | 72 | ወ | ጡረተኛ | ቱም | የለቅሶ ታሪካዊ ዳራ እና ስርዓተ ክዋኔ |
| 2 | አቶ ባልኩ ኩሙ | 88 | ወ | የሀገር ሽማግሌ | ማጂ | የክዋኔ ስርዓት |
| 3 | አቶ ዘለቀ ገሩ | 44 | ወ | የቀበሌ ሊቀመንበር | ማጂ | ስርዓተ ክዋኔ እና አጠቃላይ የትርጉም ስራ |
| 4 | አቶ አንያብ በይቲ | 70 | ወ | የሃገር ሽማግሌ | ቱም | የለቅሶ ታሪካዊ ዳራ እና ስርዓተ ክዋኔ |
| 5 | አቶ ካሳሁን ሽብሩ | 38 | ወ | ጋዜጠኛ | ሚዛን | የሙሾ ቃል ግጥም እና ውዳሴ ትርጉም |
| 6 | አቶ ካሳሁን ኦሊባብ | 32 | ወ | የመንግስት ሰራተኛ | ቱም | ታሪካዊ ዳራ |
| 7 | ወ/ሮ አስናቀች እሸቱ | 35 | ሴ | ጋዜጠኛ | ሚዛን | የሙሾ ቃል ግጥም እና ውዳሴ ትርጉም |
| 8 | ወ/ሮ ባቡ ኮዝ | 45 | ወ | የቤት እመቤት | ማጂ | የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ |
| 9 | አቶ ቸሬ አኮ | 85 | ወ | አርሶ አደር | ማጂ | የለቅሶ ታሪካዊ ዳራ እና ስርዓተ ክዋኔ |
| 10 | ወ/ሮ ማርያሜ ኒያንግ | 48 | ሴ | የቤት እመቤት | ማጂ | የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ |
| 11 | አቶ ኪያዝ ባህሩ | 61 | ወ | አርሶ አደር | ቱም | የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔና ዳራ |
| 12 | አቶ ኮይሲ ጋትና | 35 | ሴ | የቤት እመቤት | ማጂ | የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ |
| 13 | ወ/ሮ ውልቤ ቡርጂ | 45 | ሴ | የቤት እመቤት | ማጂ | የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ |
| 14 | አቶ ሰንበት ቻሞ | 40 | ወ | ነጋዴ | ማጂ | የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ |
| 15 | አቶ ኪያዝ ጊሞ | 50 | ወ | አርሶ ሰደር | ቱም | የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 16 | አቶ ጸጊ ባቻ | 45 | ወ | ጦረተኛ | ማጂ | የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ |
| 17 | ወ/ሮ ኮምቱ አኩ | 43 | ሴ | የቤት እመቤት | ማጂ | የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ እና ታሪካዊ ዳራ |
| 18 | ወ/ሮ ባቡ ኮዝ | 40 | ሴ | የቤት እመቤት | ማጂ | የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ |
| 19 | አቶ ጎጉ ንጉሴ | 55 | ወ | አርሶ አደር | ቱም | የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ |
| | | | | | | |


ADMINISTRATIVE MAP OF BENCH MAJI ZONE
SNNPRS
Sheka
GAMBELLA
KEFFA
Guraferda
Sheka
Semen Bench
Mizan Aman Town
Southern Bench
Shay Bench
MEANT GOLDIYA
Minit Shasha
BERO
Surima
MAJI
SUDAN
DEBUB OMO
N
LEGEND
International boundary
Region boundary
Zonal boundary
Gravel road.
Dry weather road
Town.
Scale
10 0 10 20 Kilometers